# ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

## 1922 - 1927





ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ

# ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

## 1922 - 1927

እምኒ ሐየውነ ለእግዚአብሔር ነሐዩ

ብንኖርም ለእግዚአብሔር እንኖራለን

ሮሜ ምዕራፍ 14 ቍጥር 8


## መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ

አሰናጅ - አምኃ መርስዔ ኀዘን



አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ
ፖ ሣ ቁጥር 1176
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ. + 251-011-123 97 46
ፋክስ. + 251-011-124 32 91
ኢሜል: aau.press@ethionet.et

© አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 2009 ዓ. ም.

ISBN 978-99944-52-75-0

በኢክሊፕስ ማተሚያ ቤት ታተመ

## መግለጫ

ይህ መጽሐፍ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የዘመን ታሪክ ውስጥ እስከ ጠላት ወረራ ዘመን ያለውን አንዱን ክፍል በመጠኑ የያዘ ነው።

ጽሑፉን በመገልበጥ እርዳታ ላደረጉልኝ ወዳጆቼም ከልብ የሆነ ምስጋና አቀርባለሁ።

1938 ዓ.ም.
መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ

## ከደራሲው

ትምህርተ ሕፃናት፣ 1917 ዓ.ም.
የአማርኛ ሰዋስው በአዲስ ሥርዓት የተሰናዳ፣ 1935 ዓ.ም.
የአማርኛ ሰዋስው 1-2ኛ ክፍል፣ 1936 ዓ.ም.
የአማርኛ ሰዋስው መክፈቻ፣ 1936 ዓ.ም.
የትእምርተ መንግሥት ታሪክ፣ 1936 ዓ.ም.
የቤተ ክርስቲያን ዜና መጀመሪያ ቍጥር፣ 1938 ዓ.ም.
ግ ን ነ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጐንደርን የመጐብኘታቸው ታሪክ፣ 1939 ዓ.ም.
ዐውደ መዋዕል፤ 1939 ዓ.ም.
የኢትዮጵያ መዝገበ ዕለታት፣ 1939 ዓ.ም.
የንጉሥ ኃይለ ሥላሴ ዕረፍት መታሰቢያ፣ 1940 ዓ.ም.
ሢመተ ሊቀ ጳጳሳት ኢትዮጵያዊ፣ 1942 ዓ.ም.
የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትሪያርክ፣ 1956 ዓ.ም.
የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 1999 ዓ.ም.
ትዝታዬ ስለ ራሴ የማስታውሰው፣ ዋሺንግተን ዲሲ፣ 2001 ዓ.ም.
ትዝታዬ ስለ ራሴ የማስታውሰው፣ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት፣ አ/አ፣ 2002 ዓ.ም.
የዘመናት ማገናዘቢያ፤ ኒው ዮርክ፣ 2004 ዓ.ም
የኢትዮጵያና የእንግሊዝ ሶማሊላንድ የወሰን መካለል ታሪክ፣
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 2007 ዓ.ም.

### ትርጒም ሥራ አዘጋጅተው ያሳተሟቸው መጻሕፍት

ጥበብን መፈለግ 1-3ኛ መጽሐፍ፣ 1946 ዓ.ም.
ሔሮዶቱስ የጥንት ታሪክ 1-4ኛ መጽሐፍ፣ 1948 ዓ.ም.
ጽሑፎችን ሰብስበው ያዘጋጇቸውና የታተሙ መጻሕፍት
ፍሬ ከናፍር ዘቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ 1-6ኛ መጽሐፍ፣ 1944 ዓ.ም.

### ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የተዘጋጁ የቅዱሳት መጻሕፍት ሥራዎች።

መቅድመ ወንጌል ንባብና ትርጓሜው፣ 1920 ዓ.ም.
የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዜና፣ 1938 ዓ.ም.

### ከሊቃውንት ጋር የተሠሩ

አረጋዊ መንፈሳዊ ንባብና ትርጓሜ፣ 1920 ዓ.ም.
መጽሐፈ ሲራክ፣ 1914 ዓ.ም.
ሰበዓቱ ኪዳናት፣ 1920 ዓ.ም.
የቤተ ክርስቲያን ጸሎት በግእዝና በአማርኛ፣ 1942 ዓ.ም.
መጽሐፈ ቅዳሴ በግእዝና በአማርኛ 1920 ዓ.ም.
The Liturgy of the Ethiopian Church 1959
(Translated by Rev. Marcos Daoud, Revised by H.E. Blatta Marse Hazen)

### በኮሚቴ የተሠሩ

መጽሐፍ ቅዱስ በአማርኛ፣ በብላታ መርስዔ ኀዘን ሊቀ መንበርነት
(1939 - 53 ዓ.ም.) ተሠርቶ የታተመ።
ፍትሐ ነገሥት በግእዝና በአማርኛ፣ በብላታ መርስዔ ኀዘን ሊቀ መንበርነት
(1962 - 63 ዓ.ም.) ተሠርቶ የታተመ።

### ያልታተሙ

የዘመን ታሪክ ትዝታዬ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት 1934 – 1937 ዓ.ም.
በአንኮበር ከተማ የሸዋን ነገሥታት መቃብር መጐብኘት ሰኔ፣ 1937 ዓ.ም.
አስማተ ሙታን፣ ለታሪክ ምርምር የሚረዳ የሙታን ማስታወሻ።

# ማውጫ


መግቢያ ....... ix

ቀዳሚ ቃል ....... xiii

ምዕራፍ 1 ....... 1

1922 ዓመተ ምሕረት....... 1

ስለ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልደትና አስተዳደግ ....... 1
የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ስለ መሆናቸው....... 4
በንጉሠ ነገሥት ዙፋን ስለ መቀመጣቸው ....... 5
የዙፋን መውረስ አዋጅ እንደ ተነገረ ....... 6
ለበጌምድር ሕዝብ የተነገረ አዋጅ....... 7
ራሶች ወደ አዲስ አበባ ስለ መጠራታቸው ....... 8
የሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ከእሳት ቃጠሎ እንደ ዳነ....... 9
ስለ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ የአርባ ዕለት ተዝካር ....... 10
ስለ ዘማች መመለስ....... 11
ስለ ሹመት....... 14
ሐዘንን ለመግለጽ ከየአውራጃው ስለመጡ መኳንንት ....... 14
ለሕዝብ የተነገሩ አዋጆች ....... 14
ወታደሮችን ስለ ማሠልጠን ....... 17
ስለ አውሮፕላን ነጂዎች ....... 18
ስለ ጦር መኰንኖች ....... 18
ስለ ሹም ሽር....... 19
የመኪና መንገዶች ሥራ ....... 21
በወሰን ላይ ስለ ደረሰ ግጭት....... 22
ስለ ታላላቅ ሰዎች ሞት ....... 25

ምዕራፍ 2 ....... 27

1923 ዓመተ ምሕረት....... 27

ስለ ወንጀለኛ መቅጫ ደንብ....... 27
ስለ አጼ መስቀል በዓል ....... 28
ስለ መስቀል በዓል ....... 28
በሐሰት ወሬ ስለ ደረሰ ቅጣት....... 30
በአውሮፕላን ነጂነት ስለተመረቁ ወጣቶች ....... 30
ስለ ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ባርያ ጋብር ሞት ....... 32
በከተማ ስለተደረገ ዝግጅት ....... 34
ለዘውድ በዓል ከያገሩ ስለ መምጣት ....... 35

የመንግሥት መልእክተኞች መግባት ....................................................36
ከበዓሉ በፊት ስለተፈጸመ ሥነ ሥርዓት....................................................43
በጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ስለተደረገው ዝግጅት ....................................................44
በዘውዱ በዓል ዋዜማ ....................................................44
ስለ ሥርዓተ ንግሥ ....................................................48
ለአልጋ ወራሹ ስለተደረገው ሥነ ሥርዓት ....................................................54
የእቴጌ አነጋገሥ ....................................................55
ስለ ጸሎተ ቅዳሴና ስለ ዑደት ....................................................56
ወደ ቤተ መንግሥት ስለ መመለስ ....................................................59
ስለ ግብሩ ሥርዓት ....................................................59
የዘውዱ በዓል በያገሩ ስለ መከበሩ....................................................60
ንጉሠ ነገሥቱ ምሕረት ስለ ማድረጋቸው ....................................................61
ደብረ ሊባኖስን ስለ መሳለም ....................................................61
የጳጳሳት ሀገረ ስብከት ስለ መደልደሉ....................................................64
በጥርና በየካቲት ወር ስለተሰጠ ሹመት....................................................66
በመስፍኑ መወለድ ስለተደረገ ደስታ....................................................67
ስለ አዲስ ቀረጥ አዋጅ....................................................68
ስለ ፋሲካ በዓል....................................................68
ስለ ሹመት....................................................69
ስለ ቅብዓ ሜሮን ....................................................70
የትምህርት ቤቶች የሽልማት መስጫ በዓል ....................................................71
ስለ ዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት....................................................74
ስለ ሕገ መንግሥት ....................................................75
ስለ ግብዣ....................................................79
የነፋስ ስልክ ቤት እንደ ተመሠረተ ....................................................80
ስለ ልዩ ልዩ ነገር ....................................................80
ስለ ታላላቅ ሰዎች ሞት ....................................................81

ምዕራፍ 3 ....................................................83

1924 ዓመተ ምሕረት....................................................83

ስለ ዘመን መለወጫ በዓል ....................................................83
ስለ አጼ መስቀል በዓል ....................................................84
ስለ መስቀል የደመራ በዓል ....................................................84
ስለ ውጋዴን....................................................85
ስለ ሴቶች ተማሪ ቤት....................................................87
ስለ ኢትዮጵያ ባንክ ምረቃ....................................................89
ስለ ምክር ቤት መከፈት....................................................91
የበጎ ፈቃድ መልእክተኞች ወደ ጃፓን ስለ መሄዳቸው....................................................96
ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን አውሮጳን ስለ መጐብኘታቸው ....................................................98
ስለ ሹመት....................................................99
ስለ ወሰን ክልል ኮሚሲዮን ....................................................100
ለወሰኑ ክልል መነሻ ስለሆነው ውል ....................................................102
የክልሉ ሥራ አጀማመር....................................................103
የሕገ መንግሥትን ትርጓሜ ስለ ማስረዳት....................................................105
ታላቅ ግብር....................................................105
ስለ ሹመት ....................................................106
የቤተ ነጋሢ ሠርግ ....................................................107

ልጅ ኢያሱ ስለ ማምለጣቸውና እንደገና ስለ መያዛቸው ....................110
የቤተ ነጋሢ ጋብቻ ....................117
ስለ ሹም ሽር ....................125
በጐጃም የተነገረ አዋጅ ....................125
በራስ ኃይሉ ላይ ስለተፈረደው ፍርድ ....................126
ስለ ልዩ ልዩ ነገር ....................130
ስለ ታላላቅ ሰዎች ሞት ....................132
ምዕራፍ 4 ....................133
1925 ዓመተ ምሕረት ....................133
ስለ ዘመን መለወጫና ስለ አጼ መስቀል በዓል ....................133
የመስቀል ደመራ በዓል ....................133
ከራስ ኃይሉ ስለተወረሰው ገንዘብ ....................134
በደብረ ማርቆስ ከተማ ስለተደረገ አምባጓሮ ....................134
ስለ ልዩ ልዩ ነገር ....................138
ወደ ወሎ ስለተደረገ ጉዞ ....................141
ስለ ልዕልት ዘነበ ወርቅ ሞት ....................143
ስለ ሐዘን ልክና ሥርዓት የተነገረ ማስታወቂያ ....................146
ስለ ልዑል ራስ ጉግሣ አርአያ ሞት ....................147
የልዕልት ዘነበ ወርቅ የአርባ ፍትሐት ....................148
ስለ ልዩ ልዩ ነገር ....................150
ስለ አቡነ ሳዊሮስ ሞት ....................156
ስለ ታላላቅ ሰዎች ሞት ....................158
ምዕራፍ 5 ....................161
1926 ዓመተ ምሕረት ....................161
ስለ ዘመን መለወጫ በዓል ....................161
ስለ አጼ መስቀል በዓል ....................161
ስለ መስቀል በዓል ....................162
እቴጌ ወደ ኢየሩሳሌም ስለ መሄዳቸው ....................162
ስለ ልዩ ልዩ ነገር ....................165
ስልክ ሥራን ስለ መጐብኘት ....................168
ስለ ሦስተኛው ዓመት የዘውድ በዓል ....................168
ስለ ፊታውራሪ ወጋየሁ ሞት ....................169
ደብረ ብርሃንንና አንኮበርን ስለ መጐብኘት ....................170
የራዲዮ ቴሌግራፊክ መሥሪያ ቤት እንደ ተመረቀ ....................171
ስለ ወሰን ክልል ሥራ ....................172
ስለ ሙሴ ባይትዝ ሞት ....................174
ወታደሮችን ስለ ማሠልጠን ....................176
የጦር ሰንደቅ ዓላማ ስለ መስጠት ....................176
ስለ ሹም ሽር ....................180
ልዑል መኰንን መስፍነ ሐረር ሐረርጌን ስለ መጐብኘታቸው ....................181
ከቀላድ ስለሚተርፍ መሬት የተሰጠ አዋጅ ....................182
ልዕልት ወለተ እስራኤል ሴት ልጅ በደኅና ስለ መገላገላቸው ....................182
ስለ ልዩ ልዩ ነገር ....................183
ስለ ታላላቅ ሰዎች ሞት ....................184

ምዕራፍ 6 ....................193
1927 ዓመተ ምሕረት....................193
ወደ ወልወል ስለ መግባት ....................193
ስለ ወልወል ግጭት....................196
ወደ ሐራዲጌት ስለ መመለስ....................202
ወደ ደጋህቡር ስለ መመለስ ....................205
ከደጋህቡር ወደ ጅጅጋ ስለ መመለስ....................206
ኮሚሲዮኑ ወደ ዋና ሰፈሩ ስለ መመለሱ ....................206
ወደ አዲስ አበባ ስለ መመለስ ....................207
የሥራውን የመጨረሻ ስምምነት ስለ መፈረምና ስለ ማስረከብ....................207
ስለ ልዩ ልዩ ነገር....................207
አባሪ 1 ....................211
የንጉሣውያን ቤተሰብ አጭር የሕይወት ታሪክ ....................211
መነን አስፋው (እቴጌ)....................211
መኰንን ኃይለ ሥላሴ (ልዑል) ....................211
መኰንን ወልደ ሚካኤል (ልዑል ራስ) ....................212
ምኒልክ (ዳግማዊ፣ አጼ)....................212
ሣህለ ሥላሴ ኃይለ ሥላሴ (ልዑል)....................212
ሣህለ ሥላሴ (ንጉሥ)....................213
ሮማነ ወርቅ (ልዕልት)....................213
ስኂን ሚካኤል (ወይዘሮ)....................213
ተናኘ ወርቅ ኃይለ ሥላሴ (ልዕልት) ....................213
አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ (ልዑል አልጋ ወራሽ)....................214
ኢያሱ ሚካኤል (ልጅ፣ አቤቶ)....................214
እምሩ ኃይለ ሥላሴ (ልዑል ራስ)....................215
እስክንድር ደስታ (ሪር አድሚራል) ....................215
እጅጋየሁ አስፋ ወሰን (ልዕልት) ....................215
ወለተ እስራኤል ሥዩም (ልዕልት)....................216
ዘነበ ወርቅ ኃይለ ሥላሴ (ልዕልት)....................216
ዘውዲቱ (ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት)....................216
የሻሸ ወርቅ ይልማ መኰንን (ልዕልት) ....................217
ይልማ መኰንን (ደጃዝማች)....................217
ጣይቱ ብጡል (እቴጌ) ....................217
ፀሐይ ኃይለ ሥላሴ (ልዕልት)....................218
አባሪ 2 ....................219
የታላላቅ ሰዎች አጭር የሕይወት ታሪክ ....................219
ሀብተ ማርያም ገ/እግዚአብሔር (ደጃዝማች) ....................219
ሆጄሌ(ሼኽ) ....................219
ሎሬንዞ ታእዛዝ (ብላቴን ጌታ)....................220
መልአኩ በያን (ዶ/ር)....................220
መስፍን ስለሺ (ራስ) ....................221
መንገሻ ዮሐንስ (ልዑል ራስ)....................221
መኰንን ሀብተ ወልድ (አቶ) ....................221
መኰንን እንዳልካቸው (ራስ ቢትወደድ)....................222

መኰንን ደስታ (ደጃዝማች) ......222
ሙሉጌታ ይገዙ (ራስ፣ ፊታውራሪ) ......223
ሚሻካ ባቢቼፍ (ሻለቃ) ......223
ሚካኤል (አቡነ) ......223
ሚካኤል (ንጉሥ) ......224
ማኅተመ ሥላሴ ወ/መስቀል (ብላቴን ጌታ) ......224
ሣህሌ ፀዳሉ (ብላቴን ጌታ) ......225
ሥዩም መንገሻ (ልዑል ራስ) ......225
ሽመልስ ሀብቴ (ፊታውራሪ) ......226
ቄርሎስ (አቡነ) ......226
በሻህ ውረድ ሀብተ ወልድ (አቶ) ......227
በየነ መርዕድ (ደጃዝማች) ......227
ባልቻ ሳፎ (ደጃዝማች፣ አባ ነፍሶ) ......227
ብሩ ወልደ ገብርኤል (ራስ) ......228
ተሰማ ባንቴ (ፊታውራሪ) ......228
ተሰማ እሸቴ (ነጋድራስ) ......228
ተሰማ ናደው (ራስ ቢትወደድ) ......229
ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም (በጅሮንድ) ......229
ታከለ ወልደ ሐዋርያት (ደጃዝማች) ......229
ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል (ፊታውራሪ) ......230
ኃይለ ሥላሴ ዓባይነህ (ደጃዝማች) ......230
ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ (ደጃዝማች) ......230
ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት (ልዑል ራስ) ......231
ኃይሉ ከበደ (ደጃዝማች፣ ሌ/ጄኔራል) ......231
ኀሩይ ወልደ ሥላሴ (ብላቴን ጌታ) ......232
ነሲቡ ዛማኤል (ደጃዝማች) ......232
አስፋው ዓሊ ......232
አበራ ካሣ (ደጃዝማች) ......233
አበበ አረጋይ (ራስ) ......233
አበበ ዳምጠው (ሜ/ጄኔራል) ......233
አባ ጅፋር ......234
አብርሃም (አቡነ) ......234
አየለ ገብሬ (ብላታ) ......234
አፈ ወርቅ ወልደ ሰማዕት (ግራዝማች) ......235
ኦኔሲሞስ ነሲብ (አቶ) ......235
ከበደ መንገሻ (ራስ) ......236
ከበደ ተሰማ (ደጃዝማች) ......236
ከበደ ተፈሪ (ዋግ ሹም) ......236
ካሣ ኃይሉ (ልዑል ራስ) ......237
ክፍሌ እርገቱ (ደጃዝማች) ......237
ወልደ ሐና (መልአከ ሕይወት) ......237
ወልደ መስቀል ታሪኩ (ጸሐፊ ትእዛዝ) ......238
ወልደ ጊዮርጊስ ወ/ዮሐንስ (ጸሐፊ ትእዛዝ) ......238
ወልደ ጻድቅ ጐሹ (ቢትወደድ) ......238
ወርቅነህ እሸቴ (አዛዥ) ......239
ዓሊ ኑር (ቀኛዝማች) ......239

ዓምደ ሚካኤል ደሳለኝ (አቶ) ....................240
ዘውዴ በላይነህ (ብላታ) ....................240
ይስሐቅ (አቡነ) ....................240
ዮፍታሔ ንጉሤ (ቀኝ ጌታ) ....................241
ደስታ ዳምጠው (ደጃዝማች፣ ራስ) ....................242
ገብረ ክርስቶስ ወልደ ዮሐንስ (ሊቄ፣ አፈ ንጉሥ) ....................242
ገብረ ጊዮርጊስ (እጨጌ፣ በኋላ አቡነ ባስልዮስ) ....................242
ጉግሣ ወሌ (ራስ) ....................243
ጌታቸው አባተ (ራስ) ....................243
ጠናጋሻው በሀብቴ (ከንቲባ) ....................244
ጴጥሮስ (አቡነ) ....................244

# ፎተግራፎች

ተፈሪ በልጅነት ዕድሜ ....................2
ተፈሪ ዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት ተማሪ ሆነው ....................4
ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ....................5
ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ ....................8
የአውሮፕላን ነጅነት ተማሪዎች ከአስተማሪያቸው ጋር ....................18
ፊታውራሪ ታፈሰ፣ ሙሴ ቬርዴር፣ ካፕቴን ዊድሜር ....................19
አዛዥ ወርቅነህ ....................21
በሐርጌሳ የኢትዮጵያ ቆንስል ....................23
ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ባርያ ጋብር ....................33
ለበዓሉ የተዘጋጀ ቅስት ....................35
የክብር አጃቢዎች ልዑል ራስ ካሣ (ግራ) ልዑል ራስ ሥዩም (ቀኝ) ....................39
ልዑል ራስ ሥዩም (ግራ) እና ልዑል ራስ ካሣ ከዱክ ኦፍ ግሎስተር ጋር ....................39
ሙዚቀኞች ከመሪያቸው ከአባ ቆሮ ጋር ....................40
እንግዶቹን ተቀባይ የክብር ዘብ ....................40
ዱክ ኦፍ ግሎስተርን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ባቡር ጣቢያ ሲቀበሏቸው ....................41
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የፈረንሳዩን ማርሻል ፍራንሼን ሲቀበሉ ....................41
ልዑል መኰንን የጃፓኑን መልእክተኛ ሲቀበሉ ....................42
የስዊድን መልእክተኞች ....................42
የዳግማዊ ምኒልክ ሐውልት ሲመረቅ ....................46
ለንግሡ በዓል ወደ መናገሻ ጊዮርጊስ ጉዞ ....................47
ከንግሡ በኋላ ዙፋን ላይ ተቀምጠው ....................58
በሠረገላ ወደ ቤተ መንግሥት ሲመለሱ ....................59
ሐረር ላይ የንግሡ በዓል ሲከበር ....................61
ዳግማዊ ምኒልክ ያሠሩት በኋላ የፈረሰው ገዳም ....................62
የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ....................65
አቡነ ቄርሎስ ....................71
የእቴጌ መነን ተማሪ ቤት ተማሪዎች ....................87
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ምክር ቤቱን ሲከፍቱ ....................91
የምክር ቤቱ መማክርት ....................92

የኢትዮጵያ መልእክተኞች በጃፓን..........97
ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን በርሊን ሲደርሱ..........98
የኢትዮጵያ የወሰን ተካላዮች..........101
የእንግሊዝ ወሰን ተካላዮች..........102
የልዑል አልጋ ወራሽና የልዕልት ወለተ እስራኤል ተክሊል በዓል..........108
ልጅ ኢያሱ ተይዘው አባይን ሲሻገሩ..........117
የልዕልት ዘነበ ወርቅና የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ የሠርግ በዓል..........118
እቴጌ መነን..........119
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ..........119
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከልዑል መኰንን ጋር..........120
ጃንሆይና እቴጌ ዙፋን ላይ ተቀምጠው..........120
ልዕልት ፀሐይ..........121
ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን..........121
ንጉሣዊ ቤተሰብ..........122
ግብዣ ላይ..........123
ከጀርመን ሚኒስትርና ባለቤቱ ጋር..........123
ልዑል መኰንን ከራስ ሙሉጌታ ጋር..........124
ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሲያስቀድሱ..........124
ራስ ኃይሉ በእስር ላይ..........127
የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት..........130
ልዕልት ዘነበ ወርቅ..........145
በአክሱም ምስል የተሠራው የቀድሞው የአራት ኪሎ ሐውልት..........151
አቡነ ሳዊሮስ..........157
እቴጌ መነን ኢየሩሳሌምን ሲጐበኙ..........163-164
የሳን ሲር ጦር አካዳሚ ተማሪዎች..........166
1921 ዓ. ም. ገደማ በፈረንሳይ አገር የኢትዮጵያ ልጆች ማኅበር..........166
የክብር ዘበኛ ወታደሮች በዘመናዊ የጦር ስልት ሥልጠና ላይ..........177
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለጦር ሚኒስትሩ የሰንደቅ ዓላማ ሲሰጡ..........178
ጦሩ ለንጉሠ ነገሥቱ ሰላምታ እየሰጠ ሲያልፍ..........178
አዲስ አበባ በ1920ዎቹ..........185-192
ቀኛዝማች ዓሊ ኑር (ግራ) ከወታደሮቻቸው ጋር..........195
የኢትዮጵያ ጦር ከጠላት ምሽግ ፊት..........196
ካፒታኖ ቺማሩታ የኢጣልያው ጦር አዛዥ..........197
ሬሣና ቊስለኛ የሚያመላልሰው ካሚዮን..........201
በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት በዓለም ማኅበር..........209
ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት የስዊድንን አልጋ ወራሽ ሲቀበሉ..........210

# የፎተግራፎች ምንጭ

| ምንጭ | ገጽ |
|---|---|
| ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ | 2 (ከላይ ቀኝ) |
| መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ (ብላታ) | 21 |
| መንገሻ ሥዩም (ልዑል ራስ) | 39 |

| ምንጭ | ገጽ |
|---|---|
| ማኅደረ ብርሃን ሀገረ ጃፓን | 97 |
| ማርገሪት ደስታ (ወ/ሮ) | 166 |
| ታደለ ይድነቃቸው (አቶ) | 117 |
| ካሣ ከበደ (ዶ/ር) | 5 |
| ወመዘክር | 127፣ 192 (ከታች) |
| ዘውዴ ረታ (አምባሳደር) | 145 |
| ዘውዴ ገብረ ሥላሴ (ደጃዝማች) | 33 |
| ዜና ጳጳሳት ኢትዮጵያውያን | 157 |
| የመንበረ ፓትሪያርክ መጻሕፍት ቤት | 65 |
| Agnes Willoughby Bancroft | 35, 40 (ከታች), 41, 42, 46, 47, 57, 59 |
| Alex T. Curle Collection | 19, 23, 101 |
| Architectural Heritage A/Ababa | 188 (ከላይ), 192 (ከላይ) |
| Barder, Owen | 62 |
| Bundesacchiv | 98 |
| Ethiopia Photographed | 191 (ከላይ), 188 (ከታች) |
| Girard, Denis | 4, 130 |
| Keystone | 58 |
| Kronprinsparets orientresa | 122 (ከላይ) |
| L'Illustration | 108, 118 |
| Library of Congress | 2 (ከታች ግራ), 8, 163, 164 |
| London Illustrated News | 195, 196, 201 |
| Bernadotte Library's archive | የውስጥ ሽፋን, 210 |
| Pilote Oublie | 18 |
| Plowman, Stephen | 61, 102 |

# ካርታዎች


ግጭቱ የደረሰበትን አካባቢ የሚያሳይ ካርታ ........ 24
የኢትዮጵያና የእንግሊዝ ሱማሌ ወሰን ........ 104
ወልወል - የጦሩ አሰፋፈር ........ 198


# ሰነዶች


የዜግነት አዋጅ ........ 16
የመጀመሪያው የበረራ የምስክር ወረቀት ........ 31
*ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ* መስከረም 13 ቀን 1924 ዓ. ም. ........ 86
የአፈርሳታ አዋጅ ........ 154

# መግቢያ

ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ በሕይወት ዘመናቸው ያዩትንና የሰሙትን ታሪክ መዝግበው ለመጪው ትውልድ በማስተላለፍ ረገድ ሀገራዊ ኃላፊነታቸውንና ግዴታቸውን ለመወጣት ሞክረዋል። ከ1896 ዓ.ም. እስከ 1922 ዓ.ም. ድረስ ያለው የዳግማዊ ምኒልክ፣ የአቤቶ ኢያሱ፣ የንግሥት ዘውዲቱ የዘመን ታሪክ ትዝታቸው የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ በሚል ርዕስ በእኔ በልጃቸው አሰናጅነት በ1999 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ አሳታሚነት ታትሞ ወጥቷል። ከ1922 ዓ.ም. እስከ 1927 ዓ.ም. ድረስ ያለው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከፊል የዘመን ታሪክ ደግሞ እነሆ ለአንባቢዎች ቀርቧል።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በፋሽስት ወረራ ዘመን (1928 – 1933 ዓ.ም) ሎንዶን በስደት ላይ በነበሩበት ዓመታት በብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ተጀምሮ የነበረው ግለ ታሪካቸው እንደገና ታርሞ እንዲታተም ሲያስቡ ለዚህ ታላቅ ሥራ ለኃላፊነት የመረጡት ብላታ መርስዔ ኀዘንን ነበር። ቀኑ ላዩ ባልተጠቀሰበት አንድ ማስታወሻ ላይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሚከተለውን ጠበቅ ያለ አደራ ሰጥተዋቸው ነበር፤

> ከዚህ ቀጥሎ ያለውን እንድትሰራ በአደራ ቃል ነው የምንሰጥህ። ይኸንን የሕይወታችንን ታሪክ እንግሊዝ አገር ሆነን ስንጽፍ አንዳንድ በኪሳችን የነበሩ የእለት ስራችንን የምንጽፍባቸውን ማስታወሻዎች ብቻ ይዘን በመሆኑ የጎደለ ነገር አንዳንድ ሳይገኝ አይቀርምና እግዚአብሔር ጊዜ ሰጥቶን ለመሙላት እምንችልበት ጊዜ ካደረሰን አስታዋሽና አትጊ እንደትሆን. . .

ብላታ መርስዔ ኀዘንም ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማስታወሻ በመስከረም 19 ቀን 1940 ዓ. ም. በጻፉት መልስ ላይ የሚከተለው ይገኝበታል።

> ከዚያም በኋላ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ታሪክ በተባለ ስያሜ ከእኔ አንድ መጽሐፍ ይወጣል። ይህ መጽሐፍ በአካሄድና አሰካክ ከፊተኞቹ ምንም ቢለወጥ፤ አንድ ታሪክ ሌላውን ምንም ጊዜም እንደደገፈ ነው።. . .

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ብላታ መርስዔ ኀዘን የተለዋወጧቸው ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ማስታወሻዎችና እርማት ያደረጉበት የመጽሐፉ የመጀመሪያው ረቂቅ እኔ ዘንድ ይገኛሉ። ማስታወሻዎቹንና የመጽሐፉን ረቂቅ ወደፊት ለጥናትና የምርምር ተቋም የማበረክት ይሆናል።

ወደ ኋላ በመጽሐፉ የእርማት ሥራ ላይ በተጨማሪነት ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስና ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል ተሳትፈውበት የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ

ሥላሴ ግለ ታሪክ ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ በሚል ርዕስ የመጀመሪያው ቅጽ በ1965 ዓ. ም. ሁለተኛው ቅጽ ደግሞ በ1966 ዓ. ም. ለኅትመት በቅቷል።

ብላታ መርስዔ ኅዘን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጻፉት ማስታወሻ ላይ እንደጠቀሱት የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሙሉ ታሪክ ለመጻፍ እቅድ ነበራቸው። ለዚህ እቅዳቸው የመጀመሪያ ሥራ ያደረጉት የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ዲስኩሮች ሰብስቦ፣ አደራጅቶ በመጽሐፍ መልክ ማውጣት ነበር። እነኚህ ዲስኩሮች ፍሬ ከናፍር በሚል ርዕስ በ7 ቅጾች ታትመው ወጥተዋል።

ብላታ አንዳንዴ እስከ ሁለት፣ ሦስት የመንግሥት ሥራዎችን በኃላፊነት ደርበው ይሠሩ ስለነበረ የጽሑፍ ሥራዎቻቸውን የሚሠሩት በትርፍ ጊዜአቸው ብቻ ነበር። ስለዚህ ነበር የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሙሉ የዘመን ታሪክ የመሰለ ከባድ ሥራ በጡረታ ጊዜ ከመንግሥት የሥራ ኃላፊነት ከተላቀቁ በኋላ እሠራዋለሁ ብለው ያቆዩት።

ከአስተዳደር ኃላፊነት ለመጀመሪያ ጊዜ የተላቀቁት በ1963 ዓ. ም. በሙሉ ሚኒስትርነት ማዕረግ የታሪካዊ ቅርሳ ቅርስ አማካሪ ሆነው በተሾሙበት ጊዜ ነበር። በሕዝብ ቤተ መጻሕፍት ወመዘክር ሕንጻ ውስጥ ቢሮና ጸሐፊ ተሰጥቷቸው የጽሑፍ ሥራቸው ላይ ለማተኮር ቻሉ።

በዓመቱ በ1964 ዓ. ም. የሥነ ጽሑፍ አገልግሎታቸው ዕውቅና አግኝቶ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት ድርጅት የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ሽልማት ተሸላሚ ሆኑ።

ብላታ ለብዙ ጊዜ እንዲቋቋም ይመኙት የነበረው የአማርኛ መርሐ ልሳን (አካዳሚ) በዚሁ ጊዜ ተቋቁሞ ስለ ነበረ አባልና የመዝገበ ቃላት አዘጋጅ ንዑስ ኮሚቴው ሊቀ መንበር ሆኑ። ሥራውንም በደስታና በትጋት ማከናወን ቀጠሉ።

በዚሁ ወቅት ነበር በ1930ዎቹ ዓመታት ውስጥ ጀምረውት የነበረውን የዳግማዊ ምኒልክ፣ የአቤቶ ኢያሱ፣ የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱን የዘመን ታሪክ መጽሐፍ አርመውና አስተካክለው የጨረሱት። ቀጥለውም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን የዘመን ታሪክ ረቂቅ ማረምና ማስፋፋት ጀመሩ።

ይህ ጊዜ ለብላታ እጅግ በጣም አስደሳችና ውጤታማ ጊዜ ነበር። ግን ምን ይሆናል ብዙ አልሰነበተም። ሕይወታቸውንና ሰላማቸውን ያቃወሱ ሁለት ክስተቶች በተከታታይ ተፈጠሩ። የመጀመሪያው በግንቦት ወር 1965 ዓ.ም. የባለቤታቸው፣ የትዳር ጓደኛቸው የወይዘሮ እታገኘሁ ባዬ በድንገት በአደጋ መሞት ነበር። ሃምሳ ዓመታት ያህል አብረዋቸው የኖሩት የአጋሮቸው የወይዘሮ እታገኘሁ ሞት ለብላታ ከባድ ሐዘን ጣለባቸው። ሁለተኛው ደግሞ በ1966 ዓ.ም አብዮት ሳቢያ የተነሣው የሀገር ሁኔታ ነው። የቅርብ ወዳጆቻቸው ካለ ፍርድ መገደልና መታሰር፣ በሰዋሰው ትምህርት ያነጹዋቸው ወጣት ተማሪዎች የአብዮቱ ሰለባ መሆናቸውና በጠቅላላው በሀገራችን ላይ የደረሰው ሁኔታ በብላታ ላይ ሊፈጥርባቸው የሚችለውን ተስፋ መቁረጥና መሪር ሐዘን መገመት አይከብድም።

ምንም እንኳን በአብዮት ዘመን እስራትም ሆነ አንዳችም መንገላታት ባይደርስባቸውም በእነኚህ ሁሉ ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታዎች ምክንያት ብላታ አቅደውት የነበረውን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሙሉ የዘመን ታሪክ ሳይጨርሱት ቀሩ።

የታሪክና ዜና ማሰናጃ ጽሕፈት ቤት ዲሬክተር በነበሩበት ጊዜ ብዙ የመንግሥት ሰነዶችን ለመመርመር ዕድሉ ገጥሟቸው ስለነበር በርግጥም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሙሉ

ታሪክ በሚገባ ሊጽፉ ከሚችሉት ሰዎች መካከል አንዱ ብላታ መርስዔ ኀዘን ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመት አይከብድም። ይህም ብቻ ሳይሆን ስለ ዘመኑ ታሪክ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጋር ለብዙ ሰዓታት በግል ለመነጋገርም ዕድሉ ነበራቸው። በሥልጣን ቁንጮ ላይ የነበሩ በርካታ የንጉሡ ባለሥልጣናትም የቅርብ ወዳጆቻቸው ስለ ነበሩና ስለሚያምኗቸውም ብዙ የሰሙትና የሚያውቁት ነገር ይኖራል። እንደ ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት ያሉ አንዳንድ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተቃዋሚዎችም ወዳጆቻቸው ስለ ነበሩ የእነሱ አስተሳሰብና አስተያየት ምን እንደነበር ሊያካፍሉን ይችሉ ነበር ብዬ አምናለሁ።

ይህ መጽሐፍ የብላታ የመጨረሻው የዘመን ታሪክ መጽሐፍ ይሆናል። ከኢጣልያ ወረራ በኋላ ከ1933 ዓ. ም. እስከ 1937 ዓ. ም. ድረስ ያለውን የዘመን ታሪክ በከፊል ጽፈውታል። ግን ጽሑፉ ግርድፍ ረቂቅ ስለሆነ አይታተምም። የታሪክ ተመራማሪዎች ሊጠቀሙበት ስለሚችሉ ግን ረቂቁን ባለበት ሁኔታ በየቤተ መጻሕፍቱ እንዲገኝ ለማድረግ እሞክራለሁ። በልዩ ልዩ ርዕሶች ላይ የጻፏቸው ሌሎች ጽሑፎችን ግን ወደፊት ሰብስቤና በቅጽ ከፋፍዬ ለማሳተም እቅድ አለኝ።

በቀድሞ ዘመን አንዳንድ የሀገራችን ብሔረሰቦችና አካባቢዎች ይጠሩበት የነበረውን ስያሜ አሁን ተግባር ላይ በዋሉና ተቀባይነት ባላቸው አጠራሮችና ስያሜዎች ከመተካት በስተቀር በዋናው ጽሑፍ ላይ አንዳችም የተጨመረ ነገር የለም።

ይህን መጽሐፍ በማዘጋጅበት ጊዜ ታሪኩን የሚያዳብሩ ፎተግራፎች፣ ካርታዎችና የሰነድ ግልባጮች፣ ማብራሪያ የሚሰጡ ኅዳጎች (ግርጌ ማስታወሻዎች) ጨምሬአለሁ። (ብመኅ) የሚል ምልክት ያለባቸው ኅዳጎች በደራሲው በብላታ መርስዔ ኀዘን የተዘጋጁ ሲሆኑ (አመኅ) የሚል ምልክት ያለባቸው ኅዳጎች ግን በእኔ በአሰናጁ የተጨመሩ ናቸው። እንዲሁም በ[ ] ዓይነት ቅንፍ ምልክት ውስጥ የተጻፉት በእኔ በአሰናጁ የተጨመሩ ናቸው።

ታሪካዊ ክስተቶች የተፈጸሙባቸውን ዘመናት በተቻለ መጠን በዓመተ ምሕረት ለመግለጽ ሞክሬአለሁ። ይህን ማድረግ ባልተቻለበት ሁኔታ ደግሞ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር (እአአ) ከሚለውን አገላለጽ ይልቅ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ያስታዋወቁትን ቃል ዓ.እ. (ዓመተ እግዚእ፣ Anno Domini) ተጠቅሜአለሁ።

በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙትን የግእዝ ቃላት፣ ዐረፍተ ነገሮች፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችና ቅኔዎች ወደ አማርኛ አስተርጒሜአቸዋለሁ። ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ትርጒም የተጠቀምሁት በብላታ መርስዔ ኀዘን ሊቀ መንበርነት ታርሞ በ1953 ዓ.ም. የታተመውን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱስ የሚባለውን ነው። በግእዝ የተጻፉትን የፍትሐ ነገሥት አንቀጾች ለመተርጐም የተጠቀምሁት በ1962 ዓ. ም. በብላታ መርስዔ ኀዘን ሊቀ መንበርነት ታትሞ የወጣውን የፍትሐ ነገሥት ነጠላ ትርጒም መጽሐፍ ነው።

በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት ካርታዎች እኔ ያሠራኋቸው ሲሆኑ ለካርታዎቹ መሠረት ያደረግሁት የፈረንሳይ፣ የእንግሊዝና የኢጣልያ ቅኝ ግዛት ቢሮዎችና የኢትዮጵያ መንግሥት ያወጧቸውን ካርታዎች ነው።

በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ መጠቍም (የስሞች ፊደላዊ ማውጫ) ይገኛል። መጠቍም በአገራችን መጻሕፍት የተለመደ አልነበረም። ይህን ባህል ለማስተዋወቅ ከሞከሩት አንዱ ብላታ መርስዔ ኀዘን ነበሩ።

አባሪ 1 ውስጥ በመጽሐፉ ውስጥ ስማቸው የተጠቀሰ የንጉሣውያን ቤተሰብን አጭር የሕይወት ታሪክ ይገኛል። አባሪ 2 ደግሞ ስማቸው በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሰ ታላላቅ ሰዎችን የሕይወት ታሪክ የያዘ ነው። አባሪ 1 እና 2 በእኔ በመጽሐፉ አሰናጅ የተጨመሩ ናቸው። አንዳንድ ታሪካቸው አባሪ 2 ውስጥ ሊካተት የሚገባ ታላላቅ ሰዎች አስተማማኝ መረጃ ባለማግኘት የተነሣ ታሪካቸው ሳይካተት እንደቀረ ላሳስብ እወዳለሁ።

በመጨረሻ መጽሐፉ እዚህ ደረጃ እንዲደርስ ለረዱኝ ሁሉ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ካፕቴን ዘለዓለም አንዳርጌ በእርማትም፣ ፎቶግራፎች በማሰባሰብ እንዲሁም የታላላቅ ሰዎች የሕይወት ታሪክ መረጃን በመሰባሰብ፣ በሌላም ባስፈለገኝ ሁሉ ምንጊዜም እርዳታው ያልተለየኝ ትልቅ ባለውለታዬ ነው። አቶ መስፍን ሽንቁጥ አዲስ አበባ ቢሮውን እንዳስፈለገኝ እንድጠቀምበት በማድረግ ከፍተኛ እርዳታ ያደረገልኝ ወዳጄ ነው። የቢሮው አስተዳዳሪ ወይዘሮ ኢየሩሳሌም ይመርም የቅንነት ትብብሯን ለግሳኛለች።

አቶ ፋንታሁን ጥሩነህ ከሚሠራበት ተቋም ከኮንግሬስ ቤተ መጻሕፍት መረጃ በማሰባሰብና በሌላም በብዙ መንገድ ድጋፉን ለግሶኛል፤ በግል ጊዜውም ለሰጠኝ ድጋፍ ባለውለታ ነኝ። ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ለድጋፋቸውና መጽሐፉ ሽፋን ጀርባ ላይ ለጻፉልኝ መልካም ቃል አመሰግናቸዋለሁ። ዶክተር ኃይለ ገብርኤል ዳኜ ፈቃደኛ ሆነው ቀዳሚ ቃሉን ስለጻፉልኝና በየጊዜው ለሰጡኝ ድጋፍ አመሰግናቸዋለሁ።

በኢትዮጵያ የስዊድን ተጠባባቂ አምባሳደር ግሩንድበርግና (Lars Grunderg) በስዊድን ቤተ መንግሥት የመዛግብትና ፎቶ ክፍል ኃላፊ ማዳም ቲና ቢየርክባካ(Tiina Björk-backa) ታሪካዊ ፎተግራፎችን ለማግኘት ላደረጉልኝ ትብብር ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ። ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ፍሎሪዳና በተለይም ዶክተር ዳንኤል ሪቡሲን (Reboussin, Daniel A) የማርቲን ሪከሊን ፎቶ ስብስቦች እንድጠቀም፤ አንግሎ ኢትዮጵያን ሶሳይቲ (Anglo-Ethiopian Society) የአግነስ ዊሎቢ ባንክሮፍት (Agnes Willoughby Bancroft) ፎተግፎችን ለመጠቀም ስለፈቀዱልኝ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው።

አቶ ቀለመ ወርቅ ጀምበር፣ አቶ አበበ ይትባረክና ዶክተር ሥርግው ገላው በግእዝ የተጻፉትን ዐረፍተ ነገሮች ወደ አማርኛ በመተርጐምና በእርማት ረድተውኛል።

ወይዘሮ ሙሉመቤት ፋሪስ፣ ወይዘሮ ማርገሪት ደስታ፣ ወይዘሮ ወይንሸት በሻህ ውረድ፣ ወይዘሮ ሰሎሜ መኰንን፣ ዶ/ር ካሣ ከበደ፣ አቶ ታደለ ይድነቃቸው፣ ሻምበል ሠይፉ ሽንቁጤ መረጃና ፎተግራፍ በማሰባሰብ ረድተውኛል።

አቶ ብርሃኑ ደቦጭ የአርትዖቱን ሥራ በሚገባ አከናውኖ ለመጽሐፉ ይዘት ላደረገው አስተዋጽዖ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስና በተለይ ለዶክተር ያዕቆብ አርሳኖ፣ ለዶክተር ባድማ በላይ እንዲሁ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

መቅደስ ኀበና የመጽሐፉን ሽፋን በመሥራትና ከአጠገቤ ሳትለይ በማናቸውም ጊዜ ድጋፏ ያልተለየኝ ልዩ ባለውለታዬ ናት።

አምኃ መርስዔ ኀዘን

2009 ዓ. ም.

# ቀዳሚ ቃል

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
1922 - 1927
ከመርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ

የዚህ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከፊል ዘመን ታሪክ ደራሲ፤ ብላታ መርስዔ ኀዘን (1891-1971) ይህን ከመጻፋቸው በፊት፣ ሌሎች ከአጼ ምኒልክ ዘመን ጀምሮ በርካታ አንኳር ጽሑፎችን ማበርከታቸው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በሰፊው ተገልጾአል። ጽሑፎቹ ያተኮሩበት ዘመን ኢትዮጵያ ከምዕራቡ ዓለም ጋር ግንኙነት አድርጋ ለመኖርና ለማደግ የምትታገልበት ጊዜ ነበር። ጽሑፎቹም ለወቅቱ ማኅበራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖማዊ እንቅስቃሴ የመረጃ ምንጭ ሆነዋል። ለዚህም ምሁራዊ አስተዋጽዖአቸው በ1936 ዓ.ም. የብላታነት ማዕረግ፣ እንዲሁም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት በ1964 አግኝተዋል።

ብላታ መርስዔ ኀዘን ማናቸው? የዕውቀታቸው ምንጭ ከየት ነው? ለመጻፍ ምን አነሣሣቸው? ብላታ፣ እንደነብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴና ዮፍታሔ ንጉሤ፣ ከጥንታዊቱ ኢትዮጵያ አብነት ትምህርት የተወረሰ፣ ከአዲሲቱ ኢትዮጵያ የተቀሰመ ዕውቀትና አስተያየት ነበራቸው። ጥንታዊውን የኢትዮጵያን ምሁራዊ ዕውቀትና ዘመናዊውን ያገናኙ ባለሙያ ነበሩ። መርስዔ ኀዘን ፊደል የጀመሩት አምስት ዓመት ሳይሞላቸው ነው። ከ1901 እስከ 1911 ዓ.ም. ቅኔና ትርጓሜ መጻሕፍት ተምረው ከዚያም በኋላ ፍትሐ ነገሥት አሂደዋል። ከዚህም ተሻግሮ ለመሄድ ጥረዋል። ዘመናዊውን ትምህርት ለመማር ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ገቡ። ሆኖም፣ መምህራቸው አስወጡአቸው። ያ ጥንታዊው ዕውቀት በምዕራቡ ይበረዛል ብለው ፈርተው ነበርና። እንደነ መልአኩ በያን ውጭ አገር ሄዶ ለመማር ያደረጉት ጥረትም አልተሳካም።

ቀደም ብሎ በ1910 ዓ.ም. በታላቁ ግቢ ውስጥ የግእዝ መጻሕፍት ትርጓሜ እንዲዘጋጅ አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኰንን አንድ ድርጅት አቁመው ሊቃውንት እንደነአለቃ ገብረ መድኅን፣ መምህር ዐወቀ፣ መምህር ወልደ ጊዮርጊስና መምህር ደስታን ዓይነት አሰባስበው ነበር። መርስዔ ኀዘን ገና በወጣትነታቸው፤ ለሊቃውንቱ በጸሐፊነት ተደለደሉ። የማይጽፉት ሊቃውንቱ በቃል የሚያወርዱትን ይጽፉላቸውና የጻፉትን ትርጓሜ ያነቡላቸው ነበር። ከሊቃውንቱ ጋር በመሥራታቸው የግእዝና አማርኛ ዕውቀታቸውን፣ የጽሕፈትና የድርሰት

ችሎታቸውን አዳበረላቸው። ይህም ለድርሰት ሥራ መነሻ ሆኖአቸው ወዲያ ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ሲቋቋም ዝግጅት ውስጥ ተደለደሉ። ብዙም ሳይቆይ በ1917 በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ግእዝና የአማርኛ ለማስተማር ተቀጠሩ።

መርስዔ ኀዘን ከአብነት ትምህርት ቤት የወረሱት አንዱ ባሕርያቸው ታታሪነት ነበርና የዕውቀት ጉጉታቸው በዚህ ሊገታ አልቻለም። የእንግሊዝኛውን መጽሐፍ ቅዱስ ከግእዙ ጋር በማመሳከር፣ እንግሊዝኛ ቋንቋን መማር ጀመሩ። በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ሲያስተምሩ ከበርካታ የውጭ አገር ምሁራን ዕውቀት ቀስመዋል። ትጉህ አንባቢ ነበሩና በማንበብ የዕውቀት አድማሳቸውን ያለማቋረጥ አሰፉት። ከዚህም የተነሣ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ታሪክ ከአለቃ ታዬ ቀጥሎ የመጀመሪያውን አማርኛ ሰዋስው በዘመናዊ ስልት ለመጻፍ በቁ። ይህም በ1935 ዓ.ም. ታትሞ፣ በትምህርት ቤት ያለፉ የሁለት ያህል ትውልድ ኢትዮጵያውያን አማርኛን በሥርዓት እንዲያጠኑት ረድቷቸዋል።

በ1922 ዓ.ም. ጅጅጋ ዘመናዊውን የራስ መኰንን ትምህርት ቤት እንዲመሩ ሆነ። ከዚያም ከእንግሊዝ ሱማሌ ግዛት ጋር የጠረፍ ክለላ ኮሚሲዮን ጸሐፊ ሆነው ወደ ሌላ ሥራ ተወሰዱ። የጣልያንን ወረራ ስም በመቀየርና ቦታ በመለዋወጥ እንደምንም ካመለጡ በኋላ፤ በርካታ አዲስ መሥሪያ ቤቶችን በመምራትና በማቋቋም ሠርተዋል። በየካቲት ወር 1936 ዓ.ም. የታሪክና የቤተ መንግሥት ዜና ማሰናጃ ጽሕፈት ቤት ተሾመው መሥሪያ ቤቱን አቋቋሙ። የአጼ ኃይለ ሥላሴ ፍሬ ከናፍር ዝግጅት ላይ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርገዋል። ምሁራዊ አስተዋጽዖአቸው እየታወቀ ሲመጣ በ1936 ዓ.ም. አቶ መርስዔ ኀዘን የብላታነት ማዕረግ ተሰጣቸው። ብላታ ማለት ብልህ፣ የነገር ብልት ዐዋቂ ሥልጡን ማለት ነው ይላሉ ደስታ ተክለ ወልድ። በርግጥም ብላታ የነገር ብልት ዐዋቂ መሆናቸው እየታወቀ መጥቶ ብዙ መሥሪያ ቤት እንዲመሩ ተደረገ። የሕዝብ ጤና ጥበቃን ሳይቀር በተጠባባቂ ሚኒስትርነት መርተዋል። የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ኮሚቴ፤ የፍትሐ ነገሥት ኮሚሲዮን፤ የወወክማና የትምህርት ሚኒስቴር ቦርድ ውስጥ ተሳትፈዋል። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ከተመሠረተበት ከ1943 ጀምሮ እስከ 1952 ዓ. ም. ድረስ፣ የእንግሊዝ ዩኒቨርሲቲ ተመራቂዎች እነ ልጅ ሚካኤል እምሩ፣ ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ የነበሩበትን ቦርድ በሊቀ መንበርነት ይመሩ ነበር።

ይህ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከፊል የዘመን ታሪክና ሌሎች ጽሑፎቻቸው እንደሚያሳዩት፣ ብላታ ከኢትዮጵያ ታላላቅ ምሁራን እንዲለዩ አድርጎአቸዋል። የኢትዮጵያ ታላላቅ ምሁራን አይጽፉም። ብዙ ብዙ ዕውቀታቸውን ይዘው ሄደዋል። የመጻፍ ጥበብ ለአምልኮ ባዕድ ይመራል ብለው ይቆጠቡ ነበርና። ብላታ ግን በየመሥሪያ ቤቱ እየተሾሙ፣ ሙሉ ጊዜአቸውን በመጻፍ ላይ ሊያውሉ ባይችሉም፣ ብዙ ብዙ ይጽፋሉ። በርካታ ጽሑፎችን ለማቅረብ የቻሉት በተለየ አሠራር ዘዴአቸው ነው። በወቅቱ ያዩትን የሰሙትን ፖለቲካዊ ሆነ ማኅበራዊ ድርጊት ወዲያው ይዘግቡ ነበር። ለምሳሌ አንኮበርን ወይም ኢሉባቦርን ሄደው ከጐበኙ ወዲያው ያዩትን የሰሙትን ይዘግባሉ። የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ ነፃ ለማውጣት በተደረገው ድርድር ግብጽ አገር ዋና ተሳታፊ ነበሩ። ሂደቱን ወዲያው መዘገቡና አስቀመጡ። አሁን ለኅትመት ቀረበ። ከመሥሪያ ቤት መጥተው ሙሉ ጊዜአቸውን

ንባብና ጽሕፈት ላይ ያውላሉ። ለዚህም ሁናቴዎችን በማመቻቸት ትልቅ አስተዋጽዖ ያደረጉት ባለቤታቸው ወይዘሮ እታገኘሁ ባዬ፣ የቤትና የንብረት አስተዳደርን ሙሉ ኃላፊነት ወሰዱላቸው። በጽሕፈት ላይ እንዲያተኩሩ ጸጥታ እንዲያገኙ ትኩረት ይሰጡ ነበር።

ሌላው ብላታን ዜና መዋዕል ከሚጽፉ ሊቃውንት የሚለያቸው፣ በነገሥታቱና በመሳፍንቱ ዜናና ድርጊት ላይ ብቻ አለማተኮራቸው ነው። የጊዜውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ድርጊቶችን አብረው ዘርዝረው ስለሚያካትቱ፣ ጽሑፋቸው የታሪክ ምንጭነት አለው። እነ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ሥነ ጽሑፍ ላይ ሲያተኩሩ፣ ብላታ ግን ከሥነ ጽሑፍ ጋር ታሪክ ዘገባ ላይ ያተኩራሉ።

የብላታ አጻጻፍ ሥልትና አስተሳሰባቸው ከአብነት ምሁራን ይለያቸዋል። አስተሳሰባቸው ምክንያታዊ ነው። የሚጽፉትን እውነተኛነት ለማረጋገጥ ካየሁትና ከሰማሁት በማለት፣ ቦታ፣ ስም፣ ጊዜን በመጥቀስ ያለማጋነንና ያለማዳላት ተጨባጩን ይተርካሉ። በእግዚአብሔር ኃይል ተፈጸመ ብለው እንደተለመደው አያልፉትም፣ ምክንያቱን ይሰጣሉ። የአስተያየት አቅጣጫቸውም ከአብነት ትምህርት ቤት ፈላስፋው ከዘርዓ ያዕቆብ ጋር የሚመሳሰል ርዕዮት አለው። ብላታ ይህን ርዕዮት ያንጸባረቁት ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ባወጡት አርማ ወይም መሪ ቃል ላይ ነው። "ኵሎ አመክሩ ወዘሠናየ አጽንዑ" ሁሉንም መርምሩ፣ መልካሙን እውነቱን አጠንክሩ፣ በሚለው የከፍተኛ ትምህርት የምርምር መሠረትን አመልክተዋል። ዶናልድ ሌቪን የክብር ዶክትሬት ሲቀበሉ የብላታን ምሁራዊነት በመግለጽ ይህን ፍልስፍና በሰፊው አብራርተዋል። ይህ መሪ ቃል፣ በዩኒቨርሲቲው ታላቅ ማኅተም፣ በዲግሪዎችና ዲፕሎማዎች ላይ ይታይ ነበር። አሁንም ከራስ መኰንን አዳራሽ መግቢያ ላይ ይነበባል። በዚህም በኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ላይ አሻራቸውን ጥለዋል።

ይህ ሁሉ አገልግሎታቸው ተደምሮ ብላታ መርስዔ ኀዘን በ1964 የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት ድርጅት የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ተሸላሚ ሆኑ። ድርጅቱም አድናቆቱን እንደሚከተለው ገልጾአል።

> የኢትዮጵያ ነፃነት ከተመለሰ ዠምሮ በልዩ ልዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ያገለግላሉ። በተጨማሪም በታሪክና በቤተ መንግሥት ዜና ማዘጋጃ በትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ቦርድ በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ዝግጅት ውስጥ ትጉህና ጥኑ አባል ሆነው መሥራታቸው ለአማርኛ ቋንቋ መስፋፋት ላበረከቱት አገልግሎት በቂ ምስክር ነው። በተለይም የአማርኛን ሰዋስው በዘመኑ አውሮጳዊ አቀራረብ ተመሳሳዩን ቃል አሳክተው አዋጁን አስማምተው የደረሱት መጽሐፍ ሦስት የተማሪዎች ትውልድ የተቀባበለው ሲሆን እነሆ እስከ ዛሬ በ1ኛ በ2ኛ ደረጃ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ማስተማሪያ ነው። በሐቅና በጥንቃቄ የተዘጋጀ የዘመናቸው ታሪክና የሕይወታቸው ትዝታ በተጣራ አማርኛ ተጽፈው ይገኛሉ። ስለዚህ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት ድርጅት በተርጓሚነት በአዘጋጂነትና ይልቁንም በደራሲነት ቍጥራቸው ከ36 በላይ የሆኑ መጻሕፍት በእርሳቸው አማካይነት የታተመ መሆኑ ለታወቀላቸውና የአማርኛን ቋንቋ ከዘመናዊ ከኪነታዊ አነጋገር በማስማማት ከሁሉም የተሻለ አገልግሎት ላበረከቱ ለክቡር ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ የ1964 ዓም የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ሽልማት የወርቅ ኒሻንና የምስክር ወረቀት ከ10 ሺህ የኢት ብር ጋር እንዲሰጣቸው በሙሉ ድምፅ ኰሚቴው ወስኖአል።

ብላታ ከዚህ በኋላም፣ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ዘመን ሙሉ ታሪክ ለመጻፍ ተነሥተው፣ ከንግሣቸው እስከ ጣልያን ወረራ ያለውን ጻፉ። ሙሉ ታሪኩን ግን ለመጻፍ እክል ገጠማቸው። በ1965 ዓ. ም. ባለቤታቸው፣ ረዳታቸው ድንገት በመኪና አደጋ ዐረፉባቸው። የኑሮ ሁኔታዎች እምብዛም አልተመቻቹላቸውም። ወዲያው ደግሞ በ1966 ዓ. ም. አብዮቱ ሲፈነዳ ሁናቴዎች ተመሰቃቀሉ። ብዙ የሥራ ጓደኞቻቸው እነ ደጃች ከፍሌ እርገቱ፣ አቶ አካለ ወርቅ ሀብተ ወልድ የመሰሉት እየተለቀሙ ሲታሰሩና ሲፈጁ መጨነቃቸው አልቀረም። በከፍተኛ የሥልጣን ቦታም ቢሠሩም፣ በሳቸው መጽሐፍ የተማረ ካድሬ ሆነ ወታደር በትሩን ወደ እርሳቸው ሊሠነዝር አልደፈረም። ሆኖም፣ እንዳቀዱት ሙሉውን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ዘመን ታሪክ አጠናቀው ለመጻፍ ሞከረው፣ ሳያጠናቅቁ በ1971 ዓ. ም. ሕይወታቸው አለፈ።

ይህ የመጨረሻ የልፋታቸው ውጤት፣ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከፊል የዘመን ታሪክ በልጃቸው በአቶ አምኃ አማካኝነት ታትሞ መቅረቡ፣ ለአዲሱ ትውልድ አንባቢዎችና ተመራማሪዎች ጠቀሜታው የጎላ ነው።

ኃይለ ገብርኤል ዳኜ
2009 ዓ. ም.

# ምዕራፍ 1

## 1922 ዓመተ ምሕረት

*ስለ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልደትና አስተዳደግ - አገረ ገዥ ስለ መሆናቸው - የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ስለ መሆናቸው - በንጉሥ ነገሥት ዙፋን ስለ መቀመጣቸው የዙፋን መውረስ አዋጅ እንደ ተነገረ - ለበጌምድር ሕዝብ የተነገረ አዋጅ - ራሶች ወደ አዲስ አበባ ስለ መጠራታቸው - የሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ከእሳት ቃጠሎ እንደ ዳነ - ስለ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ የአርባ ዕለት ተዝካር - ስለ ዘማች መመለስ - ስለ ሹመት - ሐዘንን ለመግለጽ ከየአውራጃው ስለመጡ መኳንንት - ለሕዝብ የተነገሩ አዋጆች - ወታደሮችን ስለ ማሠልጠን ስለ አውሮፕላን ነጂዎች - ስለ ጦር መኰንኖች - ስለ ሹም ሽር - የመኪና መንገዶች ሥራ በወሰን ላይ ስለ ደረሰ ግጭት - ስለ ታላላቅ ሰዎች ሞት*

### ስለ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልደትና አስተዳደግ

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የቀድሞ ስማቸው ተፈሪ መኰንን ሐምሌ 16 ቀን 1884 ዓ.ም. ሐረር ኤጀርሳ ጎሮ በተባለ ስፍራ ከራስ መኰንንና ከወይዘሮ የሺእመቤት ተወለዱ። ራስ መኰንን የጎባው የደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ወልደ መለኮትና የወይዘሮ ተናኘ ወርቅ ሣህለ ሥላሴ ልጅ ናቸው። ወይዘሮ የሺእመቤትም የወሎ ተወላጅ የፊታውራሪ አልዩ ጋምጮና የወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ ልጅ ናቸው።

ልጅ ተፈሪ መኰንን ገና ሕፃን ሳሉ እናታቸው ወይዘሮ የሺእመቤት መጋቢት 6 ቀን 1886 ዓ.ም. ዐርፈው ሐረር በጥምቀተ ባሕር ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ።

ልጅ ተፈሪ መኰንን በሕፃንነታቸው ዘመን ልዩ አስተማሪ ተደርጎላቸው የግእዝና የአማርኛ ትምህርት እየተማሩ አደጉ።

አሥር ዓመት በሆናቸው ጊዜም የሚሲዮናዊው የአባ እንድርያስ ደቀ መዝሙር አባ ሳሙኤል ወልደ ካህን[1] የሙሉ ሰዓት አስተማሪ ሆኖ ስለተቀጠረላቸው ከሌሎች የመኳንንት ልጆች ጋር ትምህርቱን በትጋት ይማሩ ጀመር። በተጨማሪም ለሕክምና ሥራ ተቀጥሮ ከፈረንሳዊ ቅኝ ግዛት ከጉዋደሉፕ የመጣው ዶክተር ቪታሊየን[2] ከሥራ በሚተርፈው ሰዓቱ የፈረንሳዊ ቋንቋ ያስተምራቸው ጀመር።

---

[1] የካቶሊክ ካህን። ግንቦት 30 ቀን 1907 ዓ.ም. ደጃዝማች ተፈሪ በአለማያ ሐይቅ ላይ በጀልባ ሽርሽር ሲያደርጉ በደረሰው የስጥመት አደጋ ከሞቱት አንዱ ናቸው። ምንጭ - መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ *የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ*፣ ገጽ 129 (አሙኅ)

[2] ዶክተር ቪታሊየን (1860-1931 ዓ. ም.) የፈረንሳይ ቅኝ አገር የነበረችው የጉዋደሉፕ ተወላጅ ጥቁር ሰው ናቸው። ከ1894 እስከ 1896 ዓ. ም. ድረስ የሐረር ሆስፒታል ሐኪም ነበሩ። ዳግማዊ ምኒልክ በታመሙ ጊዜ ከሐኪሞቹ አንዱ እሳቸው ነበሩ። ዳግማዊ ምኒልክ የምድር ባቡርን ኮንሴሽን ሰጥተዋቸው ነበር። በ1919 ዓ. እ. *Pour l'Indépendence de l'Ethiopie* የተባለ መጽሐፍ ጽፈው ነበር። ምንጭ - Pankhurst, Dr. R, *The Franco-Ethiopian Railway and Its History* (አሙኅ)



ተፈሪ በ8 ዓመት ዕድሜ



ከአባታቸው ከራስ መኰንን ጋር



ተፈሪ በለው፣ ተፈሪ መኰንን፣ ብሩ፣ እምሩ ኃ/ሥላሴ



ተፈሪ ለምድ ለብሰው

ተፈሪ በልጅነት ዕድሜ

## አገረ ገዥ ስለ መሆናቸው

ልጅ ተፈሪ መኰንን በተወለዱ በ13ኛ ዓመት በጥቅምት 21 ቀን 1898 ዓ.ም. አባታቸው ልዑል ራስ መኰንን የደጃዝማችነት ማዕረግ ሰጥተው ጋራ ሙለታ የሚባለውን አውራጃ ሾሟቸው። ግዛቱም በሞግዚትና በእንደራሴ እየተዳደረ እርሳቸው ትምህርታቸውን ቀጠሉ።

ልዑል ራስ መኰንን[3] በ1898 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ ለመውጣት በጥር 4 ቀን ከሐረር ተነሥተው ጕዞ ጀመሩ። በመንገድ ላይ ስለ ታመሙ ወደ ቁልቢ ተመልሰው ታመው ሰነበቱና መጋቢት 13 ቀን እዚያው ቁልቢ ላይ ዐረፉ። ሬሣቸውም ወደ ዋና ከተማቸው ወደ ሐረር ተወስዶ በጥምቀተ ባሕር ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበረ።

የልዑል ራስ መኰንን ሞት አዲስ አበባ ላይ በተሰማ ጊዜ በዳግማዊ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ትልቅ ሐዘን ሆነ። ዳግማዊ ምኒልክ በብዙ አዝነው ነበርና የልዑል ራስ መኰንንን የአርባ ተዝካር አዲስ አበባ ላይ ለማውጣትና ለማስለቀስ ስለፈለጉ የሐረር መኳንንት ከደጃዝማች ተፈሪ ጋራ በቶሎ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ትእዛዝ አሳለፉ። ስለዚህም መኳንንቱ ከደጃዝማች ተፈሪ ጋራ ሚያዝያ 3 ቀን ከሐረር ተነሥተው ሚያዝያ 19 ቀን አዲስ አበባ ደረሱ። የልቅሶውም ሥነ ሥርዓት በፍልውሐ ሜዳ ላይ ድንኳን ተተክሎ ዳግማዊ ምኒልክ ባሉበትና ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት ተፈጸመ።

የአርባው ተዝካር ሚያዝያ 22 ቀን ሰኞ ነበርና ፍትሐቱና ተዝካሩ እጅግ ከፍ ባለ ሥነ ሥርዓት ተከናወነ። ለነዳያንም ብዙ ምጽዋት ተመጸወተ። በማግሥቱ በሰፊ ሜዳ ላይ ትልልቅ ድንኳን ተተክሎ የአርባው ልቅሶ ተለቀሰ። አልቃሾችም የግጥም ቃል እየተናገሩ ያስለቅሱ ነበር።

ከዚህ በኋላ በግንቦት 2 ቀን ዳግማዊ ምኒልክ የሐረርን ግዛት ለትልቁ የራስ መኰንን ልጅ ለደጃዝማች ይልማ[4] ሰጥተው በነጋሪት ሾሟቸው። ለደጃዝማች ተፈሪም የሰላሌን ግዛት ሰጥተው በነጋሪት ሾሟቸውና ግዛቱ በእንደራሴ እየተዳደረ ደጃዝማች ተፈሪ በአዲስ አበባ ሆነው አዲስ በተከፈተው በዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት ትምህርታቸውን ይቀጥሉ ጀመር። ሰላሌን በተሾሙ በዓመቱም እንደገና ባሌን ተሾመው በእንደራሴ ገዝተውታል።

ደጃዝማች ይልማ መኰንን ሐረርን ተሾመው አንድ ዓመት ከአምስት ወር ከቆዩ በኋላ በመስከረም 29 ቀን 1900 ዓ.ም. በ34 ዓመት ዕድሜያቸው ዐርፈው ሐረር በጥምቀተ ባሕር ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ።

ከዚህም በኋላ ዳግማዊ ምኒልክ በመጋቢት 27 ቀን 1900 ዓ.ም. እሑድ ቀን ሹም ሽር አድርገው የሲዳሞን ገዥ ደጃዝማች ባልቻን በሐረርና በባሌ ሾሟቸው። የሲዳሞንም ግዛት ከሁለት አካፍለው በግማሹ ደጃዝማች ናደው አባ ወሎን በግማሹም ደጃዝማች ተፈሪ መኰንንን ሾሟቸው።

---

3 አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 1 ገጽ 212 ይመልከቱ። (አመነ)

4 አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 1 ገጽ 217 ይመልከቱ። (አመነ)

ደጃዝማች ተፈሪ መኰንን ወደ ሲዳሞ ሄደው አንድ ዓመት ያህል አገሩን አስተዳደሩ። ከዚያም በኋላ የአጼ ምኒልክን መታመም ስለሰሙ ለጥየቃ እንዲመጡ አስፈቅደው በ1901 ዓ.ም. በሚያዝያ ወር ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ።

ደጃዝማች ባልቻ[5] ሐረርን ሁለት ዓመት ያህል እንደገዙ ሐረርን ለቀው በ1902 ዓ.ም. በጥር ወር ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ። በዚህ ጊዜ ደጃዝማች ተፈሪ መኰንን መጋቢት 24 ቀን 1902 ዓ.ም. የሐረርን ግዛት በነጋሪት ተሾሙ። ደጃዝማች ባልቻም የቀድሞ ግዛታቸው ተሰጥቷቸው ወደ ሲዳሞ ተመለሱ።



*ተፈሪ ዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት ተማሪ ሆነው*

ደጃዝማች ተፈሪ መኰንን ወደ ሐረር ወርደው አገሩን በሚገባ ያስተዳድሩ ጀመር። አቤቶ ኢያሱም[6] የታላቅ እኅታቸውን የወይዘሮ ስኂንን ልጅ ወይዘሮ መነን አስፋውን በ1903 ዓ.ም. በሐምሌ ወር ዳሩላቸው። ከዚህ በኋላ እስከ ሰገሌ ዘመቻ ድረስ ያለው የእርሳቸው ታሪክ በአቤቶ ኢያሱ የዘመን ታሪክ[7] ላይ ይገኛልና ከዚያ መመልከት ነው።

## የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ስለ መሆናቸው

በአዲስ አበባ ያሉ መኳንንት አዲስ መንግሥት ለማቆም መክረው በመስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም. አቤቶ ኢያሱን ከመንግሥት ባስወጡ ጊዜ የዳግማዊ ምኒልክን ልጅ ወይዘሮ ዘውዲቱን ንግሥተ ነገሥታት አድርገው በኢትዮጵያ ዙፋን አስቀመጧቸው። ደጃዝማች ተፈሪንም ራስ ብለው የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ አደረጓቸው።

---

5 አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 227 ይመልከቱ። (አመኀ)

6 አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 1 ገጽ 214 ይመልከቱ። (አመኀ)

7 መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ *የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ፣ የአቤቶ ኢያሱ ዘመነ መንግሥት ታሪክ።* (አመኀ)

እንግዲህ በአልጋ ወራሽነትና በእንደራሴነት በንጉሥነትም የፈጸሙት ሥራ ሁሉ ስለ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመን በተጻፈው ታሪክ[8] ላይ ይገኛልና በዚያ መመልከት ነው።



ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ

## በንጉሠ ነገሥት ዙፋን ስለ መቀመጣቸው

ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ መጋቢት 24 ቀን 1922 ዓ.ም. በ8 ሰዓት ከዐረፉ በኋላ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ዙፋኑን ወረሱ። በማግሥቱም መጋቢት 25 ቀን ኀሙስ በሦስት ሰዓት ጳጳሳትና ሚኒስትሮች፣ መኳንንትና የጦር አለቆች ሁሉ ወደ ቤተ መንግሥት ተጠርተው መጥተው በትልቁ አዳራሽ ውስጥ ተሰበሰቡ። አራት ሰዓት ሲሆን ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ወደ ትልቁ አዳራሽ ገብተው በመንበረ ዳዊት ተቀመጡ። የመንግሥት ስማቸውም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተብሎ በክርስትና ስማቸው መሰየሙ ስለተነገረ ሁሉም «ይበጅ ያድርግ» እያለ ደስታውን በጭብጨባ ገለጠ።

ሥርዋጽ[9]፤ የኢትዮጵያ ነገሥታት ወደ ዙፋን በሚወጡበት ጊዜ ስመ መንግሥታቸው በዓለም ስም ወይም በክርስትና ስም መጠራቱ የተለመደ ነው። የዓለም ስም የሚባለው ሕዝበናኝ፣ በድልናኝ፣ በካፋ፣ ምኒልክ፣ ዘውዲቱ እንደ ማለት ነው። የክርስትና ስም የሚባለውም ኃይለ መለኮት፣ ተክለ ጊዮርጊስ፣ ኃይለ ሥላሴ እንደ ማለት ነው። የሸዋ ንጉሥ ኃይለ መለኮት የቀድሞ ስማቸው ደጃዝማች በሻህ ውረድ ሆኖ ሳለ በነገሡ ጊዜ በክርስትና ስማቸው ኃይለ መለኮት ተብሏል። አጼ ተክለ ጊዮርጊስ የቀድሞ ስማቸው ደጃዝማች ጉበዜ ገብረ መድኅን ሆኖ ሳለ በነገሡ ጊዜ በክርስትና ስማቸው ተክለ ጊዮርጊስ

[8] መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ። (አሙን)

[9] እንደ ማስረጃ ሆኖ በነገር መካከል የሚገባ። (ብሙን)

ተብለው እንደተጠሩ ሁሉ በዚህም ዘመን ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ኃይለ ሥላሴ ተብለው በክርስትና ስማቸው ተጠርተዋል።

የኢትዮጵያ ነገሥታት በስማቸው ላይ የሞገስ ወይም የፈረስ ስም እየጨመሩ በወደዱት ስም ይጠሩበታል። የሞገስ ስም የሚባለው በጐንደር ነገሥታት ዘመን መላክ ሰገድ፣ አድያም ሰገድ ሲባል የነበረውን የመሰለ ነው። የፈረስ ስም የሚባለው አባ በዝብዝ፣ አባ ዳኘው፣ አባ ጤና እንደ ማለት ያለ ነው። የግርማዊነታቸውም የፈረስ ስም አባ ጠቅል ነው። የሞገስ ስም ነገሥታት ብቻ የሚጠሩበት ሲሆን የፈረስ ስም ግን ለዜጎችም የተፈቀደ ስለሆነ ሌላ ሁሉ ይጠራበታል።

## የዙፋን መውረስ አዋጅ እንደ ተነገረ

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በመንበረ ዳዊት ከተቀመጡ በኋላ የጽሕፈት ሚኒስትሩና ሊጋባው ወደ አዋጅ መንገሪያው አደባባይ ሄደው የግርማዊነታቸውን አዋጅ በነጋሪት አሳወጁ። ቃሉም ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

አዋጅ

ንጉሥ ተፈሪ መኰንን

ሳናስበው ፈጣሪችን በሕዝቡ አድሮ መርጦን እንዳናገረው አዋጅ የናትና የልጅ ቃል ኪዳናችን ሳይፈርስ በሱ ሕግና ትእዛዝ ሰው ሆኖ ከሞት የሚቀር የለምና በጥቂት ቀን ሕመም ስለ አረፉና ስለተቀዳደምን የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ማለፍ ለእኔና ለመላ ኢትዮጵያ ኃዘናችን ቢሆን የሕዝቡ እረኛ ንጉሥ ሲሞት ንጉሥ መተካቱ የቆየ ልማድ ስለሆነ እኔም በታጨሁበት መንበረ ዳዊት ሆኜ በእግዚአብሔር ቸርነት እጠብቅሃለሁና ነጋዴም ነግድ ገበሬም እረስ ከአባቶቼ ሲያያዝ በመጣው ሕግና ደምብ አሳድርሃለሁ።

መጋቢት 28 ቀን 1922 ዓ.ም.

ከዚህ በኋላ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ከትልቁ አዳራሽ ወጥተው ወደ እልፍኝ አዳራሽ ገብተው በዙፋናቸው ተቀመጡ። ወዲያው ብፁዓን ጳጳሳት፣ ክቡራን ሚኒስትሮችና መኳንንት ተጠርተው ገብተው ከፊታቸው ሲቆሙ ንኡስ አነ አምኦኃውየ ወወሬዛ በቤተ አቡየ[10] የሚለውን ንጉሥ ዳዊት የተናገረውን ቃል በግእዝ አነበቡ። የምዕራብ ኢትዮጵያ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አብርሃምም[11] በአማርኛ ተርጒመው ለሕዝቡ አሰሙና አቡነ ዘበሰማያት ሰጥተው አሳረጉ። በዚህ ጊዜ መኳንንቱ «ሺህ ዓመት ያንግሥዎ፣ ይበጅ ያድርግ» እያሉና ለንጉሠ ነገሥቱ መልካም ምኞታቸውን እየገለጹ እጅ ነሥተው ተመለሱ።

ከዚህ ቀን በኋላ በቤተ መንግሥት ምክር ተመክሮና እርሳቸውም ፈቅደው የንጉሠ ነገሥቱ የዘውድ በዓል በተከታዩ ዓመት በጥቅምት 23 ቀን እንዲሆን ስለተወሰነ ለበዓሉ የሚያስፈልገው ድርጅት ሲዘጋጅ ከረመ። የኢትዮጵያ ወዳጆች ለሆኑ መንግሥታትም የክብር ጥሪ ተላከላቸው።

[10] ከወንድሞቼ ትንሽ በአባቴ ቤትም ጎልማሳ ነኝ። መዝ. ም. 150 ቀጥሎ ስለራሱ ከተናገረው። (አመኀ)

[11] አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 233 ይመልከቱ። (አመኀ)

## ለበጌምድር ሕዝብ የተነገረ አዋጅ

ከቋና ውጊያ[12] በኋላ ደጃዝማች ብሩ ወልደ ገብርኤል አገሩን እንዲያስተዳድሩና ጸጥታውን እንዲያስከብሩ ታዘው በደብረ ታቦር ከተማ ይገኙ ነበር። ከቋና ዘመቻ የተመለሰውም የበጌምድር ሕዝብ አምፆ እርስ በርሱ ይቃማ ነበርና ደጃዝማች ብሩ ወልደ ገብርኤል ይህንኑ በሚያዝያ 3 ቀን ወደ አዲስ አበባ በስልክ አስታወቁ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በሚያዝያ 4 ቀን የበጌምድርን ግዛት ለልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ[13] ሰጥተው በአዋጅ ከሾሙ በኋላ ለበጌምድር ሕዝብ የሚነገር የአዋጅ ቃል ከደብዳቤ ጋር ለደጃዝማች ብሩ አስተላለፉላቸው። ደብዳቤውና አዋጁ ከዚህ ያለው ነው።

ሞዓ አንበሳ

ይድረስ ከደጃዝማች ብሩ (ደብረ ታቦር)

ሚያዝያ 3 ቀን የላከኸውን የስልክ ቃል አየሁት። ከራስ ጉግሣ ወሌ ጋር ዘምቶ ሄዶ የተመለሰው በያገር ቤቱ ተሰራጭቶ እርስ በርሱ ይቃማል ያልከውን ይኸውና ያዋጅ ቃል ልኬልሃለሁና እዚያው እናንተ ዘንድ ደብረ ታቦር ላይ በሌላ በሌላውም ከተማ ሁሉ በየስፍራው እንድታስነግር ይሁን።

አዋጅ

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ።

ለራስ ካሣ ከርብ በላይ በጌምድርን ሳይንትን በእራት[14] ከርብ በታች በቆራጭነት[15] ሰጥቻለሁና የበጌምድር ሰው ራስ ጉግሣ ወሌ ቀድሞ ወደ የጁ ያዛውሩኝ ብለው ቢለምኑ የአዝመራ ጊዜ ነውና የበጌምድርን ዘማች ሳያስነሡ ከርብ በላይ ያለውን ባለትዳርና አሽከሮችዎን ይዘው መጥተው በፊት የከዳውን ኦሮሞ ይውጉ ብለን ለይተን ብናዛቸው እናንተንም አለፈቃዳችን አስነሥተው በክረምት አጕላልተው። በመጨረሻውም ያልተሠራ ውሸት ነገር አስወርተው ከዚህ ሁሉ ጥፋት የደረስከው በናንተ አለማወቅና በራስ ጉግሣ ተንኰል መሆኑን መርምሬ እውነቱን ስላገኘሁት ደም መፍሰሱ አልቀረምና የሚቀጣውን ገላህን ምሬሃለሁና። መንግሥት የወጋህ ጥፋተኛውም ያልወጋኽም ፈቃደኛ ከሰጠሁህ ዳኛ ድረስ ደብረ ታቦር ገብተህ ላግኝህ። እስከ ዳግም ትንሣኤ ገብተህ ፈቃደኛነትህን ያላስታወቅህ ግን ከአጥፊ ትቆጠራለህ። ሚያዝያ 4 ቀን 1922 ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ተጻፈ።

ይህ የአዋጅ ቃል በጌምድር ላይ በተሰማ ጊዜ ያገሩ ጸጥታ በ.ቶሎ ሊረጋጋ ቻለ። ልዑል ራስ ካሣ በዳኝነት ዕውቀት የተመሰገኑ ናቸውና መልካም ዳኛ ተሾሙልን እያለ ሕዝቡ ተስፋ አደረገ።

እንዲሁ ደግሞ በአዲስ አበባ ይኖሩ የነበሩት ጐንደሬው ብላታ ተስፋዬ ጐበዜ የጐንደር ከንቲባ ተብለው ተሾሙ።

---


12 መጋቢት 22 ቀን 1922 ዓ. ም. በራስ ጉግሣ ወሌና በጦር ሚኒስትሩ በደጃዝማች ሙሉጌታ መካከል የተደረገ ጦርነት። መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ፣ ገጽ 395 ይመልከቱ። (አመኀ)

13 አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 236 ይመልከቱ። (አመኀ)

14 ገዥነት። (አመኀ)

15 ቆራጭነት ማለት የበላይነት ማለት ነው። (አመኀ)

ከአገሩም መኳንንት በደጅ ጥናትና በመጉላላት አዲስ አበባ ላይ የነበሩት እነ ፊታውራሪ ካሣ መሸሻ እነ ደጃች ኃይሉ ንጉሤ፣ እነ ደጃች መልኬ፣ እነ ደጃች ተስፉ ከርብ በታች ባለው አገር የግዛት ሹመት ስለተሰጣቸው ለአባታቸው አገር በመብቃታቸው ደስ እያላቸው ሄዱ። በቀድሞ ጊዜ ራስ ጉግሣ ወሌ[16] የነቀሏቸውም ሰዎች ፊታውራሪ ይመር ጐሹ፣ ፊታውራሪ ኃይሉ ወንዴ፣ ፊታውራሪ አስፋው የስማዳው፣ ፊታውራሪ ብጡል የደጃች ተሰማ ውቤ[17] ልጅ ትዳርና ሹመት እያገኙ በያገራቸው እንዲገቡ ተደረገ።



ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ

ከርብ በላይ ከርብ በታች ስለሚባለው የሀገር ክፍል ጥቂት መግለጫ እሰጣለሁ። ርብ በበጌምድር ውስጥ ከአንድ ተራራ ሥር መንጭቶ እየፈሰሰ ወደ ጣና ባሕር የሚገባ ወንዝ ነው። እርሱም የሀገር ክፍል መለያ ሆኖ ከርብ በላይ ከርብ በታች እየተባለ ይነገርበታል። ከርብ በላይ የሚባለው ወደ በሽሎ በኩል ያለው አገር ሲሆን ከርብ በታች የሚባለውም ወደ መተማ በኩል የሚገኘው አገር ነው። ስለዚህም አንዳንድ ጊዜ ከርብ እስከ በሽሎ ወይም ከርብ እስከ መተማ እየተባለ ይነገራል። አሁን ልዑል ራስ ካሣ በቆራጭነት የተሾሙትም አገር በመተማ በኩል ያለውን ነው።

## ራሶች ወደ አዲስ አበባ ስለ መጠራታቸው

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በንጉሠ ነገሥትነት ዙፋን በተቀመጡበት ሰዓት በአዲስ አበባ ከተማ የነበሩት ራሶች ልዑል ራስ ካሣና ራስ ከበደ መንገሻ[18] ሲሆኑ የቀሩት

16 አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 242 ይመልከቱ። (አመነ)

17 ስለ ደጃዝማች ተሰማ ውቤ በዳግማዊ ምኒልክ የዘመን ታሪክ፣ ገጽ 67 እይ። [መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ] (ብመነ)

18 አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 235 ይመልከቱ። (አመነ)

ሦስት ራሶች፣ ልዑል ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት፣ ልዑል ራስ ሥዩም መንገሻና ልዑል ራስ ጉግሣ አርአያ በየግዛት አገራቸው ነበሩ። እነርሱም በቶሎ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ በግርማዊነታቸው ስለተጠሩ ጥሪውን በአክብሮት ተቀብለው በሚያዝያ ወር አዲስ አበባ ደርሰው መጀመሪያ ስለ ንግሥት ሞት እያለቀሱ ወደ ቤተ መንግሥት ገብተው ሐዘናቸውን ገለጹ። ቀጥሎም ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፊት ቀርበው «እንኳን ለንጉሠ ነገሥት ዙፋን ያበቃዎ» እያሉ እጅ እየነሡ ታዛዥነታቸውን አረጋገጡ።

የጐጃም ገዥ ራስ ኃይሉ[19] ባለፈው በቋና ዘመቻ ጊዜ ከራስ ጉግሣ ወሌ ጋራ የምሥጢር ስምምነት አድርገዋል በመባል ስለተጠረጠሩ ምናልባት ያምፁ ይሆናል ተብሎ ተወርቶ ነበር። አሁን ግን እንደ ወሬው ሳይሆን ጥሪውን ተቀብለው በቶሎ ስለ መጡና በሚያዝያ 14 ቀን አዲስ አበባ በሰላም ስለገቡ ደስታ ሆነ።

የትግሬም ገዥዎች ራስ ሥዩም መንገሻና[20] ራስ ጉግሣ[21] ከምጽዋ ወደ ጅቡቲ በመርከብ ተጓዘው ሚያዝያ 24 ቀን በባቡር አዲስ አበባ ገቡ። በዚህ ጊዜ ከመኳንንት ደጃዝማች ይገዙ በሀብቴ፣ ፊታውራሪ ዓምዴ፣ ከንቲባ ነሲቡ ዛማኔል፣ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴና[22] ሌሎችም ታላላቅ ሹማምንት በባቡር ማረፊያ ጠብቀው ተቀበሏቸው። ወደ ትግሬ ተልኮ ሄዶ የነበረውም ቀኛዝማች ታደሰ ገነሜ በዚሁ ቀን ከሁለቱ ራሶች ጋር አብሮ ገባ።

## የሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ከእሳት ቃጠሎ እንደ ዳነ

በዚህ ዘመን ፋሲካ ሚያዝያ 12 ቀን ውሎ ነበር። በዚህ ሌሊት በአዲስ አበባ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የእሳት አደጋ ደርሶ መንበሩ ከሥር እስከ ጫፍ ተቃጠለ። እሳቱ በብዙ ሰዎች እርዳታ ስለጠፋ ቤተ ክርስቲያኑ በጭራሽ ከመቃጠል ዳነ። የነገሩም ሁናቴ እንደሚከተለው ነው።

የትንሣኤ በዓል በተከበረበት በዚያ ሌሊት ከማታው ከአራት ሰዓት ጀምሮ ማኅሌት ተቆሞ ሕዝብ በዓሉን ሲያከብር አደረ። በዚህ ጊዜ በመንበሩ በአራቱም ማዕዘኖች ላይ የሻማ መብራት ተተክሎ ይበራ ነበር። ከሌሊቱ በስምንት ሰዓት ተኵል ቅዳሴ ተፈጽሞ ሕዝቡ ተሰናብቶ ወደየቤቱ ተመለሰ።

ፍሬ ሰሞነኛውም ዲያቆን የሻማውን መብራት ሳያጠፋ ረስቶ ቤተ ክርስቲያኑን ዘግቶ ወደ ቤቱ ሄደ። የሻማውም መብራት ሲበራ ቆይቶ ባለቀ ጊዜ ከመንበሩ እንጨት ላይ ስለደረሰ እንጨቱ በእሳት ተያይዞ እስኪነጋ ድረስ ሲቃጠል አደረ።

ከጥዋት በሁለት ሰዓት ቤተ ክርስቲያን ለመሳለም የሄዱ ሰዎች በጣሪያው ላይ ብዙ ጢስ ሲወጣና ሲጨስ አዩ። በሩን አስከፍተው ቢገቡም የእሳት አደጋ መሆኑን ስለተረዱ እየተጯጯሁ ለሌላው ሁሉ አስታወቁ። ወደ ግቢም መላከተኛ ተልኮ የቤተ መንግሥት

[19] አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 230 ይመልከቱ። (አመኀ)
[20] አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 225 ይመልከቱ። (አመኀ)
[21] አጭር የሕይወት ታሪክ ገጽ 147 ይመልከቱ። (አመኀ)
[22] አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 231 ይመልከቱ። (አመኀ)

ሹማምንት ወሬውን ስለሰሙ ቢትወደድ ወልደ ገብርኤል በሻህ፣ ሊጋባ ወዳጄ ውቤና ፊታውራሪ ደቻሳ ከነጭፍራቸው እየሮጡ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሄደው እሳቱን በቶሎ አጠፉት። መንበሩ በእሳት የተንዳ ሲሆን ቤተ ክርስቲያኑ በእግዚአብሔር ቸርነት ሳይቃጠል ቀረ። ታቦቱም አልተቃጠለም። መንበሩ ሲቃጠል ታቦት ሳይቃጠል ስለቀረበት ምክንያት በዘመኑ የተሰጠ መግለጫ የለም። እኔ ግን ምናልባት ቀሳውስት ታቦቱን ከመንበር አውጥተው በሌላ ስፍራ ቢያስቀመጡት ይሆናል ብዬ አስባለሁ። ወይም በተአምራት ተርፎ እንደሆነ ሁለተኛ ምክንያት ይሆናል።

## ስለ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ የአርባ ዕለት ተዝካር

የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ የአርባ ተዝካር ግንቦት 3 ቀን እሑድ 1922 ዓ.ም. ነበረ። ለፍትሐቱ ጸሎትና ለተዝካሩ የተጠሩት የ21 አድባራትና ገዳማት ካህናት ግንቦት 2 ቀን ቅዳሜ ከያሉበት መጥተው በመታሰቢያ በዓታ ቤተ ክርስቲያን ዋዜማ ቆመው አመሹ። ሌሊቱንም ማኅሌትና ሳታት በየክፍሉ ቆመው የፍትሐት ጸሎት ሲያደርሱ አድረው ጧት ቅዳሴ ተጀመረ። ከቅዳሴም በኋላ ሊቀ ካህናቱ መልአከ ገነት ወልደ ሐና[23] ካህናቱን የተዝካር ድግስ ወደ ተዘጋጀበት ዳስ ወስደው ግብር አስገቧቸው።

የዳሱና የግብሩ ሥርዓት እንደሚከተለው ነው። በትልቁ አዳራሽ ፊት በሜዳው ላይ ሰፊ ዳስ ተሠራ። በውስጡ የግብር ማብሊያው ቦታ ተደልድሎ አምሮ ምንጣፍ ተነጠፈበት። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የሚቀመጡበትም ዙፋን በዳሱ መካከል ከፍ ካለ ቦታ ላይ ተዘጋጀ።

አምስት ሰዓት ሲሆን ግርማዊነታቸው ከዳሱ ገብተው በዙፋን ላይ ተቀመጡ። ከዙፋን በስተቀኝ አምስቱ ብፁዓን ጳጳሳት አቡነ ሳዊሮስ[24]፣ አቡነ አብርሃም፣ አቡነ ጴጥሮስ[25]፣ አቡነ ይስሐቅ[26]፣ አቡነ ሚካኤል[27] በወምበር ተቀመጡ። በስተግራም ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ፣ ልዑል ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት፣ ልዑል ራስ ሥዩም መንገሻ፣ ልዑል ራስ ጉግሣ አርአያ፣ ክቡር ራስ ከበደ መንገሻና ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ባርያ ጋብር[28] በወምበር ተቀመጡ። ከዚያም ቀጥሎ መኳንንትና ሊቃውንት በየማዕረጋቸው፣ ካህናት በየክፍላቸው ተቀምጠው ግብሩን ይጋበዙ ጀመር።

ከመኳንንት መካከል ቢትወደድ ወልደ ገብርኤል በሻህና ደጃዝማች ይገዙ በሀብቴ፣ ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ጐሹ፣ ደጃዝማች ወንዲራድ ድፋባቸው ለየክፍሉ ተመድበው ካህናቱን ሲጋብዙ ዋሉ። የቀሩትም መኳንንት ፊታውራሪ ዓምዬ፣ ፊታውራሪ ወልደ ማርያም፣ መልአከ ገነት ወልደ ሐና፣ ቀኛዝማች ከልክሌ ወዲያና ወዲህ እየተዘዋወሩ ደስ በሚያሰኝ አኳኋን ሲያስተናብሩ ዋሉ።

23 አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 237 ይመልከቱ። (አመነ)

24 በፊት እጨጌ ወልደ ጊዮርጊስ የነበሩት። አጭር የሕይወት ታሪክ ገጽ 156 ይመልከቱ። (አመነ)

25 አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 243 ይመልከቱ። (አመነ)

26 አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 240 ይመልከቱ። (አመነ)

27 አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 223 ይመልከቱ። (አመነ)

28 አጭር የሕይወት ታሪክ ገጽ 32 ይመልከቱ። (አመነ)

የድግሱ ግብዣ በዚህ ዓይነት ተከናውኖ ከተፈጸመ በኋላ ካህናት እየመረቁና እያሳረጉ ተመለሱ። ከዳስ ውጭም በዚሁ ቀን ለብዙ ነዳያንና ለችግረኞች መብልና መጠጥ፣ የገንዘብም ምጽዋት ሲታደል ዋለ።

## ስለ ዘማች መመለስ

ለዘመቻ ወጥተው የነበሩት ደጃዝማች ሙሉጌታ ይገዙ[29] አብረዋቸው ከዘመቱት መኳንንት ጋር ስለተመለሱ ግንቦት 12 ቀን ማክሰኞ አዲስ አበባ ሲገቡ ጃንሆይ ዘማቾቹን የሚቀበሉበት ሁለት አጅባር ድንኳን በታላቁ ግቢ ውስጥ ተተክሎ ተዘጋጀ። የዘማቾቹ መኳንንት ስም የሚከተለው ነው።

ደጃዝማች ሙሉጌታ ይገዙ፣ የጦር ሚኒስትር
ደጃዝማች መሸሻ ወልዴ፣ የከምባታ ገዥ
ደጃዝማች ብሩ ወልደ ገብርኤል፣ የሲዳሞ ገዥ
ደጃዝማች መኩሪያ ገርማሜ፣ የገሞ ክፍል ገዥ
ደጃዝማች ደበበ አንዳርጋቸው፣ የገሞ ክፍል ገዥ
አዛዥ በየነ፣ የሠራዊቱ ዋና አዛዥ
አዛዥ ወሰኔ፣ የወለኔ ጦር አዝማች
ከንቲባ ማተቤ

ሌሎችም የጦር አለቆች ነበሩ። ከመኳንንቱ መካከል ደጃዝማች መኩሪያ ገርማሜ በብርቱ ታመው ነበርና በቃሬዛ እየተጓዙ መጥተው አዲስ አበባ ሲደርሱ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ትእዛዝና ፈቃድ ለሕክምና ሆስፒታል ገቡ።

ደጃዝማች ሙሉጌታ ከመኳንንቱ ጋር አስቀድሞ በማለዳ ወደ ቤተ መንግሥት ገብተው ስለ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ሞት እያለቀሱ ሐዘናቸውን ገለጹ። ከዚያም በኋላ ወደ ሰፈር ተመልሰው በሰልፍ እየሆኑ በየተራ ከጃንሆይ ፊት እየቀረቡና እየፎከሩ ተገናኙ።

የጦር ሚኒስትሩ በአንቺም ውጊያ የማረኳቸውን መኳንንት ደጃዝማች ኃይለ ማርያም ወሌንና ፊታውራሪ ሹምዬ ጃሎን ሌሎቹንም ምርኮኞች በሰንሰለት አቆራኝተው ይዘው ገቡ። በዚህ ጊዜ ሙሴ ማዬ በአየር ላይ አውሮፕላን እያበረረና እያስገመገመ ለሰልፉ ድምቀት ሰጠው። ከጦር አለቆች ውስጥ ፊታውራሪ ተሰማ ጋረደውና ፊታውራሪ ወልደ ሚካኤል ዶሪ፣ ቀኛዝማች መንገሻ አየለ፣ ፊታውራሪ ተፈረደኝ፣ ግራዝማች ኃይሌ እንደብልሃቱ የመድፈኞች አለቃ ግራዝማች ሣህሌና ሌሎችም በጃንሆይ ፊት ቀርበው ፎከሩ።

ሰልፉ እንዳበቃ ደጃዝማች ሙሉጌታ ያቀረቡትን የዲስኩር ቃል የጽሕፈት ሚኒስትሩ ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል አነበቡት። ቃሉም ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

[29] አጭር የሕይወት ታሪክ ገጽ 223 ይመልከቱ። (አመኀ)

*ጃንሆይ፣*

*ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ*

*ደገኛዪቱ እናትዎ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ከዚህ ዓለም በሞት ማለፋቸው ምንም ሐዘኑ የሁላችን ቢሆን በተለይ ለጃንሆይ መሪር ሐዘን ነውና በራሴና ከእኔ ጋራ ባሉት መኳንንቶች በሠራዊቱም ስም ሆኜ እግዚአብሔር ያጥናዎ እያልሁ የሐዘንዎ ተካፋዮች መሆናችንን ከገለጽሁ በኋላ ቀጥሎ ያለውን ለመናገር የግርማዊነትዎን ፈቃድ እለምናለሁ።*

*ጃንሆይ*

*ከጥቂት ወራት አስቀድሞ ራስ ጉግሣ ወሌ ከፈቃድዎ መውጣታቸው ምንም እንኳ ጥቂት ጥቂት ቢወራ ግርማዊነትዎ እርግጥ ነው ብለው ለጊዜው አልተቀበሉትም ነበርና ከአዲስ አበባ ስነሣ የታዘዝሁት እርስ በርሱ የሚዋጋውን የራያንና የአዘቦን ኦሮሞ ለመቅጣት ነበር። ጅሩን ካለፍሁ በኋላ ግን ራስ ጉግሣ ወሌ ከፈቃድ መውጣታቸውና መሸፈታቸው ወሬው እየሰፋ ስለሄደ ግርማዊነትዎ ሠራዊቱን እያስከተተ ይልክልኝ ጀመር። ቢሆንም እኔ እንደ ተረዳሁት ጃንሆይ አሳብዎና ጭንቀትዎ ክርስቲያን የሆነ የወንድማማች ደም በከንቱ እንዳይፈስ ነበርና የበጌምድርን ድንበር እንዳላልፍ ትእዛዝዎ ስለ መጣልኝ በዳሩ ሰፍሬ ተቀመጥሁ።*

*ራስ ጉግሣ ወሌ ግን የኢትዮጵያን ጥቅም አጥፍተው የማይገባቸውን ክብር ለራሳቸው ለማግኘት የሐሰት ወሬ እያስወሩ የዋሁንና ደጉን ሕዝብ ማታለላቸውን ሰምቼ ለጃንሆይ ባመለከት ደግነትዎ የበዛ ነውና እርሳቸው መጥተው ይውጓችሁ እንጂ እናንተ የበጌምድርን ድምበር አትለፉ የሚል ትእዛዝዎ ቢመጣብኝ በታዘዝሁት ጸንቼ ተቀመጥሁ።*

*ራስ ጉግሣ ወሌ ግን በኢትዮጵያና በግርማዊነትዎ ላይ ያሰቡት ክፉ አሳብ የሚፈጸምላቸው ስለ መሰላቸው ከደብረ ታቦር ገሥግሠው ወደ እኛ ቢመጡ ጃንሆይ የዕርቅ ነገር ጀምረናል ብለው ልከውብኛልና የዚህ ነገር ሳይጨረስ ወደ እኛ አይምጡ። በዚያውም ላይ እናትዎ እቴጌ ጣይቱ አባትዎ ራስ ወሌ የደከሙበትንና የሞቱበትን አልጋ ለማፍረስ ቢነሡና የወንድማማች ደም ቢፋሰስ ለስምዎ ጉዳት ለርስዎም ጥፋት ነውና ስለ ሕያው እግዚአብሔር ብለው ይመለሱ ወይም ባሉበት ሰፍራ ይቆዩ ብዬ ብልክባቸው እምቢ ብለው ወደ ሰፈራችን መጡ።*

*ከዚህም በኋላ እኛ የታመንን ባሮችዎ በቋና አውራጃ አንችም በሚባል በጠራ ሜዳ ላይ ጦርነት ተጋጥመን በእግዚአብሔር ኃይል በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ግንባር ለሞታቸው በማይፈሩ አርበኞችዎ ብርታት ድል አደረግናቸው።*

*ወዲያውም የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ግርማዊነትዎ ከፍ ባለው በንጉሠ ነገሥት ዙፋን መቀመጥዎንና ኃይልና ጸጋ መልበስዎን ስለሰማን ደስታችን ከልክ ያለፈ ሆነልን።*

*አሁንም በግርማዊነትዎ ትእዛዝና ፈቃድ ከተለቀቁት ምርኮኞችና ላገር መጠበቂያ ወደ በጌምድር ከተመለሱት መድፎችና መትረየሶች በቀር ያመጣናቸውን ምርኮኞችና የጦር መሣሪያዎች በግርማዊነትዎ ፊት ያቀረብንበት የዛሬው ቀን የዘላለም መታሰቢያ ሆኖልን እንዲኖር አንጠራጠርም።*

*ከአዲስ አበባም ከተነሣንበት ቀን ጀምሮ ተመልሰን እስከ መጣንበት ቀን ድረስ ችግራችንን ለማቅለል በስልክም በደብዳቤም የግርማዊነትዎን ትእዛዝ ዘወትር ማግኘታችን ለሠራዊትዎ ከልብ ማሰብዎን ያስረዳናልና ለደስታችንና ለምስጋናችን ወሰን የለውም። ደግሞ በአንድ ወር የሄድነውን መንገድ በሦስት በሦስት ሰዓት በአይሮፕላን እየተመላለሱ ትእዛዝዎን ያስታወቁንን በጦርነቱም ከእኛ ሳይለዩ ሲረዱን የዋሉትን ሙሴ ማዪንና ሙሴ ኮርዝርን ለእነርሱም መሪ የሆነውን አሽከርዎን ግራዝማች ያረጋልን በግርማዊነትዎ ፊት ልናመሰግናቸው ይገባናል። ደግሞ የፈረንሳዊ መንግሥት ከቀድሞ ጀምሮ ምንም የኢትዮጵያ መንግሥት ወዳጅ ቢሆን ዛሬ ደግሞ በተለየ ከሀገሩ የመጡ አይሮፕላኖች ላደረጉልን ትልቅ እርዳታ ምስጋና የሚገባው መሆኑን ለግርማዊነትዎ ለማሳሰብ ብናገር ድፍረት አይሆንብኝም።*

*ጃንሆይ።*

*በታላቅ እምነት የጦር ሚኒስቴር አድርገው ከሾሙኝ በኋላ በግርማዊነትዎና በመንግሥትዎ ላይ የተነሣውን ዓመፀኛ ለመቅጣት ከታመኑት መኳንንቶችዎና አርበኞችዎ ጋራ ሄጄ ድል ማድረጋችንን የምሥራች በደብዳቤ እንዳስታወቅሁዎ አሁን ደግሞ በግርማዊነትዎ ፊት ቁመን በቃላችን ለመናገር በመቻላችን ለደስታችን ወሰን የለውም።*

*ለመቼውም ቢሆን በግርማዊነትዎና በመንግሥትዎ ላይ የሚነሣውን ዓመፀኛ ሞታችንን ሳንፈራ ለመቅጣትና ትእዛዝዎን ለመፈጸም ቃል ኪዳን መግባታችንን እንገልጽልዎታለን። ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ረጅም ዕድሜ ለአርበኞችዎና ለሕዝብዎ ሰላምና ዕረፍት እንዲሰጥልን እግዚአብሔርን እንለምናለን። ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር።*

ይህ ቃል ተነቦ ሲፈጸም ተጨበጨበ። ከዚህም ቀጥሎ የጃንሆይን ቃል ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ መስቀል አነበቡ። ቃሉም የሚከተለው ነው።

*ባንድ በራስ ጉግሣ ወሌ ምክንያት የወንድማማች ደም መፍሰሱ ምንም እንኳ ጉዳቱ የራሳችን ቢሆን የኛን የዘውድ ክብር ለመጠበቅና የኢትዮጵያን መንግሥት ለማፅናት በአንድ ልብ በአንድ ኃይል ሆናችሁ በመዋጋታችሁና ትእዛዛችንን በጥንቃቄ በመፈጸማችሁ ደስታችን ትልቅ መሆኑን እንገልጽላችኋለን።*

*ደግሞ የራስ ጉግሣ ተከታዮች ደማቸውን በከንቱ እስከ ማፍሰስ የደረሱት ዕውቀት ስለሌላቸው ጉዳቱ የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑን ባያውቁት እንደሆነ አይጠረጠርም፣ እናንተ ግን ጉዳት መሆኑን ስለተረዳችሁት በችኰላ የክርስቲያንና የወንድማማችን ደም ለማፍሰስ ሳትቸኩሉ ኃይል ሳላችሁ እንደሌላችሁ ሁናችሁ ትእዛዛችንን በመፈጸም ወደ ሰፈራችሁ እስኪመጡ ታግሣችሁ በመቆየታችሁና ከመጡባችሁም በኋላ በርትታችሁ በመዋጋታችሁ ድል በማድረጋችሁም ትልቅ ምስጋና ይገባችኋል። አንተም ደጃዝማች ሙሉጌታ ከቀድሞ ጀምሮ በልዩ ልዩ የመንግሥት ሥራ ላይ ምንም ታምነህ የቆየህ ብትሆን አሁን የጦር ሚኒስቴር አድርገን ከሾምንህ ወዲህ በመጀመሪያ መታዘዝህ እግዚአብሔር ይህን ድል ስለሰጠህ ዕድለኛነትህን ይገልጽልናል።*

*አሁንም ከራስ ጉግሣ ወሌ ጋራ በተደረገው ጦርነት ውስጥ ከአንተ ጋራ ታዘው ከዘመቱት ሰዎች መካከል ለሞቱት ለልጆቻቸው ማሳደጊያ ለቆሰሉትም*

*መታመሚያና መጦሪያ እንሰጣቸዋለንና በየስማቸውና በየባልደረባቸው ጽፈህ እንድታቀርብ ይሁን።*

*ለንጉሡና ለመንግሥቱ በእምነትና በቅንነት የሚያገለግል ሰው ዋጋውን የማያጣ መሆኑን እያወቃችሁ በሥራችሁ ሁሉ እንድትበረቱ ይሁን። ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር።*

ብለው ተናግረው ሲጨርሱ ሦስት ጊዜ ከፍ ያለ ጭብጨባ ተደረገ። ቀጥሎም ደጃዝማች ሙሉጌታ ምርኮኞቹን አቅርበው በየስማቸው እየጠሩ ከአስታወቁ በኋላ ስለ ዘማቾች ክብር የደስታ መግለጫ ሰባት ጊዜ መድፍ ተተኲሶ የሰልፉ ሥርዓት ተፈጸመ።

በዚህ ቀን ደጃዝማች በየነ ወንድማገኘሁ[30] ከጃንሆይ ምሕረት አገኙና በግዞት ከነበሩበት ስፍራ በፊታውራሪ መልሴ እጅ መጥተው አዲስ አበባ ገቡ።

## ስለ ሹመት

የጦር ሚኒስትሩ ደጃዝማች ሙሉጌታ የጦር ሚኒስቴርን እንደ ያዙ በግንቦት ወር እኩሌታ ራስ ወርቅ አስረው አረንጓዴ ሱሪ ታጥቀው፣ አረንጓዴ ጥላ አሲዘው ፊታውራሪ ተብለው ተሾሙ። የግዛት አገር በቀድሞ ግዛታቸው በሶዶ ላይ የጨቦና የአመያ የወጨሶ የገሞና የጋርዱላ የኮንሶ የዘይሴ ቆራጭነት ተጨመረላቸው።

እንደ ቆየው ልማድ የንጉሡ ነገሥቱ የጦር እንደራሴ የክብር ደረጃው እንደ ራሶች ሆኖ ሳለ የማዕረግ ስሙ ፊታውራሪ ይባላል። አሁንም ደጃዝማች ሙሉጌታ በፊታውራሪነት ተሰይመው የጦር እንደራሴ የሚጠራበትን ከፍተኛውን የማዕረግ ስም አግኝተዋል።

## ሐዘንን ለመግለጽ ከየአውራጃው ስለመጡ መኳንንት

በዚህ ወር በያውራጃው የነበሩ አገር ገዥዎችና መኳንንት ከየግዛታቸው ወደ አዲስ አበባ እየመጡ ስለ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ሞት ሲያለቅሱና ሐዘናቸውን ሲገልጹ ሰነበቱ። ለምሳሌ ደጃዝማች ደስታ ዳምጠውና[31] ባለቤታቸው ልዕልት ተናኘ ወርቅ ኃይለ ሥላሴ ከግዛታቸው ከከፋ ወደ አዲስ አበባ መጥተው በግንቦት 29 ቀን ስለ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ሞት እያለቀሱ ሐዘናቸውን ገለጹ።

## ለሕዝብ የተነገሩ አዋጆች

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በንጉሠ ነገሥት ዙፋን ከተቀመጡ በኋላ በግንቦትና በሐምሌ ወር አዋጆች እንዲነገሩ አደረጉ። ከአዋጆቹ አንዱ የሐሰት ወሬ ያወራ ሰው እንዲቀጣ የታዘዘበት ነው። ቃሉም ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

[30] ደጃዝማች በየነ አባ ሰብስብ (ፊት ሊጋባ የነበሩት) በቤተ መንግሥት የተከበሩና የታፈሩ ሰው ነበሩ። በነፍስ ግዳይ ምክንያት እስራት ተፈርዶባቸው አንኮበር በእስረኝነት ይኖሩ ነበር። በ1917 ዓ. ም. እስራቱ በምሕረት ቀረላቸውና ቱሉ ቢዶ ርስታቸው ላይ ይቀመጡ ነበር። ንግሥት ዘውዲቱ በሕይወት እያሉ አልጋ ወራሹ ሥልጣኑን ሊይዙት አይገባም በማለት የሤራ መልእክት ለመኳንንቱ መላካቸው ስለተሰማና ችሎት ላይም ኃይለ ቃል በፉከራ ስለተናገሩ የግርፋት ቅጣት ተፈጽሞባቸው በእስራት ወደ ሐረር ተወስደው ነበር። ምንጭ - መርስዔ ኅዘን ወልደ ቂርቆስ፣ *የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ*፣ ገጽ 277-279 ይመልከቱ። (አሙኅ)

[31] አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 241 ይመልከቱ። (አሙኅ)

አዋጅ

በየጊዜው ነገር እየፈጠርህ ያልሆነ ወሬ ታወራለህ አሁንም በሐሰት ወሬ የተነሣ እርስ በርሳችን ደም ከመፋሰስ አገር ከመበደል ደረሰ። ከእንግዲህ ወዲህ ግን አየሁ ብሎ የማይመሰክርበትን ሐሰት ነገር አውርቶ የተገኘ ፈጥሮ ያወራው የመንግሥትን ነገር የሚነካ የሆነ እንደሆነ እንደ ጥፋቱ መጠን ቅጣት ይፈረድበታል። በሌላውም ነገር ሰው ሐሰት ያወራው ባለ ቀሚስ[32] የሆነ እንደሆነ አራት መቶ ብር ያልተሾመ ሰው ሲሆን ሁለት መቶ ብር መቀጫ እየከፈለ እኩሌታው ለከሳሹ ተሰጥቶ እኩሌታው ወደ መንግሥት ይግባ። ይህንንም መቀጫ መክፈል የሚያቅተው ሰው እንደ ገንዘቡ ግምት ታስሮ ሥራ በመሥራት ይክፈል።

ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ወሬኛነት እንደ ሥራ ተቆጥሮ ገንዘብ ማግኛ በመሆኑ ምክንያት ነገር ፈጥሮ ማውራት ተለምዶ፣ ችግር በርክቶ ነበርና ደኅናው ሰው የአዋጁን ቃል አመሰገነ።

ሁለተኛውም አዋጅ ስለ ዜግነት ነገር በሐምሌ 15 ቀን 1922 ዓ.ም. የታወጀው ነው። አዋጁ ባለ አሥራ ስምንት አንቀጽ ሆኖ የውጭ አገር ሰው የኢትዮጵያ ዜጋ ሊሆን የሚችልበትንና የማይችልበትን ሁናቴ በዝርዝር ይደነግጋል። ካሁን በፊት ስለ ዜግነት የተጻፈ የዚህ ዓይነት ሕግ ስላልነበረ አሁን በወጣው ሕግ ሕዝቡ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥትን ትጋት አደነቀ። [ሙሉ አዋጁን ገጽ 16 ይመልከቱ።]

ሦስተኛውም ሕግ ቤተ ክርስቲያንን ስለ መሥራት ወይም ስለማደስ ነገር በሐምሌ 17 ቀን የታወጀው ነው። ቃሉም የሚከተለው ነው።

አዋጅ፣

መኳንንትም የሸአለቃም በየሰጠንህ ግዛት ለነፍስህ ደኅንነት ለሰላም ኑሮ ዕረፍት የሚለመንበት ቤተ ክርስቲያን ሳይሠራ መኖሪያ ቤትህን በማደራጀት ባለአገሩም ተጐዳን ብሎ ይጮሃል እንጂ ቤተ ክርስቲያን በመፍረሱ የተሠራውም ከተበላሸ በኋላ ባለመታደሱ ተቆርቋሪ ስላላገኘ ለነፍስም ጉዳት ለሥጋም መቅሠፍት የሚአመጣ ሆኖአልና በየአውራጃህ የተተከሉትን አብያተ ክርስቲያናት የፈረሱትን አሠራና ያረጁትን አሳድስ የክርስቲያን ምልክቱ የሃይማኖት መሠረቱ ቤተ ክርስቲያን መሥራት ነው። ነገር ግን በዚህ ምክንያት አለወገን አዝዘህ ድኻ አትበድልብኝ። አጥቢያውም በገንዘቡና በጉልበቱ ረድቶ ካወጣና ከአሠራ በኋላ በጉልበቱና ከገንዘቡ የሚተርፈውን ሥራ እኔ እረዳለሁና ችግርህን በደጃዝማች ደስታ ዳምጠው በኩል አስታውቀኝ። ከዚህ አዋጅ ወዲህ ግን እስከ አንድ ዓመት ድረስ ቤተ ክርስቲያኑ ሳይሠራ ቀርቶ መፍረሱን አለመታደሱንም የሰማን እንደሆነ የቤተ ክርስቲያኑ ሥራ የሚፈጀው ታስቦ በዐጠፌታ መቀጮ ይከፍላል። ይህም ገንዘብ ለቤተ ክርስቲያኑ ሥራና ጉዳይ ይገባል።

32 ባለ ሹመት። (አሙኀ)

አዋጅ

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ።

ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ።

የኢትዮጵያ ዜጋ ሆኖ ለመቈጠር ለሚገባው ለውጭ አገር ዜጋ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ሕግ አቁመናል።

መጀመሪያ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ከአንድ ኢትዮጵያዊ ወይም ከአንዲት ኢትዮጵያዊት የተወለደ ሁሉ የኢትዮጵያ ዜጋ ነው።

ሁለተኛ።

አንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ከውጭ አገር ሴት ጋር በሥርዓት የተጋባ እንደሆነ ሴትዮዋ የኢትዮጵያ ዜጋ ትሆናለች።

ሦስተኛ።

ይህን በመሰለ ጊዜ ጊዜ በሥርዓት የተደረገ ሁኖ የሚቈጠረው ጋብቻ።

ሀ) አንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ከአንዲት የውጭ አገር ሴት ጋራ እንደ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ወይም እንደ ኢትዮጵያ ጋብቻ ልማድ በባለ አኩል ደንብ (ሲቢል) በኢትዮጵያ የሚደረገው ጋብቻ ነው።

ለ) አንድ የኢትዮጵያ ሰው ከአንዲት የውጭ አገር ሴት ጋራ በተጋቡበት አገር እንደሚደረገው የጋብቻ ሥርዓት በውጭ አገር የሚደረገው ጋብቻ ነው።

አራተኛ።

አንዲት የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነች ሴት ከአንድ ከውጭ አገር ሰው ጋራ በሥርዓት የተጋባች እንደሆነ ከውጭ አገር ሰው ጋር በመጋባቷ ምክንያት የባሏን ዜግነት የምትይዝ የሆነች እንደ ሆነ የኢትዮጵያ ዜጋ መሆንዋ ይቀራል። የጋብቻዋ ሥርዓት የባሏን ዜግነት የማይሰጣት የሆነ እንደሆነ ግን የኢትዮጵያ ዜጋ እንደሆነች ትቀራለች። ነገር ግን በጋብቻ ምክንያት የውጭ አገር ዜጋ የሆነችው ሴት ባልርስት የሆነች እንደሆነ፤ የርስቷ ነገር የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ባቆመው የርስት ደንብ ይጨረሳል።

አምስተኛ።

ይህን በመሰለ ጊዜ በሥርዓት የተደረገ ሁኖ የሚቈጠረው ጋብቻ።

ሀ) የኢትዮጵያ ሴት ከአንድ የውጭ አገር ሰው ጋራ በባሏ ቆንስል ፊት በኢትዮጵያ የምታደረገው ጋብቻ ነው።

ለ) የኢትዮጵያ ሴት ከአንድ የውጭ አገር ሰው ጋራ እንደ ባሏዋ አገር ሕግ፤ ጋብቻውም በሚፈጸምበት አገር እንደ ሚደረገው የሕግ ሥርዓት በውጭ አገር የምታደርገው ጋብቻ ነው።

ስድስተኛ።

ከዚህ በላይ በተጻፈው ክፍል እንደ ተነገረው የኢትዮጵያና የውጭ አገር ሰዎች በሥርዓት ተጋብተው ልጆች የወለዱ እንደ ሆነ የተወለዱት ልጆች ሁሉ የአባታቸውን ዜግነት ይይዛሉ። ስለሆነ የጋብቻ ሥርዓት ፈጽመው ከተጋቡ ከአንድ ኢትዮጵያዊና ከአንዲት የውጭ አገር ሴት የተወለደ ልጅ የእናቱን የቀድሞ ዜግነት አለመያዙን ሥልጣን ባላቸው በኢትዮጵያ ሹማምንቶች ፊት ተጠይቆ ማስረዳት አለበት።

ሰባተኛ።

የጋብቻ ሥርዓት ፈጽመው ከተጋቡ ከአንዲት የኢትዮጵያ ሴትና ከአንድ የውጭ አገር ሰው የተወለደ ልጅ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ እንደ ሆነ፤ ከአባቱ ዜግነት መውጣቱን አስመስክሮ በማናቸውም ጊዜ ቢሆን ወደ ኢትዮጵያ ዜግነት ሊመለስ ይችላል።

ስምንተኛ።

አንድ የውጭ አገር ሰውና አንዲት የኢትዮጵያ ሴት ልጅ ከወለዱ በኋላ እንደ አባትየው አገር ሕግ በሥራዓት የተጋቡ እንደሆነ፤ ደግሞ የአባትየው አገር ሕግ ልጁን የውጭ አገር ዜጋ የሚያደርገውና የውጭ አገር ዜጋም በመሆኑ ምክንያት የሚቀበለውን ሥልጣን ሁሉ የሚያሳጣው የሆነ እንደሆነ፤ ከጋብቻ በፊት የተወለደው ልጅ የአባቱን የውጭ አገር ዜግነት ይይዛል። በዜግነቱ የሚቀበለውን ሥልጣን ሁሉ ለማግኘት ያልቻለ እንደ ሆነ ግን የኢትዮጵያ ዜግነቱን ጠብቆ ይኖራል።

ዘጠነኛ።

አንድ የውጭ አገር ሰውና አንዲት የኢትዮጵያ ሴት ሳይጋቡ ልጅ የወለዱ እንደ ሆነ፤ የውጭው አገር ሰው ልጄ ነው ብሎ ቢቀበለውም ልጄ ነው ብሎ በተቀበለ ጊዜ የአባትየው አገር ሕግና ሥርዓት ለልጁ የአባቱን ዜግነትና ዜጋ በመሆኑ ምክንያት የሚቀበለውን ሥልጣን ሁሉ የሚያገኝ ካልሆነ በቀር የኢትዮጵያ ዜጋ መሆኑ ሊቀርበት አይችልም።

ዓሥረኛ።

የውጭ አገር ሰዎች እንደ አገራቸው ሥርዓትና ሕግ እንደ የኢትዮጵያ ልጅ ሞጋሳ አድርገው ያሳደጉ እንደ ሆን የልጁ የቀድሞ የኢትዮጵያ ዜግነቱ ምንም ቢሆን አይለወጥም።

ዓሥራ አንደኛ።

ሀ) አንዲት የኢትዮጵያ ዜጋ ከውጭ አገር ሰው ጋራ በመጋባቷ ምክንያት የሌላ አገር ዜጋ ሁና ልትቈጠር የተገባት እንደ ሆነ።

ለ) አንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ዜግነቱን ለውጦ የውጭ አገር ዜጋ የሆነ እንደሆነ የኢትዮጵያ ዜጋ መሆናቸው ይቀራል።

ዓሥራ ሁለተኛ።

ሀ) እንደ አገሩ ሕግ በፈቃዱ አዳሪ ለመሆን ወደሚችልበት ዕድሜ የደረሰ።

ለ) ቢያንስ ቢያንስ አምስት ዓመት በኢትዮጵያ የኖረ።

ሐ) ለሕይወቱና ለራሱ ለቤተ ዘመዱም የሚያስፈልገውን ነገር ለማግኘት የሚችል።

መ) የአማርኛ ቋንቋ የሚናገርና የሚጽፍ።

ሠ) ከዚህ ቀድሞ በኃጢአት ወይም በወንጀል ያልተፈረደበት መሆኑን የሚያመሰክር የውጭ አገር ሰው ሁሉ የኢትዮጵያ ዜጋ ለመሆን ይችላል።

ዓሥራ ሦስተኛ።

የኢትዮጵያ ዜጋ ለመሆን የሚፈልገውም የውጭ አገር ሰው ጥያቄውን ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያቀርባል። ከዚህም ጥያቄ ጋራ ማን እንደ ሆነ የሚመሰክርለትን ወረቀትና ከዚህ ቀድሞ ተከሶ እንደሆነ የተፈረደውን ነገር የሚያስረዳ የፍርድ ወረቀቱን ጨምሮ ያቀርባል።

ዓሥራ አራተኛ።

በተለይ የአገር ግዛት ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሌላም አንድ የመንግሥት ሹም በአንድነት ሁነው የኢትዮጵያ ዜጋ ለመሆን ከሚጠይቀው ሰው ጋራ በቀጥታ ከተነጋገሩ በኋላ፤ ጥያቄውን ተመልከተው የሚያስፈልገውን ምርመራ አድርገው የኢትዮጵያ ዜጋ እንዲሆን ይፈቅዱለታል ወይም ይከላከላል።

ዓሥራ አምስተኛ።

ዜግነቱንም በመንግሥት ማስታወቂያ (በጋዜጣ) ይቀበላል። አዲሱም የኢትዮጵያ ዜጋ በነዚሁ ሹሞች ፊት ቀርቦ የኢትዮጵያን መንግሥት እንዳይከዳ ይምላል።

ዓሥራ ስድስተኛ።

የውጭ አገር ሰው በዚህ አደራረግ የተቀበለው የኢትዮጵያ ዜግነት ለራሱ ብቻ ይረጋል እንጂ ሚስቱ የኢትዮጵያ ዜጋ ለመሆን ካልጠየቀች በቀር አስቀድሞ የያዘቿውን ዜግነት አይለውጠውም።

ዓሥራ ሰባተኛ።

አስቀድሞ የኢትዮጵያ ዜጋ የነበሩ የውጭ አገር ዜጋ የሆኑ ሰዎች በኢትዮጵያ ለመኖር ተመልሰው መጥተው እንደሆነ ወደ ኢትዮጵያ ዜግነት ለመመለስ ከመንግሥት የጠየቁ እንደሆነ የኢትዮጵያ ዜጋ ለመሆን ይችላሉ።

ዓሥራ ስምንተኛ።

ከውጭ አገር ሰው ጋራ በመጋባትዋ ምክንያት የኢትዮጵያ ዜጋ መሆኑዋ የቀረ የኢትዮጵያ ሴት ከባሏ ተፋትታ ወይም ባሏ መቶባት ጋብቻዋ ፈርሶ ወይም ከርሱ በመለየቷ ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሳ የተቀመጠች እንደ ሆነና እንደ ቀድሞ የኢትዮጵያ ዜጋ ልሁን ብላ ከኢትዮጵያ መንግሥት የጠየቀች እንደሆነ፤ እንደ ገና የኢትዮጵያ ዜጋ ለመሆን ትችላለች።

ይህ ሕግ ከዚህ ቀድሞ ስለ ዜግነት ነገር የወጡትን ሕጎች ሁሉ ያፈርሳል።

ሐምሌ ፲፭ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ።

**የዜግነት አዋጅ**

## ወታደሮችን ስለ ማሠልጠን

ወታደሮችን በዘመናዊ የሰልፍ ትምህርት ማሠልጠን የተጀመረው በአቤቶ ኢያሱ ዘመን በ1906 ዓ.ም. ነበር። አሠልጣኞች ሆነው ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኙትም ሰዎች ስለ ሥራ ፍለጋ ወደ ውጭ አገር ሄደው በወታደርነት ተቀጥረው በማገልገል ሳሉ የሰልፍ ትምህርት ተምረውና ዐውቀው የተመለሱ ኢትዮጵያውያን ናቸው። ከእነርሱም ዋነኞቹ እነ አቃ ገብሩ ናቸው። ከሰገሌ ዘመቻ በኋላም እነ ግራዝማች ገብረ ዮሐንስ መጥተው አስተምረዋል።

አቃ ገብሩ በትሪፖሊ ለኢጣልያኖች ተቀጥረው በወታደርነት ሲሠሩ የነበሩ ናቸው። በአቤቶ ኢያሱ ዘመን ከትሪፖሊ ወደ አሥመራ ተመልሰው ነበርና በአትዮጵያ ቆንስል በልጅ ነሲቡ ዛማኔል[33] በኩል በምሥጢር ተላልከው በ1906 ዓ.ም. እንደ እርሳቸው ከሆኑ ከአራት መቶ አሥራ ሁለት ወታደሮች ጋራ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ጥርምቡሌ የተባለውን የከተማ ዘበኛ በአዲስ አበባ አቋቁመው አሠለጠኑ። ጥሩምቡሌዎች ያገለገሉት በከተማ ብቻ ሳይሆን በሰገሌ ዘመቻ ጊዜም በጦር ሜዳ ላይ በአሳዩት የጀግንነት ሥራ ተመስግነዋል።[34] ከዚያ በኋላም የጥርምቡሌ ጭፍራ ድርጅት ቀስ በቀስ እየተቀነሰ ሄዶ ወደ ሌላ አቋም ተለውጧል።

ግራዝማች ገብረ ዮሐንስ በ1910 ዓ.ም. በልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኰንን ፈቃድና ትእዛዝ የመትረየስ ዘበኛ የተባለውን ጭፍራ የሰልፍ ትምህርት እያስተማሩ ያሠለጠኑ ናቸው። እርሳቸው ከሀገራቸው ወጥተው በምሥራቅ አፍሪካ ለቅኝ አገር ገዥዎች በወታደርነት በማገልገል ሳሉ የሰልፍ ትምህርት ተምረውና ዐውቀው የተመለሱ ናቸው።[35]

የመትረየስ ዘበኛ የተባለው ጭፍራ በኋለኛው ጊዜ የክብር ዘበኛ ተብሎ የተጠራው ነው። እርሱም በተሟላ ትጥቅና መሣሪያ ደርጅቶ ይታይ ነበር።

እንዲሁ ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ ገዥ ከንቲባ ነሲቡ ዛማኔል ቀድሞ በአቃ ገብሩ ተጀምሮ የነበረውን የሰልፍ ትምህርት በመቀጠል የከተማው ዘበኞች በሰልፍ ትምህርት እንዲሠለጥኑ አደረጉ። እነርሱም በ1919 ዓ.ም. በመስቀል የደመራ በዓል ላይ ሰልፍ አሳይተው የተመሰገኑት ናቸው።

ከዚህም በኋላ የወታደር ትምህርት በይበልጥ እንዲስፋፋ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ ባለፈው ዓመት ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ከቤልጅግ አገር የጦር መኰንኖች ለአስተማሪነት ተቀጥረው እንዲመጡና የክብር ዘበኞችን እንዲያስተምሩ አደረጉ። እነርሱም ማጆር ፖሌ፣ ካፐቴን ፋኔል፣ ካፐቴን ሲስተርማን የተባሉ ናቸው።

ቤልጅጐች የክብር ዘበኛን ማሠልጠን ከጀመሩ በኋላ የቀድሞው አሠልጣኝ ግራዝማች ገብረ ዮሐንስ ለውጋዴን ጠረፍ ጠባቂ የሚሆን ጭፍራ እያስተማሩ እንዲያሠለጥኑ ስለ ታዘዙ ከአንድ ሻምበል ጭፍራ ጋራ በ1922 ዓ.ም. ወደ ጅጅጋ ከተማ ተዛውረው ይሠሩ ጀመር።

---

33 አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 231 ይመልከቱ። (አመኀ)

34 የንግሥት ዘውዲቱ የዘመን ታሪክ፣ ገጽ 174 እይ። [መርስዔ ኀዘን ወ/ቂ፣ የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ] (ብመኀ)

35 መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ገጽ 318 ይመልከቱ። (ብመኀ)

## ስለ አውሮፕላን ነጂዎች

አውሮፕላን በ1920 ዓ.ም. በነሐሴ ወር መጥቶ ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ አበባ ላይ ከዐረፈ በኋላ የአውሮፕላን ነጂነት ትምህርት አዲስ አበባ ላይ ተጀመረ። በዚህም ዓመት በሰኔ ወር ትምህርት ቤቱ ወደ ጅጅጋ ከተማ ተዛውሮ ትምህርቱ ቀጠለ። ምክንያቱም በክረምት ወራት የአዲስ አበባ ዝናሙና ጭቃው አስቸጋሪ ስለሆነ ጅጅጋ ግን በክረምት ወራት ምቹ መሆኑን በመመልከት ነው።



ከግራ ወደ ቀኝ፤ ደስታ፣ ደምሴ፣ ሥዩም፣ አስፋው፣ ፒካፔር፣ ቬርዴር፣ ሚሽካ
የአውሮፕላን ነጅነት ተማሪዎች ከአስተማሪያቸው ጋር

አውሮፕላን አስተማሪው ሙሴ ቬርዴርና ሜካኒሲዬው ሙሴ ፒካፔር ክረምቱን ሙሉ ሲያስተምሩና አውሮፕላን ሲያስነዱ ጅጅጋ ላይ ከረሙ። ተማሪዎቹ ብዙዎች ሲሆኑ ከእነርሱም መካከል ሚሽካ ባቢቼፍንና[36] አስፋው ዓሊን[37] በተለይ አስታውሳቸዋለሁ።


## ስለ ጦር መኰንኖች

ካፕቴን ዊድሜር የተባለ ፈረንሳዊ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ትእዛዝ በጅጅጋ ከተማ የጦር መኰንኖችን እያስተማረ ሲያሠለጥን ከረመ። መኰንኖቹ ለዘውድ በዓል ቀን ለሥራ ብቁ ሆነው እንዲገኙ ተፈልጎ ነበርና ክረምቱን ያለ ዕረፍት በትጋት ሲማሩ ከረሙ።

[36] አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 223 ይመልከቱ። (አሙን)

[37] አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 232 ይመልከቱ። (አሙን)

በዚህ ጊዜ ዘውድነህ ቅጣው የተባለው ወጣት ለፈረንሳዊ ቋንቋ አስተርጓሚ ሆኖ በትምህርቱ ሥራ ከካፕቴን ዊድሜር ጋር በትጋት ይሠራ ነበር።



ፊታውራሪ ታፈሰ፣ ሙሴ ቬርዴር፣ ካፕቴን ዊድሜር

## ስለ ሹም ሽር

በዚህ ወራት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሹመት እየሰጡ ብዙ ሰዎችን ደስ አሰኙ። ይህም እንደሚከተለው ነው።

በግንቦት 20 ቀን ፊታውራሪ ዓምዴ ሀብተ ሥላሴ ደጃዝማች ተብለው አንጾኪያንና ግድምን፣ ኤፍራታን ተሾሙ።

ሊቀ መኳስ አምባቸው ገሠሠ ደጃዝማች ተብለው ዋድላና ደላንታን ተሾሙ። ፊታውራሪ በየነ መርዕድ[38] ደጃዝማች ተብለው ጉናንና ባኮን ተሾሙ። ፊታውራሪ ገብረ ማርያም ጋሪ ደጃዝማች ተብለው የሐረር እንደራሴ ሆኑ።

በሰኔ 19 ቀን የሚከተሉት ሰዎች ተሾሙ። ደጃዝማች ደበበ አንዳርጋቸው ማጂንና ጐልደያን፣ ፊታውራሪ ወልደ ማርያም በልታን የደጃዝማች ደበበ የነበረውን፣ ወምበሩ ግራዝማች ባንት ይዋሉ ወረገኑንና ቀኛዝማች ተገኝ የግራዝማች ባንት ይዋሉ የነበረውን ወምበርነትና[39] አቶ አበበ ናቄ ባላምባራስ ተብለው የግራዝማች ገብረ ወልድን ወምበርነት፣

[38] አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 226 ይመልከቱ። (አመኀ)

[39] ዳኝነት (አመኀ)

ፊታውራሪ ዱሬሳ አመንቴ ብላታ ተብለው የእርሻ ሚኒስቴርን ዲሬክተርነት፣ አቶ ወልደ አማኑኤል ጠምቄ የኢሉባቦርን ነጋድራስነት፣ አቶ ታፈሰ ወርቅ በፊታውራሪ ሙሉጌታ ግዛት ነጋድራስነትን፣ አቶ ደሳለኝ ቸርነት የአቶ ታፈሰ ወርቅን የፍርድ ጸሐፊዎች አለቅነትን ተሾሙ።

በሐምሌ 17 ቀን የሚከተሉት ሰዎች ተሾሙ። ደጃዝማች አደፍርሰው ኖኖ እነሞርና እነቆር በግዛት ተሰጥቷቸው የግቢ ዘበኛ አለቅነትን፣ ፊታውራሪ ኃይሌ ወልደ ሩፌ የባሶ ግዛት ተሰጥቷቸው የስልክ ሚኒስቴርን፣ ቀኛዝማች ኃይለ ሥላሴ መገኖ በግርማዊት እቴጌ መነን ክፍል ሙሉ ቤት አዛዥነትን፤ ፊታውራሪ ጣሰው ዋለሉ ዋና እልፍኝ አስከልካይነትን፣ ቀኛዝማች ወልደ ዮሐንስ ወልደ አብ በላይኛውና በታችኛው ግቢ የጥይት ቤት ሻለቅነትን፣ ቀኛዝማች ለጥ ይበሉ ገብሬ ጥቁር ምድርንና የግቢ ዘበኛ ዲሬክተርነትን፣ ቀኛዝማች ፀምሩ ገብረ ሥላሴ በፍርድ ሚኒስቴር የቀለብና የደመወዝ አላፊነት ሹመትን፣ ባላምባራስ ተክለ ማርቆስ ወልደ ገብርኤል ግራዝማች ተብለው የጽሕፈት ሚኒስቴር ዲሬክተርነትን፣ ግራዝማች ኃይሌ እንደብልሃቱ የሠይፈ ጃግሬ ሻለቅነትን፣ ግራዝማች ግርማ ማሞ በሲዳሞ ውስጥ የግዛት አገርን ተሾሙ።

ሐምሌ 20 ቀን ልጅ ተፈራ ገብረ ማርያም የጅቡቲን ቆንስልነት ተሾሙ።

በነሐሴ 22 ቀን የሚከተሉት ሰዎች ተሾሙ። ግራዝማች ወልደ መድኅን የአድአ ምስለኔነትን፣[40] ግራዝማች አበበ ረዴ የባለሟል ቤተ ደንብ አለቅነትን፣ ልጅ ታፈሰ አደፍርሰው ባላምባራስ ተብለው የአቡጀዲ ፋብሪካን፣ ልጅ ተረፈ ወልደ ገብርኤል ከልጅ ተሰማ ዓሊ በታች የእልፍኝ አስከልካይነትን፣ ልጅ ጌታሁን ዋለሉ የግራዝማች አበበ ረዴ ምክትልነትን ተሾሙ።

በነሐሴ 26 ቀን ጸሐፌ ትእዛዝ አፈ ወርቅ የእርሻ ሚኒስቴርን፣ ሊቀ መኳስ መንገሻ ወሰኔ ደጃዝማች ተብለው ቅምብቢትንና ትቤን፣ ደጃዝማች መስፍን ገመች ቋራን ተሾሙ።

ከዚህም ሌላ በሚያዝያ 9 ቀን አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ የብርሃንና ሰላምን ዲሬክተርነት ተሾመው ነበር። እኒህ ሰው በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት የግቢው አስተዳዳሪ ሆነው ተሾመው አራት ዓመት ያህል የሠሩ ናቸው። የግእዝና የአማርኛ ቅኔ ዐዋቂ ከመሆናቸው የተነሣ በየጊዜው እየጻፉ በጋዜጣ በሚያወጡት ቃል በሁሉም ዘንድ የታወቁና የተመሰገኑ ናቸው።

አሁንም የሥነ ጽሕፈት ችሎታቸው ታውቆላቸው የጋዜጣው ዲሬክተር ሆነው ስለተሾሙ አንድ ጋዜጠኛ እንዲህ የሚል የግጥም ቃል በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ጽፎ አወጣ።

ብርሃንና ሰላም መልኩን አሳመረ
በማኅተመ ወርቅ ይታተም ጀመረ።
እንግዲህ እንጻፍ ስንፈት ሳይገባን
በማኅተመ ወርቅ ከታተመልን።

[40] ምስለኔ ከጭቃ ሹም በላይ የሆነ የመንግሥት፣ ያገረ ገዥ ወይም የመልከኛ ሹም (ተወካይ)። (አሙኀ)

## የመኪና መንገዶች ሥራ

ከደሴ ወደ አሰብ የሚያልፍ የመኪና መንገድ ባለፈው ዓመት በመሐንዲሶች ተቀይሶ ሥራው ተጀምሮ ነበርና በዚህም ዓመት ሥራው እንደቀጠለ ነው። ለመንገድ ሥራ አላፊ የሆኑት ሹም ባላምባራስ በየነ መርሻ ሲሆኑ ዋነኞቹም መሐንዲሶች ከሆላንድ ተቀጥረው የመጡት ሙሴ ደማስና ሙሴ ደቭሪስ ይባላሉ።



አዛዥ ወርቅነህ

ወደ ጅማም የሚያልፍ የመኪና መንገድ በ1921 ዓ.ም. በመጋቢት ወር ከአዲስ አበባ ተጀምሮ ነበር፤ በዚህ ዓመትም የቅየሳው ሥራ እስከ ወሊሶ መድረሱ ተነገረ። በድንጋይ ንጣፍ የተሠራው መንገድ እስከ ሰበታ ከተማ ከደረሰ በኋላ በአቃቂና በሌሎችም ወንዞች ላይ ሦስት ድልድዮች በጥርብ ድንጋይና በቅስት ተሠርተው ነበር።

የሥራው ዋና ሹም አዛዥ ወርቅነህ እሸቴ በግንቦት 21 ቀን ግርማዊ ንጉሥ ነገሥትን ከመሳፍንትና ከመኳንንት ጋር ጠርተው አስመርቀው ድልድዮቹ ለትራፊክ ተከፈቱ።

አዛዥ ወርቅነህ[41] በዚህ ቀን በጃንሆይ ፊት ባደረጉት ንግግር ለሥራው የተደረገው ወጭ ገንዘብ 142,254 ብር መሆኑን ገለጹ።

አሠሪውን አቶ መንገሻ ከፈላን ስለ ትጋቱ ከአመሰገኑ በኋላም መሳፍንትና መኳንንት እርዳታ እንዲሰጡ ስለጠየቁ በዚያው ዕለት ስድሳ ሺህ ብር ያህል የእርዳታ ገቢ ተገኘ።

---

41 አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 238 ይመልከቱ። (አመነ)

| | ብር |
|---|---|
| ልዑል ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት | 20,000 |
| ደጃዝማች ብሩ ወልደ ገብርኤል | 10,000 |
| ልዑል አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ | 10,000 |
| ልዑል ራስ ሥዩም መንገሻ | 5,000 |
| አፈ ንጉሥ አረጋይ ቢቸሬ | 3,000 |
| ደጃዝማች አበራ ተድላ | 5,000 |
| ሊጋባ ወዳጄ ውቤ | 2,000 |
| ፊታውራሪ ጣሰው ዋለሉ | 2,000 |
| ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል | 1,000 |
| ፊታውራሪ አሥራት ወልደ ገብርኤል | 1,000 |
| ቀኛዝማች ፍቅረ ሥላሴ ከተማ | 1,000 |
| ልጅ በልሁ ደገፉ | 100 |
| ባላምባራስ ቸርነት አያልነህ | 100 |
| ድምር | 60,200 |

አቶ ተሰማ እሸቴም[42] በጅማ ከተማ ያላቸውን 1 ሺህ ሜትር ካሬ ባዶ ቦታ ለካሚዮን ማቆሚያ ስጥቻለሁ ሲሉ አስታወቁ። ከዚህም በኋላ የምረቃው በዓል ተፈጽሞ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ወደ ቤተ መንግሥታቸው ተመለሱ።

## በወሰን ላይ ስለ ደረሰ ግጭት

በጅጅጋ በኩል ባለው ወሰን ላይ በእንግሊዝ ኢላሎችና[43] በኢትዮጵያ ወታደሮች መካከል በሰኔ መጨረሻ ግድም ግጭት ሆኖ አራት የጅጅጋ ወታደሮች ተገደሉ። በዚህም ምክንያት ሁለቱ መንግሥታት (እንግሊዝና ኢትዮጵያ) በየበኩላቸው ያዘዟቸው ሹማምንት ወደ ስፍራው ሄደው ነገሩን ይመረምሩ ጀመር። የግጭቱ አነሣሥና የነገሩ ሁናቴ እንደሚከተለው ነበር።


በጅጅጋ በኩል ያለው የሁለቱ መንግሥታት ግዛት የወሰን መስመር በግንቦት 7 ቀን 1889 ዓ.ም. በተፈረመ ውል ተጠቅሶ ከመጻፉ በስተቀር በመሬት ላይ የተከለለ የወሰን ምልክት አልነበረውም። ስለዚህም የገደቡርሲን ጎሣዎች በያመቱ ግብር የሚያስገብሩ የጅጅጋ ወታደሮች በገደቡርሲ ወረዳ እስከ ፉሉንፉል[44] ኮረብታ እየሄዱ ግብር ሲቀበሉ ይኖሩ ነበር። በዚህም ዓመት ግብር ለማስገባት ከጅጅጋ የተላኩ አሥር ወታደሮች ወደ ገደቡርሲ ሄደው፤ የቆየውን ልማድ በመከተል እስከ ፉሉንፉል ኮረብታ ድረስ ሄዱና ከዘላኖቹ የግብር ከብት ተቀብለው እየነዱ ወደ ሜራሌ ተመለሱ። ይህን ነገር የእንግሊዝ ኢላሎች በሰሙ ጊዜ ከቦረማ

[42] አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 228 ይመልከቱ። (አሙኀ)

[43] ኢላሎ ማለት ደንበኛ ወታደር ሳይሆን የአገርን ጸጥታ የሚጠብቅ ዘበኛ ማለት ነው። (ብሙኀ)

[44] ይህ ኮረብታ ከእንግሊዞች ግዛት ከቦረማ በግምት ከ10 ማይልስ [16 ኪ/ሜ] ያልራቀ ነው። (ብሙኀ)

ተነሥተው ወዲያው ዕለቱን ተከታተሏቸው። በማግሥቱም የጅጅጋ ወታደሮች ወደ ሰፈሩበት ወደ ሜራሌ ደርሰው በእንግሊዝ ግዛት ውስጥ ገብታችኋልና እጃችሁን ስጡን ብለው ጠየቋቸው። ወታደሮቹም ይህ ያለንበት ስፍራ የኢትዮጵያ ግዛት ስለሆነ እጃችንን አንሰጥም በማለት እምቢ ስላሉ ጠብ ተነሥቶ ተኲስ ተጀመረና አራት የጅጅጋ ወታደሮች ተገደሉ። የቀሩትም ሸሽተው ጅጅጋ ገብተው የደረሰባቸውን ነገር ለአለቆቻቸው አስታወቁ።




አቶ ዘውዴ ታደሰ፣ ከጀርባ የቆንስሉ ጸሐፊ
በሐርጌሳ የኢትዮጵያ ቆንስል

ይህ ግጭት በሁለቱ መንግሥታት ዘንድ ስለተሰማ ሹማምንቶቻቸው ወደ ስፍራው ሄደው ነገሩን በኮሚሲዮን እንዲመረምሩ በየበኩላቸው አዘዙ። በእንግሊዝ መንግሥት በኩል የታዘዙት የእንግሊዝ ሱማሌላንድ ዋና ጸሐፊ ሜጀር ሎረንስ ሲሆኑ፤ በኢትዮጵያም መንግሥት በኩል የጅጅጋ አውራጃ ገዥ ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል[45] ታዘዙ። በሐርጌሳ ተቀማጭ የሆኑት የኢትዮጵያ ቆንስል አቶ ዘውዴ ታደሰም በተጨማሪ ታዘዙ።

ከዚህ በኋላ ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል በጅጅጋ ካሉት ሹማምንትና ሠራተኞች አንዳንዶችን አስከትለው በሐምሌ 7 ቀን 1922 ዓ.ም. ወደ ገደቡርሲ ተጓዙ። የጦር መኰንኖችን ለማሠልጠን የመጣ ካፒቴን ዊድሜርና የትምህርት ቤቱ ሹም አቶ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስም የጉዳዩ ተካፋይ በመሆን አብረው ተጓዙ። እንግዲህ ከጅጅጋ በተነሡበት በመጀመሪያ ቀን ሸቤሌ ከተማ አደሩና በማግሥቱ ኀግቲ ደርሰው ሰፈሩ። ኀግቲ ለገደቡርሲዎችና

[45] አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 229 ይመልከቱ። (አመነ)

ለኢሣዎች አማካይ ስፍራ ከመሆንዋ በላይ ለወሰንም የቀረበች ናት። ከጅጅጋም 80 ኪሎ ሜትር ያህል የምትርቅ ይመስለኛል። ስለዚህም ጎግቲ የሕዝብ መስፈሪያ ከተማ እንድትሆን በዚሁ ጊዜ በፊታውራሪ ታፈሰ ለከተማነት ተቆረቆረች። ስለ ጸጥታ ጥበቃም አንድ የመቶ አለቃ ከነጭፍራው እንዲቀመጥበት ተደረገ።




አምኃ መርስዔ ኅዘን

ግጭቱ የደረሰበትን አካባቢ የሚያሳይ ካርታ

ከዚህ በኋላ ፊታውራሪ ታፈሰ ከጎግቲ ተነሥተው ጉዟቸውን ወደ ምሥራቅ ቀጠሉና አውቦባ ላይ ሰፈሩ። አውቦባ በሜራሌና በትልቁ የደረብሌ ተራራ መካከል የሚገኝ የእስላሞች ቅዱስ ስፍራ ነው። የጥንት መስጊድ ፍርስራሽ ይታይበታል። ደረብሌ የተባለው ተራራ ከጫፉ ላይ ሆኖ ሌሊት ወደ ህንድ ውቅያኖስ ለሚመለከት ሰው የመርከቦችን መብራት የሚያሳይ ከፍተኛ ተራራ ነው።

ከእንግሊዝ መንግሥት በኩል የታዘዘው ሜጀር ሎረንስ ሰፈሩን ለአውቦባ አቅራቢያ በሆነች በቀልጨድ ኮረብታ ሥር አደረገ። ከዚያም በኋላ የኮሚሲዮኑ ስብሰባ በየተራ በሁለቱም ሰፈር በአውቦባና በቀልጨድ ላይ እየተደረገ የነገሩ ምርመራ ተጀመረ። ጠብ ወደተደረገባቸውም ስፍራዎች ወደ ፉሉንፉልና ወደ ሜራሌ እየሄዱ አገሩን ተመለከቱ።

የአራቱን ወታደሮችም መቃብር በሜራሌ ላይ ጐበኙ። የምርመራውና የጉብኘቱ ሥራ አሥራ አምስት ቀን ያህል ቀጥሎ ከተፈጸመ በኋላ ግጭት ሊደርስ የቻለው የወሰን ክልል ባለመኖሩ ምክንያት መሆኑ ስለታወቀ የምርመራው ውጤት ይኸው ሆነ። ምክንያቱም ፉሉንፉልንና ሜራሌን እንግሊዞችም ኢትዮጵያውያንም በበኩላቸው የእኛ ግዛት ናቸው ስለሚሉ ወሰን አልፎ የገባው የትኛው ወገን እንደሆነ ለመለየት ስላልተቻለ ነው።

ስለዚህ በኢትዮጵያና በእንግሊዝ ሱማሌ ግዛት መካከል ያለው ወሰን በውሉ መሠረት በመሬት ላይ በቶሎ እንዲከለል ሁለቱም ወገኖች ለየመንግሥታቸው እንዲያሳስቡ እስከዚያም ድረስ በየጊዜው ግጭት እንዳይፈጠር በቆልጨድ ኮረብታ ሥር አድርጎ ወደ ሐሪራድ ወንዝ የሚወስደው የእግር መንገድ ለሁለቱም ወገኖች ሠራተኞች ጊዜያዊ የወሰን ምልክት ሆኖ እንዲቆይና የሁለቱም ወገኖች ሠራተኞች እንዳይተላለፉት ስምምነት ተፈርሞ ስብሰባው ተፈጸመ። ይህ ጊዜያዊ ወሰን ትልቁን ተራራ ደረብሌን ወደ ኢትዮጵያ አስቀርቶ በሥሩ የሚያልፍ ነው። ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያውያኑ ሹማምንት ከአውበባ ሰፈር ተነሥተው ሰተዋ የሚባለውን ወንዝ ተሻግረው እርሻ ባለበት በደበቡር ላይ ሰፈሩ።

ከዚያም ተነሥተው ጉዟቸውን ቀጠሉና የእንግሊዞችን ከተማ ቦረማን በስተምሥራቅ እየተመለከቱ በሰው ጋራ ሥር አልፈው ተፈሪ በር ከተማ ገቡ። እርሱም ባላገሩ አውበሬ እያለ የሚጠራው ነው። ከጎግቲ እስከ አውበሬ (ተፈሪ በር) ርሕቀቱ 70 ኪሎ ሜትር ያህል ነው። ፊታውራሪ ታፈሰ በተፈሪ በር ባላባቶቹን እነ ግራዝማች ዶዲን እያነጋገሩ ጥቂት ቀን ከቆዩ በኋላ ወደ ጅጅጋ ተመልሰዋል። ተፈሪ በር ከጅጅጋ 73 ኪሎ ሜትር ያህል የሚርቅ ነው።

በዚህ ግጭት ምክንያት የተገኘው የምርመራ ውጤት ለወሰን ክልል ሥራ ምክንያት ሆኖ እንዳገለገለ ወደፊት ልንመለከት ነው። እኔም ይህን የግጭት ታሪክ የጻፍሁት ወደፊት ለሚከተለው የወሰን ክልል ሥራ መነሻ የሆነውን ሰበብ በቅድሚያ መግለጽ ጠቃሚ መስሎ ስለታየኝ ነው።

## ስለ ታላላቅ ሰዎች ሞት

በ1922 ዓ.ም. የተሰማው የታላላቅ ሰዎች ሞት ከዚህ በታች እንደተጻፈው ነው።

የኢሉባቦር ገዢ ራስ ናደው አባ ወሎ በኅዳር 2 ቀን 1922 ዓ.ም. በግዛታቸው በጎሬ ከተማ ላይ መሞታቸው ተሰማ። የተቀበሩትም በዚያው ከተማ በምትገኝ በቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ነው። ዐፅማቸውም ከአንድ ዓመት በኋላ ፈልሶ መጥቶ በየካቲት ወር 1923 ዓ.ም. ደብረ ሊባኖስ ተቀብሮአል።

ደጃዝማች ገድሌ በየካቲት 19 ቀን በ64 ዓመት ዕድሜያቸው ሞተው ደብረ ሊባኖስ ተቀበሩ። ስለ ሞታቸውም የካቲት 24 ቀን አዲስ አበባ ጃንሜዳ ላይ ድንኳን ተተክሎ ውሎ ሆኖ ተለቀሰላቸው።

የካቲት 28 ቀን ወይዘሮ ወለተ ዮሐንስ ወልደ ሚካኤል በ75 ዓመት ዕድሜያቸው ሞተው አዲስ አበባ ሥላሴ ተቀበሩ። ወይዘሮ ወለተ ዮሐንስ የልዑል ራስ መኰንን ታናሽ እኅት፣ የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ አክስት ናቸው። የቀብሩም ሥርዓት ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱና

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ባሉበት ጳጳሳትና ሚኒስትሮች መኳንንትና ሠራዊት በተሰበሰቡበት ነጋሪት በሐዘን ምት እየተመታ በታላቅ ክብር ተፈጸመ።

በዚህ ወራት የጦር ሚኒስትሩ ደጃዝማች ሙሉጌታ ከሠራዊት ጋር ወደ ስሜን ዘምተው ደላንታ ላይ ነበሩና የወይዘሮ ወለተ ዮሐንስ የሣልስት ልቅሶ በተለቀሰበት ቀን ግርማዊ ንጉሥ አንድ የማጽናኛ ቃል ለሐዘነተኞቹ እንዲነበብ አደረጉ። ቃሉም ይህ ነው።

> የከበደውን የውነተኛ ሐዘኔንና ጉዳቴን ለመተው ግድ የሆነብኝ ይህ ጊዜ መኳንንቱና ሠራዊቱ ወደ ጦር የወጡበት ጊዜ ነውና ለነርሱ ማሰብና መጨነቅ የተገባ ስለሆነ ነው። ወደማንቀርበት ዓለም ለሄዱት ማዘኑን ታግሣችሁ ከእንግዲህ ወዲህ እሳቸውን በማጣት የተጐዳሁት እኔ ነኝ እንጂ ለእናንተ እኔ በሚቻለኝ አለሁና ስለ መንግሥቱም ስለ እኔም እዘኑልኝ። ይህንን ያሰኘኝ ያለፈው ሐዘን ሳይርቅ ይህንን የተካ ፈጣሪያችን ወደ ብስጭት ቁጥሮ እንዳይቀየመን በመፍራት ነው።

ነጋድራስ ኃይሌ ሹምዬ የወሎ ነጋድራስ ሰኔ 21 ቀን 1922 ዓ.ም. በአርባ ዘጠኝ ዓመት ዕድሜያቸው ሞተው ደሴ መድኃኔ ዓለም ተቀበሩ። ነጋድራስ ኃይሌ በ1900 ዓ.ም. የፍርድ መዝገብ ሥራ በአፈ ንጉሥ ነሲቡና በወምበሮች ችሎት ሲቋቋም የፍርድ ጸሐፊዎች አለቃ ሆነው የሠሩ ናቸው። ከዚያም በኋላ በልዩ በቆመ ፍርድ ቤትና በሌላም ክፍል እየተሾሙ አገልግለዋል። የነጋድራስነት ሹመታቸውም በዚሁ ዓመት በነሐሴ 7 ቀን ለልጃቸው ለልጅ ትርፌ ሹምዬ ተሰጠ።

ወይዘሮ የውብዳር የባለ ፍትሐ ነገሥቱ የአለቃ ገብረ ክርስቶስ[46] ባለቤት ሐምሌ 21 ቀን በእንጦጦ ተራራ ጥግ በበቅሎ ሆነው አንድ ትንሽ ወንዝ ሲሻገሩ ድንገት ደራሽ ጐርፍ ወሰዳቸው። ሬሣቸው ተፈልጎ ባለመገኘቱም ታዘነላቸው። ወይዘሮ የውብዳር የዳግማዊ ምኒልክ ሚስት የነበሩት የወይዘሮ ባፈና የልጅ ልጅ ናቸው።

[46] አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 241 ይመልከቱ። (አሙኀ)

# ምዕራፍ 2

## 1923 ዓመተ ምሕረት

*ስለ ወንጀለኛ መቅጫ ደንብ - ስለ አጼ መስቀል በዓል - ስለ መስቀል በዓል - በሐሰት ወሬ ስለ ደረሰ ቅጣት - በአውሮፕላን ነጂነት ስለተመረቁ ወጣቶች - ስለ ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ባርያ ጋብር ሞት - በከተማ ስለተደረገ ዝግጅት - ለዘውድ በዓል ከያገሩ ስለ መምጣት - የመንግሥት መልእክተኞች መግባት - ከበዓሉ በፊት ስለተፈጸመ ሥነ ሥርዓት በጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ስለተደረገው ዝግጅት - በዘውዱ በዓል ዋዜማ - ስለ ሥርዓተ ንግሥ - ለአልጋ ወራሹ ስለተደረገው ሥነ ሥርዓት - የእቴጌ አነጋገሥ - ስለ ጸሎተ ቅዳሴና ስለ ዑደት - ወደ ቤተ መንግሥት ስለ መመለስ - ስለ ግብሩ ሥርዓት - የመንግሥታት መልእክተኞች መመለስ - የዘውዱ በዓል በያገሩ ስለ መከበሩ - ንጉሠ ነገሥቱ ምሕረት ስለ ማድረጋቸው - ደብረ ሊባኖስን ስለ መሳለም - የጳጳሳት ሀገረ ስብከት ስለ መደልደሉ በጥርና በየካቲት ወር ስለተሰጠ ሹመት -በመስፍኑ መወለድ ስለተደረገ ድግስ - ስለ አዲስ ቀረጥ አዋጅ - ስለ ፋሲካ በዓል - ስለ ሹመት - ስለ ቅብዓ ሜሮን - የትምህርት ቤቶች የሽልማት መስጫ በዓል - ስለ ዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት - ስለ ሕገ መንግሥት - ስለ ግብዣ - የነፋስ ስልክ ቤት እንደ ተመሠረተ - ስለ ልዩ ልዩ ነገር - ስለ ታላላቅ ሰዎች ሞት*

### ስለ ወንጀለኛ መቅጫ ደንብ

1923 ዓ.ም. ዘመነ ሉቃስ ኀሙስ ባተ። በመስከረም 1 ቀን ጧት የበዓል መከፈቻ መድፍ ተተኩሶ በቤተ መንግሥት የአዲሱ ዓመት በዓል እንደ ተለመደው ተከብሮ ዋለ።

በዚህም ዕለት ኘ ደንብ በሚል አርእስት የታተመ አንድ የሕግ መጽሐፍ በንጉሠ ነገሥቱ ተፈቅዶ ወጣ። እስከዚህም ጊዜ ድረስ ወንጀለኛ የሚቀጣው፣ ነፍሰ ገዳይ ሲሆን የግእዙ ፍትሐ ነገሥት በሊቃውንት እየታየ ነበር። ሌላውም ወንጀለኛ በዳኛ አእምሮና በልማዳዊ ሕግ ይፈረድበት ነበር። አሁን ግን ንጉሠ ነገሥቱ የአውሮጳውያንን የሥልጣኔ አኗኗር ስለተመለከቱና ወንጀሉ ወይም ቅጣቱ በደንብ ተገልጾ እንዲደነገግ ስለ ፈለጉ ይህ ደንብ እንዲወጣ አደረጉ። ደንቡ በአምስት ታላላቅ ክፍሎች ተከፍሏል። እያንዳንዱም አንቀጽ በምዕራፎች የተከፈለ ሆኖ 488 ተራ ቍጥሮች ያሉበት ነው። ታትሞ የወጣውም መጽሐፍ ባለ 84 ገጽ ነበር።

ካሁን በፊት በ1919 ዓ.ም. በሰኔ ወር የተቋቋሙት የወንጀል ክፍል ዳኞች ለጊዜው በተሰጣቸው ደንብ እየሠሩ ቆይተው ነበር።

ከዚህ በኋላ ግን አዲሱ የወንጀለኛ መቅጫ ደንብ[47] ስለተሰጣቸውና ሥራው በይበልጥ ስለተቃና ሕዝቡ ንጉሠ ነገሥቱን አመሰገነ።

## ስለ አጼ መስቀል በዓል

የአጼ መስቀል በዓል መስከረም 10 ቀን ቅዳሜ በግርማዊ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ፊት በቤተ መንግሥቱ ተከበረ። በበዓሉ ላይ ሊቀ ጳጳሳቱ አቡነ ቄርሎስና ጳጳሳቱ፣ ልዑል ራስ ሥዩም መንገሻና ልዑል ራስ ጉግሣ አርአያ፣ ልዑል አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ፣ የጦር ሚኒስትሩ ፊታውራሪ ሙሉጌታና ሌሎች መኳንንት ሁሉ ነበሩ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የዲፕሎማቲክን ሰዎች በየተራ ወደ ጃንሆይ እያቀረቡና እጅ እያስነሡ በየማዕረግ ስፍራቸው አስቀመጧቸው።

ከዚያም በኋላ ካህናት የተለመደውን የበዓሉን ጸሎት ጀመሩና መሪዎቹ የመናገሻ ማርቆስ ካህናት እንዲህ ብለው ምስባክ ሰበኩ።

ቅንት ሰይፈከ ኀያል ውስተ ሐቌከ[48]
በሥንከ ወበላህይከ
አርትዕ ተሠራሕ ወንገሥ።

በዚህ ዘመን ንጉሠ ነገሥቱ ዘውድ የሚጭኑ ናቸውና ምስባኩ የሚያሳየው የዘመኑን ታሪክ ነው።

ከዚያም ቀጥሎ ድምፃዊው ካህን ደብተራ ወልደ ማርያም ተቀጸል ጽጌ ኃይለ ሥላሴ ሐጼጌ[49] እያለ ሲያመለጥን የድምፁ ውበት ደስ አሰ። በተጨማሪም የንጉሠ ነገሥቱ ስም በተቀጸል ጽጌ ጊዜ የተጠራበት የመጀመሪያው ቀን ስለሆነ ዜማውን የሰሙ ሁሉ እንኳን ለዚህ ያበቃቸው እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ። የካህናቱ ወረብና ሽብሸባ እንዳበቃ አበባ ታድሎና ሊቀ ጳጳሳቱ አሳርገው የበዓሉ ፍጻሜ ሆነ።

## ስለ መስቀል በዓል

የመስቀል ደመራ በዓል መስከረም 16 ቀን ዓርብ ከእኩለ ቀን በኋላ እንደ ተለመደው በሠራዊት ሰልፍ ተከበረ። ደመራው የቆመው በታላቁ ግቢ አጠገብ ባለው ሜዳ ላይ ነበር።

[47] ይህ ደንብ የካቲት 26 ቀን 1934 ዓ.ም. ለሁለተኛ ጊዜ ታትሞ ወጥቶ ነበር። መጋቢት 17 ቀን 1946 ዓ.ም. በፍትሐ ነገሥትና በኢትዮጵያ የነበሩትን ልማዶችና ባህሎችን መሠረት በማድረግ የወንጀል፣ የፍትሐ ብሔር፣ የንግድና የባሕር ሕጎችን ለማዘጋጀት የፍትሐ ነገሥት አርቃቂ ኮሚሲዮን (ኮዲፊኬሽን ኮሚሲዮን) ሲቋቋም በመጀመሪያ የኮሚሲዮኑ ፕሬዜዳንት የፍርድ ሚኒስትሩ ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ነበሩ። በኋላ ግን የፍርድ ምክትል ሚኒስትሩ ብላታ መርስዔ ኀዘን የኮሚሲዮኑ ሊቀ መንበር ሆኑ። የኮሚሲዮኑም አባላት ሦስት የታወቁ የአውሮጳ የሕግ ፕሮፌሰሮችና የበሰለ የባህልና የሕግ ዕውቀት ያላቸው ኢትዮጵያውያን ነበሩ። የተረቀቁት ሕጎች በፓርላማና በንጉሠ ነገሥቱ ጸድቀው ፍትሐ ብሔር ሕግ በ1952 ዓ.ም.፣ ወንጀለኛ መቅጫም በ1954 ዓ.ም. ሕግ ሆነዋል። እነኚህ ሕጎች እስካሁን ድረስ በመሠረቱ አልተቀየሩም፤ ከአንዳንድ ማሻሻያዎች በስተቀር በኢትዮጵያም በኤርትራም እየተሠራባቸው ናቸው። (አመኀ)

[48] ኃያል ሆይ፣ በቁንጅናህና በውበትህ ሠይፍህን በወገብህ ታጠቅ። ስለ ቅንነትና ስለ የዋህነት ስለ ጽድቅም አቅና ተከናወን ንገሥም። መዝ. 44 ቍ 3-4(አመኀ)

[49] አጼ ኃይለ ሥላሴ ሆይ፣ አበባን ተቀዳጅ። (አመኀ)

ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ጃንሆይ ታጅበው መጥተው ለበዓል ማክበሪያ በተዘጋጀው ድንኳን ውስጥ በወርቅ ወምበር ላይ ተቀመጡ። ሊቀ ጳጳሳቱ፣ መሳፍንቱና መኳንንቱ የዲፕሎማቲክም ሰዎች በቀኝና በግራ በየማዕረጋቸው ተቀመጡ።

ከዚህ በኋላ ካህናቱ የበዓሉን ጸሎት ማድረስ ጀመሩ። በጸሎቱ ፍጻሜ ጃንሆይ ከመኳንንት ጋር ሆነው ደመራውን ሦስት ጊዜ ዞሩትና ተመልሰው በወምበራቸው ሲቀመጡ የሠራዊት ሰልፍ ተጀመረ።

መጀመሪያ የባልደራሶች አለቃ ቀኛዝማች ገብረ ጊዮርጊስ የንጉሠ ነገሥቱን ፈረሶች በጥሩ ዕቃ አስጌጦ እያሳበ ተሰለፈና ከብዙ ጭፍራ ጋር ደመራውን ዞሮ አለፈ። ቀጥሎም የየቤተ ደንቡ ጭፍራ በየአለቃው እየተሰለፈ አምሮ አጌጦ አለፈ። እነርሱም ሠይፈ ጃግሬዎችና የግቢ ሚኒስትሩ የቢትወደድ ወልደ ገብርኤል በሻህ ጭፍሮች፣ የደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ባልደረቦች የሆኑ የቤት አሽከሮች ናቸው።

ከዚያ በኋላ በአውሮጳውያን ሥርዓት ሰልፍ ተምረው የሠለጠኑት የእልፍኝ ዘበኞች እጅግ አምረው ተሰልፈው አለፉ። ቀጥሎም የጦር ሚኒስትሩ የፊታውራሪ ሙሉጌታ አሽከሮች በእንደራሴያቸው መሪነት ተሰልፈው አለፉ። ቀጥሎ የወረገኑ ሹም የግራዝማች ባንት ይዋሉ ጭፍሮችና ዕቃ ቤቶች የሚባሉት የበጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴ ከተማ ጭፍሮች እንዲሁ ደግሞ የፖስታ ሚኒስትሩ የፊታውራሪ ኃይሌ ወልደ ሩፌና የገንዘብ ሚኒስትሩ የበጅሮንድ ዘለቀ፣ የሊጋባ ወዳጄ ጭፍሮች በየክፍላቸው ተሰልፈው አለፉ። የግርማዊት እቴጌ መነን አሽከሮችም በአዛዥ ኃይለ ሥላሴ መገኖ ሥር ሆነው ተሰልፈው አለፉ።

ከዚህ ሁሉ በኋላ ሐረርጌዎች በደጅ አጋፋሪው በአጋፋሪ ከልክሌና በእልፍኝ አስከልካዩ በግራዝማች ዘውዴ አረጋይ እግር ተሰልፈው፣ ግምጃ ቤቶችና የግቢ ሠራተኞች በበጅሮንድ ተሰማ ባንቴና በአዛዥ ይርዳው እግር ተሰልፈው እጅግ አምረው አለፉ። በዚህ አኳኋን ሰልፉ ታይቶ ተፈጸመና ጃንሆይ በ11 ሰዓት ተኩል ወደ ቤተ መንግሥታቸው ተመለሱ።

ከመስቀል በኋላ በቤተ መንግሥት ሹም ሽር ተደርጎ የሚከተለው ሹመት ተሰጠ።

ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ጐሹ አሩሲን፣ ፊታውራሪ ወልደ አማኑኤል ሐዋስ ደጃዝማች ተብለው መርሐ ቤቴንና ጃማን ተሾሙ። አቶ ተሰማ ደባልቄ በልዩ በቆመው ፍርድ ቤት[50] ዳኛ ሆነው ተሾሙ። ይህ ሹመት የነጋድራስ ደስታ ምትኬ የነበረው ነው።

ፊታውራሪ ደቻሳ የመታሰቢያ ቤትን ዘበኝነት፣ ልጅ ግርማ ያየህ ይራድ የእንጨት ጉምሩክን፣[51] ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅ የጨርጨርን ዲሬክተርነት ተሾሙ።

እንዲሁ ደግሞ አቶ ሙሉጌታ የሐረርጌው ቀኛዝማች ተብለው የቡልጋን ምስለኔነት ተሾሙ። ልጅ በልሁ ደገፉና ልጅ ከበደ ተሰማ በያዙት ሥራ ላይ በቤተ መንግሥት ባለው ሠረገላና አቶሞቢል ዲሬክተርነትን ተሾሙ። አቶ ድጋፌ በእቴጌ መነን ቤት ጸሐፌ ትእዛዝነትን ተሾሙ።

[50] በኢትዮጵያና በውጪ አገር ዜጎች መካከል የሚነሣውን የወንጀል ወይም የሀብት ክርክር የሚሰማ። (አመነ)

[51] የደን ሀብትን ለመጠበቅ የምርት ገደብን የሚወስንና ግብር የሚቀበል ድርጅት። ምንጭ- አቶ ኃይለ ማርያም መንገሻ። (አመነ)

## በሐሰት ወሬ ስለ ደረሰ ቅጣት

ማንም ሰው አላፊ ሊሆንበትና ዋቢ ሊያሳልፍ የማይችልበትን ወሬ ከሌላ ሰማሁ ብሎ ወይም ወሬ ፈጥሮ ሲያወራ ቢገኝ ይቀጣል ተብሎ ባለፈው ግንቦት 30 ቀን 1922 ዓ.ም. በወጣው አዋጅ ተነግሮ ነበር።

አሁን በዚህ ዓመትም በመስከረም ወር አቶ ወልደ ጻድቅ አስረስ የተባለ በሥራ ሚኒስቴር ክፍል የመንግሥት ሹም የነበረ ሰው በዓይኑ ያላየውንና ዋቢ ሊያሳልፍ ያልቻለበትን ወሬ ተናግሮ ስለተገኘ ተከሶ ከንጉሣዊ ችሎት ቀርቦ ነበር። በተጠየቀ ጊዜም እነ እገሌ ነገሩኝ ብሎ የሁለት ሰዎችን ስም ጠቅሶ ስለተናገረ ሰዎቹ ተጠርተው ተጠየቁ። እነርሱም ከአንተ ቃል ሰማን እንጂ እኛ አልነገርንህም ብለው ስለ መሰከሩበትና ማስረጃ ስላጣ ከሹመቱ ተሽሮ እንዲታሰር ተፈረደበት። የእርሱ ሹመት የነበረውንም አቶ በቀለ ጐሹ ባላምባራስ ተብለው በመስከረም 15 ቀን ተሾሙ።

እነዚያም መስካሪዎች የሐሰቱን ወሬ ሰምተው ለዳኛ ባለማስታወቃቸው ደግሞም የፍርዱን ፍጻሜ ከመስማታቸው በፊት በአደባባይ ሄደው ስለተገኙ እየተጠሩ ተይዘው እያንዳንዳቸው በ200 ብር መቀጫና በ2 ወር እስራት እንዲቀጡ ተፈረደባቸው።

ተነገረ ስለተባለው የሐሰት ወሬ የነገሩን ዝርዝር የሚያስረዳኝ አላገሁም። የነገሩ ሁናቴና ቅጣቱ ግን መስከረም 8 ቀን 1923 ዓ.ም. ታትሞ በወጣው በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ በሰፊው ስለተገለጸ የዘመኑን ታሪክ ለመንገር ስል ባጭሩ ጽፌአለሁ። በዚያ ዘመን የሐሰት ወሬ አስቸግሮ ስለነበረ ይህ ፍርድ በሰሚዎች ዘንድ አስደሳች ሆኖ ሰነበተ።


## በአውሮፕላን ነጂነት ስለተመረቁ ወጣቶች

አውሮፕላን የመንዳት ትምህርት ተምረው ከኢትዮጵያውያን ወገን ለመጀመሪያ ጊዜ የበራሪ ምስክር ወረቀት የተቀበሉት ሁለት ወጣቶች የነጂነት ችሎታቸውን ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አሳይተው በጥቅምት 3 ቀን ተመረቁ። እነርሱም አስፋው ዓሊና ሚሽካ ባቢቼፍ ናቸው።

ባለፈው ሰኔ አምስት ወጣቶች ከአዲስ አበባ ወደ ጅጅጋ ተልከው በክረምቱ ወራት አስተማሪው ሙሴ ቬርዴር የአውሮፕላን ነጂነትን ትምህርት ሲያስተምራቸውና ሲያሠለጥናቸው ከርመው ነበር። ከተማሪዎቹ መካከል አስፋው ዓሊና ሚሽካ ባቢቼፍ በቶሎ ሠልጥነው ለነጂነት ስለ በቁ ችሎታቸው በአስተማሪውና የመንግሥት ተመልካቾች በሆኑ ሹማምንት ተፈትኖ እንዲረጋገጥ በአገረ ገዥው በኩል ትእዛዝ ተላለፈ። በዚህም መሠረት ሦስት ሹማምንት[52] በመስከረም 14 እና 15 1923 ዓ.ም. ከያንዳንዳቸው ጋራ በየተራ በአየር ላይ በመብረር ፈተና አድርገው ነጂዎቹ ያለ መሪ ወይም ያለ አስተማሪ ብቻቸውን በአየር ላይ ለመብረር፣ በደኅና ለማስነሣትና ለማሳረፍ መቻላቸውን ተመለከቱ። ከዚህም በኋላ ለከተማው ታላላቆች ሁሉ ጥሪ ተደርጎ መስከረም 21 ቀን በአውሮፕላን ሜዳ በዓል ተደረገ። በዚህም ቀን ወጣቶቹ በየተራ አውሮፕላን እያስነሡና እያበረሩ ለሕዝቡ አሳዩና ሻምፓኝ

[52] ሦስቱ ሹማምንት የጅጅጋ ጉምሩክ ሹም ልጅ ተስፋ ያየህ ይራድ፣ የጅጅጋ ማዘጋጃ ቤት ሹም፤ አቶ መዓዛ ወልደ ሕይወትና በጅጅጋ የራስ መኰንን ትምህርት ቤት ሹም የነበሩት የዚህ ታሪክ ጸሐፊ አቶ መርስዔ ኅዘን ወልደ ቂርቆስ ነበሩ። (አመኅ)

ተከፍቶ ተጨበጨበላቸው። በዚህ ጊዜ ፈታኞቹ ሹማምንት የበረራ ምስክር ወረቀት ጽፈውና ፈርመው ስለሰጧቸው ወረቀቱን ይዘው እነርሱ ራሳቸው አውሮፕላን እየነዱ ወደ አዲስ አበባ ወጡ።



አምኃ መርስዔ ኀዘን

የመጀመሪያው የበረራ የምስክር ወረቀት

የወረቀቱ ቃል

እኛ ከዚህ በታች ፊርማችንን የፈረምን ልጅ ተስፋ ያየህ ይራድ አቶ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ አቶ መዓዛ ወልደ ሕይወት የአውሮፕላን ተማሪዎች አስፋው ዓሊና ሚሽካ ባቢቼፍ ትምህርታቸውን ጨርሰው ፈተና ባደረጉበት በመስከረም 14፣ 15 ቀን 1923 ዓ.ም. በክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ ቃል የመንግሥት ተመልካቾች ሆነን ሄደን፣ አስተማሪያቸው ሙሴ ቤዴል የሰጡዋቸውን ፈተና ሁሉ በያይነቱ መፈጸማቸውን አይተናል። እኛም እራሳችን እያንዳንዳችን ከያንዳንዳቸው ጋራ ወደ አየር ወጥተን ባመለከትናቸው አኳያ ሁሉ በደኅና እየሄዱ ማብረራቸውንና ሲያስነሡም ሲያሳርፉም ያለ አንዳች ችግር ለመሥራት መቻላቸውን እንመሰክራለን። መስከረም 21 ቀን 1923 ዓመት ጅጅጋ።

የሚል ሆኖ ሦስቱም የመንግሥት ተመልካቾች ፈርሙውበታል።

አዲስ አበባ ከደረሱ በኋላ የነጂነት ችሎታቸውን በሥራ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አሳዩና የኒሻን ሽልማት ተሸለሙ። የተሰጣቸው የበረራ የምስክርነት ወረቀትም በግርማዊነታቸው ታይቶ ስለ ጸደቀ የአውሮፕላን ነጂነት ተቀዳሚዎች እየተባሉ ተመሰገኑ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትም የነጂነት ችሎታቸውን አይተው ከተረዱ በኋላ በወረቀቱ እግርጌ የሚከተለውን ቃል በመጻፍ አረጋገጡላቸው።

አስፋውና ሚሽካ ባቢቼፍ በኢትዮጵያ መጀመሪያ የአይሮፕላን መንዳት ስለተማሩ ፈተናቸውን ፈጽመው መንዳታቸውን አይተናልና ለዚህም ዕውቀት ተቀዳሚ በመሆናቸው ምስጋና ይገባቸዋል።

ጥቅምት 3 ቀን 1923 ዓ.ም　　ቀ. ኃይለ ሥላሴ ን. ነ.

በተጨማሪም ልዑል አስፋ ወሰንና ልዑል መኰንን፣ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴና አስተማሪዎቹ ፈርመውበት ለነጂዎቹ ተሰጣቸው።

እንዲሁ ደግሞ ካፕቴን ዊድሜር የተባለ ፈረንሳዊ ባለፈው ክረምት በጅጅጋ ከተማ ያስተማራቸውና ያሠለጠናቸው የጦር መኰንኖች በመስከረም መጨረሻ ወደ አዲስ አበባ ተመለሱና ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፊት በሰልፍ ቀርበው ሰላምታ ሰጡ። እነዚህ መኰንኖች ለዘውድ በዓል ከብር ከውጭ አገር የሚመጡትን የመንግሥት መልእክተኞች በሚገባ ለመቀበልና የበዓሉን ሥነ ሥርዓት ለማስከበር በሚገባ የሠለጠኑ ስለሆኑ ወዲያው በየተመደበው ሥራ ተሰማርተው ይሠሩ ጀመር።

## ስለ ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ባርያ ጋብር ሞት

ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ባርያ ጋብር በ57 ዓመት ዕድሜያቸው ሞተው አዲስ አበባ ሥላሴ ተቀበሩ። ስለ እርሳቸው የሰማሁትንም በሚከተለው እገልጻለሁ።

ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ የተወለዱት ጥቅምት 14 ቀን 1866 ዓ.ም. ነው። የ16 ዓመት ወጣት ሳሉ በ1881 ዓ.ም. ታላቅ ወንድማቸው ፊታውራሪ ደባልቀው ወደ ምጽዋ ሰደዋቸው እዚያው የኢጣልያ ቋንቋ ተማሩ። ወደ ሀገራቸው ወደ ትግሬ ተመልሰው ከአጎታቸው ከራስ አሉላ ጋራ ተቀምጠው ሳሉ ራስ አሉላ የደጃዝማችነት ማዕረግ ሰጥተው ሾሟቸው። ራስ አሉላ ከሞቱ በኋላም እዚያው ትግሬ ላይ ሳሉ ልዑል ራስ መኰንን የትግሬ ግዛት ተሰጥቷቸው በ1891 ዓ.ም. ትግሬ በገቡ ጊዜ ስላገኟቸውና ብልህነታቸውን ስለተመለከቱ በተከዜና በመረብ መካከል ያለውን አገር በጠባቂነት እንዲያስተዳድሩ አደረጓቸው። ቀጥሎም ለዳግማዊ ምኒልክ ስላስታወቁላቸው በ1892 ዓ.ም. ወደ ሸዋ መጥተው በአዲስ ዓለም ከተማ ከንጉሠ ነገሥቱ ከዳግማዊ ምኒልክ ጋር ተገናኙ። ንጉሠ ነገሥቱም ብልህነታቸውን አይተው ስለ ወደዱዋቸው በአድዋና በአክሱም ሾሟቸው። ባለሚል ስላደረጓቸው በ1896 ዓ.ም. በሰኔ ወር የንጉሥ ሣህለ ሥላሴን ተወላጅ ወይዘሮ አማረችን ዳሩላቸው፣ ማዕረጋቸውም እያደገ ሄደ። የአክሱም ገዥ በነበሩበትም ዘመን ፕሮፌሰር ኢኖ ሊትማን የተባለ የጀርመን ሊቅ በ1897 ዓ.ም. ወደ አክሱም መጥቶ ነበርና የታሪክ ምርመራ ሲያደርግ በሐውልቶች ላይ የተጻፉ የታሪክ ነገሮችንና የቀዳማዊ ምኒልክ አጽም መገቱን ለዳግማዊ ምኒልክ ስላስታወቁ ሽልማትና ምስጋና ተቀበሉ።

ዳግማዊ ምኒልክ ታመው ከቤት በዋሉበት ጊዜ ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ በአዲስ አበባ ነበሩና መሃል ሰፋሪ የሚባለው የመንግሥት ጭፍራ በ1902 ዓ.ም. በእቴጌ ጣይቱ ላይ የአድማ ጉባዔ ከፍቶ ሲነጋገር ሳለ ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ከመሃል ሰፋሪ ጋራ በመተባበር እንደ አፈ ጉባዔ ሆነው ይታዩ ነበር።[53] ከዚያም በኋላ በግዛታቸው በአድዋና በአክሱም ሳሉ ዳግማዊ ምኒልክ በዐረፉበት ዘመን አቤቶ ኢያሱ ወደ አዲስ አበባ ቢጠሩዋቸው ምክንያት በመስጠት የማይመጡ ሆኑ። ደግሞም ከኢጣልያኖች ሦስት ሺህ ወጨፎ[54] ጠበንጃ ተቀብለው ለውጊያ ይሰናዳሉ ተብሎ ስለተወራባቸው የመንግሥት ፈቃደኞች የሆኑት የአጋሜው

[53] መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ይመልከቱ። (አሙኀ)

[54] በኢጣልያንኛ Vetterli። በአንደኛው የዓለም ጦርነት የኢጣልያ እግረኛ ሠራዊት መደበኛ መሣሪያ። (አሙኀ)

ገዥ ራስ ስብሐትና የመቀሌው ገዥ ደጃዝማች ሥዩም መንገሻ እንዲጠባበቋቸው የአቤቶ ኢያሱ ትእዛዝ ተላለፈ።



ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ባርያ ጋብር

ነገሩ በዚህ ሁናቴ ሳለ የካቲት 18 ቀን 1906 ዓ.ም. ከራስ ስብሐት ጋር በድንገት አምባጓሮ ስለተጋጠሙ አኾራ ላይ ውጊያ ተደረገ። በውጊያው ራስ ስብሐት ከሁለት ልጆቻቸው ጋር ሞቱና በሁለቱም ወገን ሠራዊት አልቆ ድሉ ለደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ሆነ። ዳሩ ግን ደጃዝማች ሥዩም መንገሻ ከመቀሌ ገሥግሠው እንደገና ጦርነት ስለገጠሟቸውና ድል ስላደረጓቸው የመረብን ወንዝ ተሻግረው ወደ ኢጣልያ ግዛት ገብተው ረጋይሌ በተባለ ስፍራ ይኖሩ ጀመር።

አቤቶ ኢያሱ ከመንግሥት ከተሻሩ በኋላ በኢትዮጵያ ዙፋን የተተኩት ግርማዊት ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱና ልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኰንን ምሕረት አድርገውላቸው በ1909 ዓ.ም. ተመልሰው በሚያዝያ ወር አዲስ አበባ ገቡ። ጥቂት ወራት በደጅ ጥናት ከቆዩ በኋላም ወደ ቀድሞው ማዕረጋቸው ተመልሰውና ሜጫን ተሾመው በባለሚልነት የሚኖሩ ሆኑ።

አቤቶ ኢያሱ በ1913 ዓ.ም. ትግሬ ላይ ተይዘው ወደ አዲስ አበባ በመጡበት ጊዜ የአድዋ ግዛት ለደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ተሰጣቸው። የቤተ መንግሥት ማዕረጋቸውና ባላሚልነታቸውም ከቀድሞው የበለጠ ሆነ። የትግሬውን መስፍን የራስ ሥዩም መንገሻን ልጅ ወይዘሮ ወለተ እስራኤልንም በሕግ አገቡ።

ከዚህም በኋላ በ1919 ዓ.ም. ሰኔ 24 እጃቸው ተይዞ በግዞት ስፍራ ተቀመጡ። ስለተጋዙበት ምክንያት በግልጽ የተነገረ አልነበረም። ሆኖም የአልጋ ወራሹን ሥልጣን

በመቃወም በነገር ውስጥ መግባታቸው ስለተሰማባቸው ነው እየተባለ ተወርቶ ነበር። ጥቂት ቀን እጃቸውን ተይዘው ከቆዩ በኋላ በግዛታቸው በሜጫ ላይ እንዲቀመጡ ስለተወሰነ ወደዚያ ሄደው በግዞት ተቀመጡ። በዚያም አንድ ዓመት ከስድስት ወር ከቆዩ በኋላ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ምሕረት አድርገውላቸው ተመለሱና ኅዳር 28 ቀን 1921 ዓ.ም. አዲስ አበባ ገብተው በማዕረግ ይኖሩ ጀመር።

በዚሁም ጊዜ እንደ ቁርጥማት ያለ ሕመም ስላደረባቸው በሐኪም ምክር ወደ ሙቀት ስፍራ እየሄዱ ተቀምጠው ነበር። ይሁን እንጂ ሕመሙ ስላልተሻላቸው ጠበል ለመጠመቅ ወደ ሚጣቅ አማኑኤል ሄደው ነበር። እዚያው እንዳሉ ጥቅምት 2 ቀን 1923 ዓ.ም. ዐረፉ። ሬሣቸውም ወደ አዲስ አበባ ተወስዶ ጥቅምት 6 ቀን በመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ። የቀብሩም ሥነ ሥርዓት ግርማዊ ጃንሆይና ግርማዊት እቴጌ ባሉበት ጳጳሳትና መሳፍንት፣ ሚኒስትሮችና መኳንንት በተሰበሰቡበት በታላቅ ክብር ተፈጸመ።

## በከተማ ስለተደረገ ዝግጅት

የከተማው ዋና ዋና መንገድ ከዘውዱ በዓል ከሦስት ወር በፊት ጀምሮ በጥሩ ድንጋይ ሲደለደልና በአስፋልት ሲዘጋጅ ከረመ። ይኸውም ከላጋር አንሥቶ እስከ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ከዚያም እስከ ታላቁ ቤተ መንግሥትና እስከ አልጋ ወራሹ ቤት ድረስ ያለው መንገድ ነው። በየመንገዱም ዳር የስሚንቶ ምሰሶ እየተተከለ ሽቦ ተዘረጋበትና በኤሌክትሪክ መብራት እንዲደምቅ ተደረገ። ይህን ሥራ ለማስፈጸም የታዘዙት ሊጋባ ወዳጄና ከንቲባ ነሲቡ ዛማኔል ሥራውን ሲከታተሉ ስለ ከረሙ በትጋታቸው ተመሰገኑ።

እንዲሁ ደግሞ ከንቲባ ነሲቡ በዘውዱ በዓል ቀን ተመልካቾች በመንገድ ዳር ተቀምጠው ለማየት የሚችሉበትን ስፍራ አዘጋጅተው ነበርና ከበዓሉ ከአንድ ወር በፊት የሚከተለውን ማስታወቂያ አወጡ።

ማስታወቂያ

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘውድ የሚጭኑት ጥቅምት 23 ቀን 1923 ዓ.ም. በዚሁ ቀን ዘውድ ጭነው ከቤተ ክርስቲያን ወደ ቤተ መንግሥት ሲመለሱ በየመንገድ ዳር በተዘጋጀው ስፍራ ተቀምጦ ለማየት የሚፈልግ ሰው ከጥቅምት 1 ቀን ጀምሮ የፈቃድ ወረቀት ከማዘጋጃ ቤት ለማግኘት ይችላል። ለማየትም የተዘጋጀው ስፍራ ሦስት ማዕረግ አለው።

መጀመሪያው ማዕረግ አሥር ብር ይከፈልበታል

ሁለተኛው ማዕረግ አምስት ብር ይከፈልበታል

ሦስተኛው ማዕረግ ሁለት ብር ተኩል ይከፈልበታል።

መስከረም 20 ቀን 1923 ዓ.ም. ያዲስ አበባ ከንቲባ።



ለበዓሉ የተዘጋጀ ቅስት

## ለዘውድ በዓል ከያገሩ ስለ መምጣት

መኳንንት የዘውዱን በዓል ለማክበር ይመጡ ዘንድ ከንጉሠ ነገሥቱ እያስፈቀዱ በየጊዜው ከውጭ አገርና ከአገር ውስጥ መምጣት ጀመሩ።

በውጭ አገር በትምህርት ላይ የነበሩት

ልዕልት ፀሐይ ኃይለ ሥላሴ፤
ወይዘሪት የምሥራች እምሩ፤
ወይዘሪት አምሳለ ኅሩይ፤
ደጃዝማች ጌታቸው አባተና[55]
ልጅ መልአኩ በያን[56]

ከአውሮጳና ከአሜሪካ መጥተው ጥቅምት 10 ቀን አዲስ አበባ ገቡ።

ከአገር ውስጥም ከዚህ በታች የተጻፉት መኳንንት ከጥቅምት 5 ቀን ጀምሮ በየጊዜው አዲስ አበባ ገብተው ነበር።

ዋግ ሹም ከበደ ተፈሪ[57] የዋግ ገዥ፤

ደጃዝማች ብሩ ወልደ ገብርኤል[58] የሲዳሞ ገዥ፤

---

[55] አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 243 ይመልከቱ። (አመጎ)

[56] አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 220 ይመልከቱ። (አመጎ)

[57] አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 235 ይመልከቱ። (አመጎ)

[58] አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 227 ይመልከቱ። (አመጎ)

ደጃዝማች መኰንን ወሰኔ የወለጋ ቄለም ገዥ፤

ደጃዝማች ሀብተ ሚካኤል ይናዱ የሊሙ ገዥ፤

ደጃዝማች እምሩ ኃይለ ሥላሴ የወሎ እንደራሴ፤

ደጃዝማች አበበ ዳምጠው፤[59]

ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ገብረ እግዚአብሔር[60] የወለጋ ለቀምት ገዥ፤

ሊቀ መኳስ መኰንን ዋልቴ፤

ደጃዝማች አምባቸው ገሠሠ የዋድላና ደላንታ ገዥ፤

የጅማ አባ ጅፋር[61] ዋነኛው ልጅ አባ ዱላ፤

እነዚህና እነዚህን የመሰለ ሁሉ ናቸው።

## የመንግሥት መልእክተኞች መግባት

ለዘውድ በዓል ጥሪ የተደረገላቸው የውጭ አገር መንግሥታት መልእክተኞች ከጥቅምት 11 ቀን አንሥቶ በየቀኑ ወደ አዲስ አበባ መግባት ጀመሩ። እንግዶቹን በባቡር ማረፊያ እየጠበቁ እንዲቀበሉ የሚከተሉት የኢትዮጵያ መኳንንት ታዘዙ።

ልዑል አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ፤

ልዑል ራስ ጉግሣ አርአያ፣ የትግሬ ገዥ፤

ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ጐሹ፣ ያገር ግዛት ሚኒስትር፤

ደጃዝማች መኰንን ደምሰው፣ የወለጋ አርጆ ገዥ፤

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር፤

አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የክፍል ሹም፤

አቶ ተስፋዬ ተገኝ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የክፍል ሹም።

እነዚህና ሌሎችም ናቸው።

ከቤልጅግ የመጡት ሰልፍ አስተማሪዎች እነ ማጆር ፖሌ ያሠለጠኑዋቸውም የክብር ዘበኛ ወታደሮች የአንበሳ ጋማ ያለበትን መለዮ በየራሳቸው አድርገው ሠይፋቸውን መዝዘው በቀኝና በግራ ተሰልፈው ሰላምታ እየሰጡና በሻለቃቸው በባላምባራስ መኩሪያ ባንትይርጉ እየተመሩ አቀባበሉን ሲያከናውኑ ሰነበቱ። ከስዊስ የመጣው ሙዚቃ አስተማሪ ሙሴ ኒኮ ያሠለጠናቸውም የሼኽ ሆጀሌ[62] ወጣቶች የየመንግሥታቱን ማርሽ በሙዚቃ እየነፉ ሥራቸውን አከናወኑ።

59 አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 233 ይመልከቱ። (አሙኀ)

60 አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 219 ይመልከቱ። (አሙኀ)

61 አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 233 ይመልከቱ። (አሙኀ)

62 አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 219 ይመልከቱ። (አሙኀ)

መኳንንቱ እንግዶቹን በባቡር ማረፊያ ላይ ከተቀበሉ በኋላ ከያንዳንድ እንግዳ ጋር በአቶሞቢል ተቀምጦ መጓዝና ወደ ተሰናዳው ስፍራ ማድረስ ቀጥሎም በቀጠሮ ቀን ወደ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ወስዶ ማገናኘትና መንከባከብ ተግባራቸው ነበር።

እያንዳንዱም መልእክተኛ ከንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀርቦ ሲገናኝ የመልእክቱን ወረቀትና ለግርማዊነታቸው የተላከውን ገጸ በረከት ያስረክብ ነበር። በዚህም ጊዜ ለያንዳንዱ መልእክተኛ ክብር 13፣ 13 መድፍ ሲተኰስ ሰነበተ።

የመልእክተኞቹም ስም የሚከተለው ነው።

- የእንግሊዝ ንጉሥ መልእክተኛ፤ ልዑል ዱክ ኦፍ ግሎስተር (የእንግሊዝ ንጉሥ ልጅ) ከ6 ምክትል መልእክተኞች ጋር።
- የዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ፕሬዜዳንት መልእክተኞች፤ ክቡር ሀ መሪ ጃኮቢ። ልዩ አምባሳደር ከ2 ምክትል መልእክተኞች ጋር።
- የጃፓን ንጉሥ ነገሥት መልእክተኛ፤ ክቡር ሙሴ ኢዛቡሮ ዮሺዳ። ልዩ አምባሳደር ከአንድ ምክትል መልእክተኛ ጋር።
- የሆላንድ ንግሥት መልእክተኛ፤ ክቡር ዮንሄር ሀ መ ቫን ሔርስማድ ልዩ አምባሳደር ከሁለት ምክትል መልእክተኞች ጋር።
- የኢጣልያ ንጉሥ መልእክተኛ፤ ልዑል ፌርዲናንዶ የሳቮያና ጀኖቫ፣ የኡዲኒ ፕሪንስ ከዘጠኝ ምክትል መልእክተኞች ጋር።
- የፈረንሳዊ ሬፑብሊክ ፕሬዜዳንት መልእክተኛ፤ ክቡር ማርሻል ፍራንሼ ዲስፔሬ ከአንድ ኤድ ደካምፕና ከሁለት መልእክተኞች ጋር።
- የግሪክ ሬፑብሊክ ፕሬዜዳንት መልእክተኛ፤ ክቡር ኮንት ፔ ሜታክሳስ ልዩ አምባሳደር ከአንድ ምክትል መልእክተኛ ጋር።
- የስዊድን ንጉሥ መልእክተኛ፤ ክቡር ሆክ አሮልድ ደቤልት። ልዩ አምባሳደር ከ2 ምክትል መልእክተኞች ጋር።
- የጀርመን ሬፑብሊክ ፕሬዜዳንት መልእክተኛ፤ ክቡር ባሮን ቮን ባልትሐውዘን ልዩ አምባሳደር ከአንድ ምክትል መልእክተኛ ጋር።
- የቤልጅግ ንጉሥ መልእክተኛ፤ ክቡር ሙሴ ማክሲሞ ዤራር ልዩ አምባሳደር።
- የግብጽ ንጉሥ መልእክተኛ፤ ክቡር ሞሐመድ ቶፊክ ነሲም ፓሻ። ልዩ አምባሳደር ከ4 ምክትል መልእክተኞች ጋር።
- የእስክንድርያ ፓትረያርክ አቡነ ዮሐንስ መልእክተኛ፤ የጊርጋ ጳጳስ አቡነ ዮሳብና የመጅሊስ ሚሊ[63] ወኪል ቆሞስ ጊዮርጊስ።

ከነዚህ ከተጻፉት የመንግሥት መልእክተኞች መካከል ክቡር ማርሻል ፍራንሼ ዲስፔሬ በጥቅምት 17 ቀን ሲገቡ፣ እንዲሁ ደግሞ ልዑል ዱክ ኦፍ ግሎስተር በጥቅምት 18

[63] በግብጽ ቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን በተካሄደው የህዳሴ እንቅሳቀሴ መሠረት በጥር 29 ቀን 1866 ዓ. ም. የተቋቋመ የምዕመናን ጉባኤ። ጉባኤው የቤተ ክርስቲያኑን ንብረት በበላይነት ለመቆጣጠርና ለሕዝበ ክርስቲያኑ ማኅበራዊ ጉዳዮች ኃላፊነት አለው። (አመኀ)

ቀን ሲገቡ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከመሳፍንትና ከመኳንንት ጋር በላጋር ጠብቀው በልዩ ክብር ተቀበሏቸው። አብረዋቸው የነበሩትም መሳፍንት የሚከተሉት ናቸው።

ልዑል ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት
ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ
ልዑል ራስ ሥዩም መንገሻ
ልዑል ራስ ጉግሣ አርአያ
ልዑል አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ
ፊታውራሪ ሙሉጌታ ይገዙ
ደጃዝማች ብሩ ወልደ ገብርኤል
ቢትወደድ ወልደ ገብርኤል በሻህ
ቢትወደድ ጌታቸው አባተ
ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ጐሹ
ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ዓባይነህ[64]
ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው
ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ መስቀል ታሪኩ
ጸሐፌ ትእዛዝ አፈ ወርቅ ወልደ ማርያም
አፈ ንጉሥ አረጋይ ቢቸሬ
ደጃዝማች መኰንን ወሰኔ
ደጃዝማች አደፍርሰው ይናዱ
ከንቲባ ነሲቡ ዛማኔል
ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ
ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል
ፊታውራሪ ጣሰው ዋለሉ
ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ዓባይነህ[62]
ግራዝማች ኃይለ ማርያም ገሠሠ

እንግዶቹ ከባቡር ወርደው ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ጋር ከተገናኙ በኋላ ከመሳፍንቱና ከመኳንንቱም ጋር እየተገናኙ ተዋወቁ። የመተዋወቁ ሥነ ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ ክቡር ማርሻል ፍራንሼ ከልዑል ራስ ሥዩም ጋር በአንድ አቶሞቢል ተቀምጠው ወደ ተሰናዳላቸው ማረፊያ ሄዱ።

ልዑል ዱክ ኦፍ ግሎስተርም ከልዑል ራስ ካሣ ጋር በአንድ አቶሞቢል ተቀምጠውና በፈረሰኞች ታጅበው ወደ ተዘጋጀላቸው ስፍራ ሄዱ።

---

64 አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 230 ይመልከቱ። (አሙኅ)



የክብር አጃቢዎች ልዑል ራስ ካሣ (ግራ) ልዑል ራስ ሥዩም (ቀኝ)



ልዑል ራስ ሥዩም (ግራ) እና ልዑል ራስ ካሣ ከዱክ ኦፍ ግሎስተር ጋር



ሙዚቀኞች ከመሪያቸው ከአባ ቆሮ ጋር



እንግዶቹን ተቀባይ የክብር ዘብ



ዱክ ኦፍ ግሎስተርን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ባቡር ጣቢያ ሲቀበሏቸው



ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የፈረንሳዩን ማርሻል ፍራንሼን ሲቀበሉ



ልዑል መኰንን የጃፓኑን መልእክተኛ ሲቀበሉ



የስዊድን መልእክተኞች

## ከበዓሉ በፊት ስለተፈጸመ ሥነ ሥርዓት

የንጉሠ ነገሥቱና የእቴጌይቱ ሥርዓተ ንግሥ የሚፈጸምባቸው ንዋያተ ንግሥ በጥቅምት መባቻ ላይ በቤተ መንግሥቱ አጠገብ ወደሚገኘው ወደ በዓታ ቤተ ክርስቲያን ተወስደው በጠረጴዛ ላይ ተደረደሩና ሁለት ሱባኤ ሙሉ ቅዳሴ እየተቀደሰና ምህላ እየተደረሰ ጳጳሳትና ቀሳውስት ሲጸልዩባቸው ሰነበቱ።

ለበዓሉ ሰባት ቀን ሲቀረውም የገንዘብ ሚኒስትሩ በጅሮንድ ዘለቀ አግደው የንጉሠ ነገሥቱንና የእቴጌይቱን ዘውድና ሌሎቹንም ንዋያተ ንግሥ ከበዓታ አስነሥተው፣ በሠረገላ አድርገውና በክብር ዘበኛ ጭፍራ ታጅበው ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሄዱ። ከቤተ ክርስቲያን ሲደርሱ ሊቀ ካህናቱ መልአከ ገነት ወልደ ሐና ካህናቱን ሰብስበው ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ[65] እያሉ እየዘመሩ ተቀበሏቸው። ከዚያም በኋላ የተመረጡ ቀሳውስት ንዋያተ ንግሡን ከበጅሮንድ ተቀብለው ወደ ቤተ መቅደስ አስገቡና በጠረጴዛ ላይ ደረደሩዋቸው።

የዕቃዎቹም ዝርዝር የሚከተለው ነው።

የንጉሠ ነገሥቱ ንዋያተ ንግሥ

- ዘውድ
- ሉል
- ልብሰ መንግሥት
- በትረ መንግሥት
- ባለ አልማዝ ቀለበት (ሕለተ ወርቅ)
- ሁለት ባለወርቅ ጦር
- ሰገባው በወርቅና በአልማዝ ያጌጠ ሠይፍ።
- በወርቅ ያጌጠ መጽሐፍ ቅዱስ

የእቴጌይቱ ንዋያተ ንግሥ

- ዘውድ
- ልብሰ መንግሥት
- ባለ አልማዝ ቀለበት

ቅብዓ ቅዱስም ከንዋያተ ንግሥ ጋራ በጠረጴዛው ላይ ተቀመጠ። ከዚህ በኋላ የተመረጡ 49 መነኰሳት በሰባት በሰባት ክፍል ተከፍለው በየቀኑ 49 መዝሙረ ዳዊት እየደገሙና በእግዚኦ ምህላ እያደረሱ ሱባኤውን ሙሉ ጸለዩበት። በየዕለቱም ቅዳሴ ሲቀደስበት ሰነበተ። የጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን እስከዛሬ ድረስ አራዳ ጊዮርጊስ በመባል ታውቆ ይኖር ነበር። ከዚህ ቀን በኋላ ግን መናገሻ ጊዮርጊስ የሚል የመጠሪያ ስም ተሰጠው። ምክንያቱም ከ14 ዓመት በፊት ንግሥት ዘውዲቱ ነግሠውበት ስለነበረና አሁን ደግሞ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንገሻ ለመሆን ዕድልን ስለአገኘ ነው።

---

[65] ምስጉን ሆኖ የተመሰገነ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን። (አመኀ)

## በጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ስለተደረገው ዝግጅት

የዘውድ በዓል የሚፈጸምበት የጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በአበባና በልዩ ልዩ ጌጥ ተጌጦ በኤሌክትሪክም መብራት አሸብርቆ ተዘጋጀ። ከቅኔ ማኅሌት በስተምዕራብ በኩል ክብረ በዓል የሚፈጽምበት ታላቅ አዳራሽ በብረት ቀስት ተገጣጥሞ ተዘጋጀ። ውስጡም በሰንደቅ ዓላማና በኤሌክትሪክ መብራት አጌጠ። በአዳራሹ አጠገብ በስተግራ በኩል ለማረፊያ የሚሆን ትልቅ ድንኳን ተተከለ።

አዳራሹና መቅደሱ በትይዩ እንዲገኝ ለማድረግ ሲባል በቅኔ ማኅሌት መካከል አዲስ በር ተከፈተ። በአዳራሹም ራስጌ የቅዳሴ መቀደሻ መንበር ተሰናዳ። በመንበሩ ፊት የንዋያተ ንግሥ መደርደሪያ ጠረጴዛ ተደረገ። ሥርዓተ ንግሡን ለማድረስ ባለወጎች የሆኑት ጳጳሳትና መምህራንና ሊቃውንትና መዘምራን የሚቆሙበት በጠረጴዛው አጠገብ ያለው ወለል ልዩ ልዩ ኅብር ምንጣፍ ተነጠፈበት።

ንጉሠ ነገሥቱ የሚቀመጡበት ዙፋናዊ ወምበር በአዳራሹ መካከል ተቀመጠ። በቀኙና በግራው ጳጳሳትና የመንግሥታት መልእክተኞች መሳፍንትና መኳንንት የሚቀመጡባቸው ወምበሮች በየደረጃው ተመድበው ተዘጋጁ።

## በዘውዱ በዓል ዋዜማ

በዘውዱ በዓል ዋዜማ ጥቅምት 22 ቀን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ለመሳፍንትና ለመኳንንት ለሹማምንትና ለሊቃውንት ልዩ ልዩ ሽልማት ሰጡ።

እንዲሁም ደግሞ በዚሁ ቀን በአራዳ ላይ በቤተ ክርስቲያን አጠገብ የቆመውን የዳግማዊ ምኒልክ ሐውልት መሳፍንትና መኳንንት በተሰበሰቡትና ከየመንግሥታት የመጡትም መልእክተኞች ባሉበት ላይ መርቀው ገለጡ። የዚህ ሐውልት ሥራ ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ በሕይወት ሳሉ ተጀምሮ እየተሠራ ቆይቶ ነበር።

አሁን ሥራው ስለተፈጸመ እነሆ ተመረቀ። በምረቃውም ላይ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ።

*ልዑላን የኢትዮጵያና የውጭ አገር መሳፍንቶችና መኳንንቶች ሆይ*

*የታላቁ ንጉሥ ዘዳግማዊ ምኒልክ ሐውልት የቆመበት ይህ ቀን ለሙሉ ኢትዮጵያ ሕዝብ የደስታ ቀን መሆኑን ማንም አይዘነጋውም። ሰው በዚህ ዓለም ሲኖር ድካሙ እጅግ ብዙ ነው።*

*ነገር ግን ደግሞ በሠራው ሥራ ለስሙ መልካም መታሰቢያ ትቶ ከመሄዱ በቀር ሌላ የሚበልጥ ነገር የለምና ዛሬ ይህ ሐውልት መቆሙ አጼ ምኒልክ የድካማቸውን ዋጋ ለማግኘት የሚገባቸው እጅግ የታደሉ መሆናቸውን ያስረዳናል።*

*አጼ ምኒልክ ከቀድሞ ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው በነጋሢ ተወላጅነታቸው ምንም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቢሆኑ በዚህም ላይ ዕድለኛ ነበሩና በአባታቸው በአጼ ልብነ ድንግል ዘመን በግራኝ አሕመድ ጦርነት የተለያዩትንና የተከፋፈሉትን የኢትዮጵያ አውራጃች አጼ ቴዎድሮስና*

*አጼ ዮሐንስ የጀመሩትን የመሠረቱትን ተከትለው አንድ ለማድረግ በየጊዜው ጦርነት ያደርጉ እንደ ነበረ የኢትዮጵያ አርበኞች ሁላችሁም የምታውቁት ነው።*

*በዚሁም ሁሉ ድካማቸው እግዚአብሔር ስለረዳቸውና ኢትዮጵያን አንድ ስላደረጉ ስማቸው በዓለም ላይ የታወቀ ሆነ። የኢትዮጵያንም አንድነት ካደላደሉና ካፀኑ በኋላ ከውጭ አገር መንግሥታት ጋር የሚያገናኝ የወዳጅነት ሥራ ለመሥራት ጀመሩ።*

*ኢትዮጵያ ከዓለም መንግሥታት ጋር ተዛመደች። ሕዝባቸውም ወደ ሥልጣኔ ደረጃ እንዲራመድ አደረጉ። ዕድለኛም ከመሆናቸው የተነሣ ዘመናቸው ዘመነ ሰላም ስለሆነ ገበሬ በማረሱ፣ ነጋዴ በመነገዱ ወደ ትልቅ ብልጥግና እንዲደርስ አደረጉ። አጼ ምኒልክ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው የሠሩትን መልካም ሥራ ታሪካቸው ይቊጠረው እንጂ አሁን ጨርሰን ለመናገር ጊዜ አናገኝም።*

*ነገር ግን በዚህ ዓለም የሚኖር ሰው ምንም ዐዋቂና ትጉህ ቢሆን ከሞት ለማምለጥ የሚችል የለምና ለኢትዮጵያ ስፋት፣ ለሕዝባቸው ልማት የሚሆነውን ሥራ እስከሚቻላቸው ከሠሩ በኋላ በታኅሣሥ 3 ቀን 1906 ዓመተ ምሕረት ከዚህ ከምድራዊ ዓለም ወደ ሰማያዊ ዓለም አለፉ።*

*ሰው ፍጡር ስለሆነ ከዚህ የበለጠ ለማድረግ አይቻልምና ነው እንጂ፤ አጼ ምኒልክ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው የሠሩትን መልካም ሥራ ሁሉ ስናመዛዝነው ይህ ሐውልት ዋጋቸው ለመሆን አይበቃም።*

*በኢትዮጵያ በቀድሞ ዘመን ለመንግሥታቸው መልካም ሥራ የሠሩ ብዙ ነገሥታት ነበሩ። ነገር ግን ሐውልት የቆመለት አንድ ንጉሥ እንኳ መኖሩን አልሰማንም።*

*አሁን ግን አጼ ምኒልክ ከውጭ አገር መንግሥቶች የሚያገናኝ ሥራ ጀምረው ስለ አቆዩን፣ መልካም ለሠሩ ነገሥታት ሐውልት ማቆም የሚገባ መሆኑን ስላወቅን በዚህ ሐውልት ሥራቸው ተመሰከረላቸው ለማለት እንችላለን።*

*ከሁሉም ይልቅ አጼ ምኒልክ ከውጭ አገር መንግሥቶች ጋር የወዳጅነት መገናኛ ከማድረጋቸው የተነሣ የወዳጅነት ውል የተዋዋሏቸውና የሌሎችም የልዩ ልዩ መንግሥቶች መሳፍንቶችና እንደራሴዎች ለዘውድ በዓላቸው መጥተው ሳሉ አጋጥሟቸው የአጼ ምኒልክ ሐውልት ሲመረቅ ከእኛ ጋር ቆመው የደስታችን ተካፋይ መሆናቸው የአጼ ምኒልክን ዕድለኛ መሆን ያስረዳናል።*

*ወደፊትም ለነገሥታት ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ትልልቅ ሥራ የሚሠሩና የሠሩ አርበኞች ለሥራቸውና ለስማቸው መታሰቢያ የሚሆን ሐውልት እያከታተልን እናቆማለን።*

*ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር*

ይህን ዲስኩር ተናግረው ከጨረሱ በኋላ ተጨበጨበና የምረቃው ሥነ በዓል ተፈጽሞ ወደ ቤተ መንግሥታቸው ተመለሱ።





የዳግማዊ ምኒልክ ሐውልት ሲመረቅ





ላይ ሰልፈኞች፣ ታች ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና እቴጌ መነን
ለንግሡ በዓል ወደ መናገሻ ጊዮርጊስ ጉዞ

## ስለ ሥርዓተ ንግሥ

የንጉሠ ነገሥቱና የእቴጌይቱ ሥርዓተ ንግሥ በአንድ ትንሽ መጽሐፍ ቀደም ብሎ ታትሞ ወጥቶ ነበርና ማንኛቸውም ሰው መጽሐፉን እየተመለከተ የሥነ ሥርዓቱን አፈጻጸም ተገንዝቦት ነበር። አሁንም ከብዙ በጥቂቱ ፍሬ ነገሩን ለመግለጽ ከዚህ በታች እጽፋለሁ።

ዋናው በዓል ጥቅምት 23 ቀን 1923 ዓ.ም. እሑድ ነበር። ቅዳሜ ማታ የመናገሻ ጊዮርጊስ ካህናትና ከየአድባራቱ ተመርጠው የመጡ መዘምራን ከማታው ከ4 ሰዓት ጀምረው ማኅሌት ቆመው አደሩ። እኩሌቶቹ መወድስ ሲቆሙ እኩሌቶቹ ክስተት አርያም[66] ያደርሱ ነበርና ማኅሌቱ ደምቆ አደረ።

ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌይቱም ከ4 ሰዓት በኋላ በመሳፍንትና በመኳንንት ታጅበው ወደ ቤተ ክርስቲያን ወጥተው ለዚህ ማዕረግ ላበቃቸውና ከዚህ ዕለት ላደረሳቸው አምላክ ምስጋና ከአቀረቡ በኋላ ወደ ማረፊያው ድንኳን ሄደው ጸሎተ ሕሊና ሲያደርሱ አደሩ። ጧት ሲነጋ መሳፍንትና መኳንንት ሙሉ የማዕረግ ልብሳቸውን ከኒሻን ጋር ለብሰው የራስ ሉልና የራስ ወርቅ ደፍተው በአዳራሹ ውስጥ በተሰናዳላቸው ስፍራ በየማዕረጋቸው ተቀመጡ። የውጭ አገር መንግሥታት መልእክተኞችም ሙሉ የማዕረግ ልብሳቸውን ለብሰው በተለይ በተለይ በተሰናዳላቸው የክብር ስፍራ ተቀመጡ። ጳጳሳትና መምህራን በመንበሩ አጠገብ በወለሉ ላይ ቆመው ለሥራ ተዘጋጁ።

ከጧቱ በአንድ ሰዓት ንጉሠ ነገሥቱ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥርዓተ ንግሥ ወደሚፈጸምበት አዳራሽ ገብተው በመንበሩ አጠገብ ተሳለሙና ለጥቂት ደቂቃ ጸሎተ ሕሊና አደረሱ። ቀጥሎም ፊታቸውን ወደ መቅደሱ አድርገው ቆመው ተፈሣሕኩ እስመ ይቤሉኒ ቤተ እግዚአብሔር ነሐውር[67] የሚለውን የዳዊት መዝሙር ደገሙ። ይህን እንደ ጨረሱም በተሰናዳው ዙፋን ላይ ተቀመጡ። እቴጌይቱ ግን ልብሰ መንግሥታቸውን ለብሰው በሌላ ስፍራ ተቀምጠው ቆይተው ነበር።

በዚህ ጊዜ ጳጳሳትና መምህራን በወለሉ ላይ ስፍራ ስፍራቸውን ይዘው ለሥራ ተዘጋጁ። ንዋያተ ንግሥም ከመቅደስ ወደ አዳራሹ ወጥተው በግርማዊነታቸው ፊት በተዘረጉት ጠረጴዛዎች ላይ ተደረደሩ።

ከዚህ በኋላ ሊቀ ጳጳሳቱ አቡነ ቄርሎስ ወደ ጠረጴዛዎች ቀረብ አሉና ፊታቸውን ወደ መሳፍንቱና ወደ መኳንንቱ አድርገው እንዲህ አሉ።

> እናንት የኢትዮጵያ መሳፍንትና ሚኒስትሮች መኳንንትና የጦር አለቆች ወታደሮችና ሠራዊቶች በቤተ ክህነትም ያላችሁ ሊቃውንትና አለቆች መምህራንና ቀሳውስት ሁሉ ይህ ንጉሠ ነገሥታችን ግርማዊ ኃይለ ሥላሴ ከሰሎሞንና ከንግሥተ ሳባ ከተወለደው ከዳግማዊ ምኒልክ ጀምሮ ሳይቋረጥ ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣው ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ መሆኑን ሁላችሁም ታውቃላችሁ። አሁን በእግዚአብሔር ፈቃድና ቸርነት ዘውድ ጭኖ እንዲነግሥ ልቀባው ነውና በሥጋዊና በመንፈሳዊ ሥራው ሁሉ አገርም በማሠልጠን ሃይማኖትም

[66] ሰማይ መከፈት፣ የዜማ ስም። በታላቅ በዓል ቀን እንዲሁም ታላላቅ ሰዎች ሲሞቱ የሚዘመር ነው። (አመኀ)

[67] ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ። መዝ. 121 ቍጥር 1 (አመኀ)

በማጽናት በዘመኑም ኢትዮጵያ በዕውቀትና በትምህርት በጥበብም ከፍ ከፍ እንድትል በመትጋት ከወሰንም እስከ ወሰን የኢትዮጵያ ባንዲራ እንዲዘረጋ በማድረግ ይህንንም በመሰለው በመልካም ሥራው ሁሉ እንድትገዙለትና እንድትረዱት አደራ እላችኋለሁ።

ሊቀ ጳጳሳቱ ይህን ተናግረው ሲጨርሱ ሕዝቡም ለንጉሠ ነገሥታችን እግዚአብሔር እንደ ቃልዎ ያድርግላቸው አሜን አሉ።

ከዚህም በኋላ ሊቀ ጳጳሳቱ ፊታቸውን ወደ ንጉሠ ነገሥቱ አዞሩና የሚከተሉትን ጥያቄዎች እየጠየቋቸው ንጉሠ ነገሥቱ ቆመው መልስ ሰጡ።

ጥያቄ። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሆይ እንደ ነገሥታት ደንብ ሲነግሡ የሚገባውን መሐላ ለመማል ይፈቅዳሉን።

መልስ። አዎን እፈቅዳለሁ።

ጥያቄ። ከቅዱሳን ነገሥታት ከአብርሃ ወአጽብሓ ጀምሮ በኢትዮጵያ ጸንቶ የኖረውን የእስከንድርያ የኦርቶዶክስን ሃይማኖት አጽንተው ለማኖርና የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የወሰነችውን ሕግና ሥርዓት ባለማፍረስ ለመጠበቅ ይምሉ ዘንድ ይፈቅዳሉን።

መልስ። የእስከንድርያ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት እስካሁንም አምኜበት የምኖር ነውና ወደፊትም በእግዚአብሔር እርዳታ ጠብቄ እንድኖር ለመማል ፈቃዴ ነው።

ጥያቄ። በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት በኢትዮጵያ ያለውን ሕዝብ በሥልጣንዎና በኃይልዎ በሚሠሩት ሥራ ሁሉ በርኅራኄና በትዕግሥት እንደ ሕጉ ለጥቅሙ እያሰቡ ይጠብቁታልን።

መልስ። ሕግ ለሰው አኗኗር መሠረት መሆኑን ዐውቃለሁና የምክር ቤቱንም ሕግ አክብሬ እጠብቃለሁ። በሚቻለኝም ሁሉ ሕጉ እንዲፈጸም አደርጋለሁ።

ጥያቄ። በኢትዮጵያ ሥጋዊና መንፈሳዊ ትምህርት የሚሰፋበትና ወንጌል የሚሰበክበት የትምህርት ቤት እንዲቆም በቸርነትዎና በሥልጣንዎ ይረዳሉን።

መልስ። ትምህርት ለቤተ መንግሥትና ለቤተ ክህነት ትልቅ ጥቅም መሆኑን ዐውቃለሁና በሚቻለኝ ሁሉ ለመርዳት ፈቃዴ ነው።

ይህ የመሐላ ቃል በጥያቄና በመልስ ከተነገረ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ እጃቸውን በወንጌል ላይ ጭነው አሁን የተናገርሁትን ሁሉ በእግዚአብሔር ረዳትነት ለመፈጸም ምያለሁ ብለው ወንጌሉን ተሳለሙ። ቀጥሎም የመሐላው ቃል በተጻፈበት ደብተር ላይ ፊርማቸውን ፈርመው በወምበራቸው ተቀመጡ።

ሊቀ ጳጳሳቱም 71ኛውን የዳዊት መዝሙር እግዚአ ኵነኔከ ሀቦ ለንጉሥ[68] ከሚለው ላይ አንሥቶ ወይሰገዱ ሎቱ ኵሎሙ ነገሥተ ምድር[69] እስከሚለው ድረስ ጸልየው በወምበራቸው ተቀመጡ።

68 አቤቱ ፍርድህን ለንጉሥ ስጥ። መዝ. 71 ቍጥር 1 (አመነ)

69 የምድር ነገሥታት ሁሉ ይሰግዱለታል። መዝ. 71 ቍጥር 11 (አመነ)

ከዚህ ቀጥሎ ልብስ ተክህኖ የለበሱ ሁለት ቀሳውስትና ሁለት ዲያቆናት ንዋያተ ንግሡ በተደረደሩበት ጠረጴዛ አጠገብ በሊቀ ጳጳሳቱና በጳጳሳቱ ፊት በቀኝና በግራ ቆሙ። ቀሳውስቱ ጥና ይዘው ያጥናሉ፤ ዲያቆናቱም ባለ መጾር መስቀል ይዘዋል።

ከዚህ በኋላ ሥርዓተ ቅዳሴ ተጀመረ። ቅዳሴው ከጸሎተ አኰቴት ላይ ሲደርስ አንድ ዲያቆን ተንሥኡ ለጸሎት ብሎ አዜመና ቄሱ ነአኵቶ ለገባሬ ሠናያት ላዕሌነ[70] የሚለውን አደረሱ።

ዲያቆኑ በዜማ ጸልዩ በእንተ እለ ያበውኡ መበዓ[71] ሲል የገንዘብ ሚኒስትሩ በጅሮንድ ዘለቀ አግደው አሥር ወቄት ወርቅ በንጉሠ ነገሥቱ ስም ለቤተ ክርስቲያን መባዕ በጠረጴዛው ላይ አስቀመጡ።

ጸሎቱም ሲቀጥል ቆየና ዲያቆን ከሮሜ የጳውሎስ መልእክት ለኵሉ ነፍስ መኰንን ተኰነኑ የሚለውን ክፍል ወለዘሂ ክብረ አክብሩ[72] እስከሚለው ድረስ አነበበ። ሁለተኛውም ዲያቆን ከመጀመሪያው የጴጥሮስ መልእክት አትሕቱ እንከ ርእሰክሙ ለኵሉ ፍጥረተ እጓለ እመሕያው ከሚለው አንሥቶ ለእግዚአብሔርኒ ፍርህዎ ወለንጉሥኒ አክብርዎ[73] እስከሚለው ድረስ አነበበ። ከዚህ በኋላ ኪዳን ተደረሰና የንግሡ ሥነ ሥርዓት ቀጠለ።

የላስታው መምህር አባ ጎሩይ ልብሰ መንግሥቱን ከጠረጴዛው አንሥተው ወደ ሊቀ ጳጳሳቱ አቀረቡና ሊቀ ጳጳሳቱ ከባረኩት በኋላ መምህሩ ተቀብለው ለኢትዮጵያ ሰሜን ጳጳስ ለአቡነ ይስሐቅ ሰጧቸው። ጳጳሱም ጸሎት ጸልየውበት ለመምህሩ መለሱላቸው። መምህሩም ወደ ሊቀ ጳጳሳቱ አቅርበው አስባርከው ለጳጳሱ መለሱና ጳጳሱ አቡነ ይስሐቅ ለንጉሠ ነገሥቱ አለበሱዋቸው።

ከዚህ ቀጥሎ ከመዘምራን መካከል የተመረጡ አሥር ድምፀ መልካሞች በወለሉ ላይ ትንሽ ገባ ብለው ቆሙና ፊታቸውን ወደ ንጉሠ ነገሥቱ አድርገው ጐሥዓ ልብየ ቃለ ሠናየ[74] የሚለው የአርባዕት ምዕራፍ በአራራይ ዜማ እየተቀባበሉ አዜሙትና ቅንት ሰይፈከ ኀያል ውስተ ሐቌከ በሥንከ ወበላህይከ[75] ከሚለው ሲደርሱ ዜማውን አቆሙት።

በዚህ ጊዜ የተድባበ ማርያም መምህር ሠይፉን ከጠረጴዛው አንሥተው ወደ ሊቀ ጳጳሳቱ አቅርበው አስባረኩና ለኢትዮጵያ ደቡብ ጳጳስ ለአቡነ ሳዊሮስ ሰጡዋቸው። እሳቸውም፤

> አቤቱ አምላክ ሆይ ጸሎታችንን ትሰማ ዘንድ እንለምንሃለን፤ አገልጋይህን ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴን በሥራው ሁሉ ምራው ደግፈው፤ በዚህም አሁን በሚታጠቀው ሠይፍ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሆኖ ክፉ አድራጎችን

---

70 በእኛ ላይ መልካም ተግባራት የሚያከናውነውን እናመሰግናለን። መጽሐፈ ቅዳሴ (አመንጎ)

71 መብዓ (ስጦታ) ስለሚያገቡ ሰዎች ጸልዩ። መጽሐፈ ቅዳሴ (አመንጎ)

72 ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለሥልጣኖች ይገዛ። ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ። ሮሜ ም 13፣ ቍ 1/8 (አመንጎ)

73 እንግዲህ ክፋትን ሁሉ ተንኰልንም ሁሉ ግብዝነትንም ቅንዓትንም ሁሉ አስወግዳችሁ፣ እግዚአብሔርን ፍሩ፣ ንጉሥን አክብሩ። 1ኛ ጴጥ. ም 2 ቍ 1/17 (አመንጎ)

74 ልቤ መልካም ነገርን አፈለቀ። መዝ. 44 ቍ 1 (አመንጎ)

75 ኃያል ሆይ፣ በቍንጅናህና በውበትህ ሠይፍህን በወገብህ ታጠቅ። መዝ. 44 ቍ 3 (አመንጎ)

> እንዲበቀልበትና እንዲቀጣበት፤ ለመልካም አድራጎትም እንዲመካበትና እንዲጽናናበት አድርገው፤ በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

ብለው ጸለዩበትና ባርከው ለመምህሩ ሰጡ። መምህራኑም ወደ ሊቀ ጳጳሳቱ አቅርበውና አስባርከው ለጳጳሱ መለሱላቸው። ጳጳሱ አቡነ ሳዊሮስም የመከዱን ጫፍ ለንጉሠ ነገሥቱ አሲዘው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ።

> በዚህ ሠይፍ እውነተኛ ፍርድ ፍረድበት፣ የእግዚአብሔርን ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ጠብቅበት፤ ልጆቻቸውና ባሎቻቸው የሞቱባቸውን ሕፃናቶች እርዳና የተበላሸውን አድስበት፤ የታደሰውንም አፅናበት፤ ዓመፀኞችን ቅጣበት፤ ፈቃደኞችን ሹምበት። በዘመንህም ሁሉ ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን አገልግልበት። እንደዚህም ብታደርግ በሚመጣው በዘለዓለም ሕይወት መንግሥት ከእርሱ ጋር ትነግሣለህ።

አሏቸው። ንጉሠ ነገሥቱም ይህን የተናገሩትን ሁሉ ለመፈጸም ያብቃኝ ብለው ተቀብለው በቀኝ ወገባቸው ታጠቁት።

ከዚህም ቀጥሎ መዘምራኑ የምዕራፉን ዜማ አርትዕ ተሠራሕ ወንገሥ[76] ከሚለው አንሥተው ቀጠሉና በትረ ጽድቅ ወበትረ መንግሥትከ[77] ከሚለው ሲደርሱ አቆሙት።

በዚህ ጊዜ የሐይቁ መምህር በትረ መንግሥቱን ከጠረጴዛው አንሥተው ወደ ሊቀ ጳጳሳቱ አቅርበው አስባረኩና ለኢትዮጵያ ሰሜን ጳጳስ ለአቡነ ይስሐቅ ሰጧቸው። ጳጳሱም በትረ መንግሥቱን በእጃቸው ይዘው የመቶ ዘጠነኛውን የዳዊት መዝሙር፤ ይቤሎ እግዚእ ለእግዚእየ ንበር በየማንየ[78] ከሚለው አንሥተው በትረ ኃይል ይፌኑ ለከ እግዚአብሔር እምጽዮን ወትኴንን በማእከለ ጸላእትከ[79] እስከሚለው ድረስ ደግመው ጸለዩበትና ባርከው ለመምህሩ ሰጧቸው። መምህሩም እንደገና ወደ ሊቀ ጳጳሳቱ አቅርበውና አስባርከው ለጳጳሱ መለሱላቸውና ጳጳሱ በትረ መንግሥቱን ለንጉሠ ነገሥቱ በቀኝ እጃቸው አሲያዙዋቸው።

ከዚህም ቀጥሎ የመርጡለ ማርያም መምህር ሉሉን ከጠረጴዛው አንሥተው ወደ ሊቀ ጳጳሳቱ አቅርበው አስባረኩና ለኢትዮጵያ ምዕራብ ጳጳስ ለአቡነ አብርሃም ሰጧቸው። ጳጳሱም ጸሎተ ምናሴን፤ ርኁቀ መዓት ወብዙኀ ሣህል[80] እስከሚለው ድረስ ደግመው ጸልየው ባረኩትና ለመምህሩ መለሱላቸው። መምህሩም ወደ ሊቀ ጳጳሳቱ ወስደው አስባርከው ለጳጳሱ ሰጡ። ጳጳሱ አቡነ አብርሃምም ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ቀርበው «ሰማይንና ምድርን በእጅ የያዘ አምላክ ይህን ሉል ይባርክልዎ» ብለው ሰጧቸው። ንጉሠ ነገሥቱም ሉሉን በግራ እጃቸው ተቀብለው ያዙት።

ከዚህ ቀጥሎ የጣና ቂርቆስ መምህር ባለ አልማዙን ቀለበት (ሕለተ ወርቅ) ከጠረጴዛው አንሥተው ወደ ሊቀ ጳጳሳቱ አቅርበው አስባረኩና ለኢትዮጵያ አዜብ ጳጳስ

[76] አቅና ተከናወን ንገሥም። መዝ. 44 ቁ. 4 (አመን)

[77] የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር ነው። መዝ. 44 ቁ. 6/7 (አመን)

[78] እግዚአብሔር ጌታዬን በቀኝ ተቀመጥ አለው። መዝ. 109 (110) ቁ. 1 (አመን)

[79] እግዚአብሔር የኃይልን በትር ከጽዮን ይልክልሃል፤ በጠላቶችህም መካከል ግዛ። መዝ. 109 (110) ቁ. 2 (አመን)

[80] መዓትህ የራቀ፣ ምሕረትህም የበዛ። (አመን)

አቡነ ሚካኤል ሰጡዋቸው። ጳጳሱም ከጸለዩበትና ከባረኩት በኋላ ለመምህሩ መለሱላቸው። መምህሩም እንደገና ወደ ሊቀ ጳጳሳቱ አቅርበው ለንጉሥነት ክብር የሚሆን ይህን ቀለበት ይቀበሉ ብለው ለንጉሠ ነገሥቱ በቀኝ እጃቸው በአራተኛው ጣታቸው ላይ አጠለቁላቸው።

ከዚህ በኋላ መዘምራኑ ዜማውን አርትዕ ተሠራሕ ወንገሥ ከሚለው እንሥተው ቀጠሉና አኀፃከ ስሑል ኃያል[81] ከሚለው ሲደርሱ አቆሙት።

በዚህ ጊዜ የደብረ ወገግ (አሰቦት) መምህር አባ ገብረ አብ ሁለቱን ጦሮች ከጠረጴዛው አንሥተው ወደ ሊቀ ጳጳሳቱ አቅርበው አስባረኩና ለኢትዮጵያ ምሥራቅ ጳጳስ ለአቡነ ጴጥሮስ ሰጧቸው። ጳጳሱም ንሣእ ወልታ ወኲናተ ወተንሥእ ለረዲአቱ። በላ ለነፍሱ ረዳኢኪ አነ። በበአቱ ወበፀአቱ ከመ ብንተ ዐይን ዕቀቦ ለንጉሥነ ኃይለ ሥላሴ።[82] ብለው ጸልየው ባረኩትና ለመምህሩ ሰጡ። መምህሩም እንደገና ወደ ሊቀ ጳጳሳቱ አቅርበው አስባረኩና ለጳጳሱ ሰጡ። ጳጳሱ አቡነ ጴጥሮስም እግዚኦ ሰማዕነ በእዘኒነ[83] የሚለውን 44ኛውን የዳዊት መዝሙር ወኲናትየኒ ኢያድኅነኒ ዘእንበለ የማንከ ወመዝራዕትከ ወብርሃነ ገጽከ[84] እስከሚለው ድረስ ደግመው ጦሮቹን ለንጉሠ ነገሥቱ አቀረቡ። የንጉሠ ነገሥቱም ጋሻ ጃግሬ ሁለቱን ጦሮች ከንጉሠ ነገሥቱ ተቀብሎ ያዘ።

ከዚህ በኋላ መዘምራኑ የምዕራፉን ዜማ አፍቀርከ ጽድቀ ወዐመፃ ጸላእከ[85] ከሚለው ላይ አንሥተው ቀጠሉና ከርቤ ወቀንዓት ወሰሊሖት እምነ አልባሲከ[86] ከሚለው ሲደርሱ አቆሙት።

በዚህ ጊዜ የደብረ ሊባኖስ ፀባቴ ቀርነ ቅብዑን ከጠረጴዛው አንሥተው ለሊቀ ጳጳሳቱ አቅርበው አስባረኩና ለኢትዮጵያ ደቡብ ጳጳስ ለአቡነ ሳዊሮስ ሰጧቸው። ጳጳሱም ቀርነ ቅብዑን በእጃቸው ይዘው በሊቀ ጳጳሳቱ ፊት ቆሙ። ሊቀ ጳጳሳቱ ከዚህ በታች ያለውን ጸሎት ጸለዩ።

> ቅዱስ አምላክ ሆይ፤ ከተቀደሰው መንበረ መንግሥት፤ ከማይወሰነውም ሥልጣንህ ከዘለዓለሙ ጌትነትህ፤ የሚያጽናናውን መንፈስ ቅዱሳን (ጰራቅሊጦስን) በዚህ ቅብዓ መንግሥት ተቀብቶ የከበረና የተቀደሰ ይሆን ዘንድ፤ በጽድቅህም ብርሃን መኰናጸፊያ ተኰናጽፎ የሚቃወሙትን የመንግሥት ጠላቶች ያሸንፍ ዘንድ ክንዱን አበርታው። አንተም ደስ በሚያሰኙህ በቅዱሳን ነገሥታት መካከል እንደ ሰማይ ኮከብ ያበራ ዘንድ ጸጋህን ስጠው።
>
> ቅዱስ አምላክ ሆይ የብሉይ ነገሥታት ካህናት ነቢያትም ሕዝብህን እስራኤልን እንዲገዙና እንዲያስተምሩ በተቀደሰ ቅብዓ እንደ ቀባሃቸው አሁንም በዚያው ልማድ አንተ የመረጥኸውን አገልጋይህን ኃይለ ሥላሴን ባርከው ቀድሰው ለእኛም በሰጠኸን ሥልጣን ቅብዓ መንግሥቱን ተቀብቶ የኢትዮጵያ

---

81 ኃያል ሆይ፣ ፍላጻዎችህ የተሳሉ ናቸው። መዝ. 44 ቍ 5 (አመኀ)

82 ጥሩርና ጋሻ ያዝ፣ እርሱንም ለመርዳት ተነሥ፣ ነፍሱንም ረዳትሽ እኔ ነኝ በላት። ንጉሣችን ኃይለ ሥላሴንም በመግቢያውም በመውጫውም እንደ ዐይን ብሌን ጠብቀው። ከመዝ. 34 ቍ 1-2 የተዛመደ። (አመኀ)

83 አቤቱ፣ በጆሮአችን ሰማን። መዝ. 43 (44) ቍ 1 (አመኀ)

84 ቀኝህና ክንድህ የፊትህም ብርሃን ነው እንጂ። መዝ. 43 ቍ 3 (አመኀ)

85 ጽድቅን ወደድህ ዓመፃንም ጠላህ። መዝ. 44 ቍ 7 (አመኀ)

86 በልብሶችህ ሁሉ ከርቤና ሽቱ ዝባድም አሉ። መዝ. 44 ቍ 8 (አመኀ)

ንጉሠ ነገሥት ይሆን ዘንድ ኃይልን ስጠው። በመንፈስህም አበርታው። የጥበብና የማስተዋል፣ የምክርና የኃይል፤ የዕውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ አሳድርበት። ከአሁኑ ጀምሮ ለዘለዓለም። አሜን።

ብለው ጸልየው ሲጨርሱ ጳጳሱ ቅብዓ ቅዱሱን ለሊቀ ጳጳሳቱ ሰጡ። ሊቀ ጳጳሳቱም ከቅብዓ መንግሥት በአውራ ጣታቸው እያጠቀሱ ሳሙኤል ዳዊትን፣ ሳዶቅ ዮናታንና ሰሎሞንን እንደ ቀቡ እኔም በዚህ በተቀደሰውና በተባረከው ቅብዓ መንግሥት እቀባዎታለሁ ብለው የንጉሠ ነገሥቱን ራስ ቀቧቸው። ቀጥሎም በእንተ ንጉሥ[87] የሚለው መስተብቍዕ ከጳጳሳቱ በአንደኛው ተደገመና ጸሎቱ ወይተናገር ጽድቀ በውስተ ልቡ[88] ከሚለው ላይ ሲደርስ ሊቀ ጳጳሳቱ የንጉሠ ነገሥቱን ደረትና ልብ ቀቡ።

ከዚህ በኋላ መዘምራኑ እምከቡዳነ አቅርንት ዘእምኔሆሙ አስተፌሥሐከ[89] የሚለውን የምዕራፉን መነሻ አዚመው እዚያው ላይ አቆሙት።

በዚህ ጊዜ ቁምስና ያላቸውን የአክሱም መምህር አባ ገብረ ማርያም ዘውዱን ከጠረጴዛው አንሥተው ለሊቀ ጳጳሳቱ ለአቡነ ቄርሎስ አቀረቡ። ሊቀ ጳጳሳቱም እግዚኦ በኃይልከ ይትፌሣሕ ንጉሥ[90] የሚለውን 20ኛውን የዳዊት መዝሙር እስከ መጨረሻው አነበቡና ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ጸሎት ጸለዩ።

> አቤቱ የታመንህ አምላካችን ሆይ፤ ይህን ዘውድ ትባርክ ዘንድ እንለምንሃለን፤ ይህንንም አገልጋይህን ንጉሣችንን ኃይለ ሥላሴን ዘውዱን ለመቀበል የበቃና የተዘጋጀ እንዲሆን ቀድሰው ይህንንም ከጥሩ ወርቅ የተሠራውን ዘውድ እንደ ጫንህለት በቸርነትህ ብዛት የበጎነትን ዘውድ በልቡ ጫንለት። በዘለዓለሙ ንጉሣችንን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።

ከዚህም በኋላ ሊቀ ጳጳሳቱ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ቀርበው

> ይህን ዘውድ የጽድቅና የምስጋና ዘውድ ያድርግልዎ፤ በዚህም በእኛ ቡራኬ የቀና ሃይማኖትና መልካም ምግባርን ይዘው የዘለዓለም መንግሥቱን ዘውድ ለማግኘት ያብቃዎ አሜን።

ብለው ተናገሩና ዘውዱን ጫኑላቸው። በዚህ ጊዜ ከፍ ያለ ጭብጨባ ተጨበጨበ።

ንጉሠ ነገሥቱ ቅብዓ መንግሥት ተቀብተው ዘውድ ከጫኑ በኋላ ንዑስ እነ አምኃውየ[91] የሚለውን የዳዊት መዝሙር ወቀብዐኒ ቅብዓ ቅዱስ[92] እስከሚለው ድረስ በታላቅ ድምፅ አነበቡ።

እስከዚህ ጊዜ ድረስ ንጉሠ ነገሥቱ ቆመው ነበርና ከዚህ በኋላ በዙፋናቸው ተቀመጡ። መሳፍንትና መኳንንትም የራስ ሉላቸውንና የራስ ወርቃቸውን ከየራሳቸው

---

87 ስለ ንጉሥ። (አመነ)

88 በልቡም እውነትን ይናገራል። (አመነ)

89 ከዝሆን ጥርሶች አዳራሽ ደስ ያሰኙሃል። መዝ. 44 ቍ 8 (አመነ)

90 አቤቱ፣ በኃይልህ ንጉሥ ደስ ይለዋል። መዝ. 20 ቍ 1 (አመነ)

91 ከወንድሞቼ ይልቅ ትንሽ ነበርሁ። መዝ. ም. 150 ቀጥሎ ስለራሱ ከተናገረው። (አመነ)

92 ቅብዓ ቅዱስንም ቀባኝ። መዝ. ም. 150 ቀጥሎ ስለራሱ ከተናገረው። (አመነ)

እያወረዱ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት እያጐነበሱ እጅ ነሡ። ሕዝቡም ደስታውን በጭብጨባና በዕልልታ ገለጸ።

ከዚህ በኋላ ሊቀ ጳጳሳቱ ከጳጳሳቱ ጋር ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ቀርበው እንዲህ አሉ።

ግርማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆይ! ዛሬ በፊትዎ የታመንሁና እውነተኛ እሆናለሁ፤ ሃይማኖትና እውነትም ይመሰክሩልኛል። ከእኔም ጋራ ያሉት ጳጳሳትና ሥልጣንም የሰጠኋቸው ቀሳውስትና ዲያቆናት እንደ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት ለመንግሥትዎ እንዲታዘዙና ቤተ ክርስቲያንንም እንዲጠብቁ አደርጋለሁ። ለዚሁም ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል በክንድዎ ላይ ሆኖ ይርዳዎ።

ብለው የንጉሠ ነገሥቱን ቀኝ ትከሻ ሳሙ። የቀሩትም ጳጳሳት መስቀል አሳልመው እግዚእትነ ማርያም በረድኤት አትለይዎ። እያሉ እጅ ነሥተው ተመለሱ።

## ለአልጋ ወራሹ ስለተደረገው ሥነ ሥርዓት

ከዚህ በኋላ አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን አክሊላቸውን ከራሳቸው አውርደው ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ቀረቡና በጉልበታቸው ተንበረከኩ። ወዲያው ሊቀ ጳጳሳቱ ቀርበው እንዲህ እያሉ ጥያቄ አቀረቡላቸውና መልሱን ሰጡ።

ጥያቄ። ለንጉሠ ነገሥቱ ለአባትህ በሕይወትህ ሁሉ አገልጋይ ለመሆን ትፈቅዳለህን።

መልስ። አክብር አባከ ወእመከ[93] የተባለውን ትእዛዝ ሰምቻለሁና በፍጹም ልቤ እገዛለሁ።

ጥያቄ። እንደ አቤሴሎም ደፍረህ፤ እንደ አዶንያስ ቸኩለህ ከአባትህ ፈቃድ ለመውጣት፣ ያልሰጠህን ለመሻት ከሚመክሩህ ጋር እንዳትተባበርና እንዳትከተል ትጠነቀቃለህን።

መልስ። ከአባቱ ፈቃድ የሚወጣ የተረገመና ሞት የሚገባው መሆኑን ሰምቻለሁና ይኸንን በመሰለው መንገድ አባቴን እንዳላስቀይም እጠነቀቃለሁ።

ጥያቄ። አባትህ ንጉሠ ነገሥቱ ፈቅዶ በምክር ቤት አስመስክሮ ያቆመውን ሕግ፤ ከክፉ ሰዎች ጋር ተቀላቅለህ እንቅፋት ሳትሆን ለሕግ ፈቃደኛ ለመሆን ትወዳለህን።

መልስ። ንጉሠ ነገሥቱ አባቴ ተቀብሎ ያቆመውን ሕግ አክብሮ ለመጠበቅ እውነተኛ ፈቃዴ ነው።

ብለው ቃላቸውን ሰጡና ይኸው ቃል በተጻፈበት ደብተር ላይ ፊርማቸውን ፈርመው የአባታቸውን የንጉሠ ነገሥቱን ጉልበት ሳሙ።

ከዚህ ቀጥሎ ንጉሠ ነገሥቱ እግዚአብሔር የኃይሌና የሥልጣኔ፣ የዙፋኔና የዘውዴ ተቀባይ ያድርግህ ብለው በትረ መንግሥት የያዙበትን ቀኝ እጃቸውን ዘረጉባቸው። አልጋ ወራሹም አሜን እግዚአብሔር እንደ ቃልዎ ያድርግልኝ ብለው የንጉሠ ነገሥቱን ቀኝ እጃቸውን ተሳልመው አክሊላቸውን አድርገው ወደ መቀመጫቸው ተመለሱ።

[93] አባትና እናትህን አክብር። (አመን)

ከዚህ በኋላ መሳፍንቱ የራስ ሉላቸውን ራሶች የራስ ወርቃቸውን እያወለቁ በየተራ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ በየተራ እየቀረቡና እያጐነበሱ እጅ ነሡ። ሚኒስትሮችና መኳንንትም ሌላውም በሥርዓተ ንግሡ የነበረው ሁሉ ተነሥቶ ቆሞ ሺህ ዓመት ያንግሥዎ እያለ አጎንብሶ እጅ ነሣ። ሕዝቡም ሁሉ አጨበጨበ በስተውጭም ዕልል ተባለ። ወዲያው የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር (ሂም ናሲዮናል) ተነፋ ቀጥሎም መቶ አንድ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ።

## የእቴጌ አነጋገሥ

የንጉሠ ነገሥቱ ሥርዓተ ንግሥ በዚህ አኳኋን ከተፈጸመ በኋላ መዘምራኑ አዋልደ ንግሥት ለክብርከ፣ ወትቀውም ንግሥት በየማንከ፣ በአልባሰ ወርቅ ዑጽፍት ወኍብርት[94] የሚለውን የምዕራፉን ዜማ አዚመው እዚያው ላይ አቆሙት።

በዚህ ጊዜ እቴጌ መነን ከቆዩበት ስፍራ ልብሰ መንግሥት እንደለበሱ ተነሥተው በወይዛዝር ታጅበው መጡና በንጉሠ ነገሥቱ ቀኝ በተዘረጋላቸው የወርቅ ወምበር ተቀመጡ። በፊትና በኋላ አጅበዋቸው የመጡት የመንግሥት ዘር የሆኑት ወይዛዝሮች አክሊላቸውን ሳያደርጉ የማዕረግ ልብሳቸውን ለብሰው በእቴጌ ኋላ ቆመው ቆዩ።

ከዚህ በኋላ መዘምራኑ ስምዒ ወለትየ ወርእዪ ወአፅምኢ እዝነኪ፣ እስመ ፈተወ ንጉሥ ሥነኪ እስመ ውእቱ እግዚእኪ[95] የሚለውን የምዕራፉን ዜማ አዜሙና አቆሙት። በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ ደቡብ ጳጳስ አቡነ ሳዊሮስ ባለ አልማዙን ቀለበት ከጠረጴዛው አንሥተው ይዘው የሚከተለውን ቃል ተናገሩ።

> የሃይማኖት ምልክት የሚሆን ይህን ቀለበት ይቀበሉ፣ በዚህም ቀለበት ምልክትነት፣ ሥልጣን ሁሉ ገንዘቡ የሚሆን እግዚአብሔር ክብርዎን ያብዛልዎ። ሁልጊዜም ፍጹም እንዲሆኑ ፈሪሃ እግዚአብሔርን በልብዎ ያሳድርብዎ፣ ሁልጊዜም እርሱን ደስ የሚያሰኝ ሥራ ለመሥራት ያብቃዎ።

ብለው ተናገሩና ቀለበቱን በእቴጌይቱ ቀኝ እጅ በአራተኛይቱ ጣታቸው ላይ አጠለቁላቸው። ከዚህም በኋላ ሁለት ቆሞሳት የእቴጌይቱን ዘውድ ከጠረጴዛው አንሥተው ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ፊት አቀረቡ። ሊቀ ጳጳሳቱ አቡነ ቄርሎስ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ቀርበው ቆሙ። አቡነ ቄርሎስም ዘውዱን ከጠረጴዛው ላይ አንሥተው ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀረቡ። ንጉሠ ነገሥቱም ዘውዱን አንሥተው፤

> እቴጌ ከእግዚአብሔር የተፈቀደልኝን ዘውድ ከእርስዎ እጅ እንደ ተቀበልሁ፣ እቴጌ መነንም ይህን ዘውድ ከእኔ ተቀብላ የክብሬ ተካፋይ እንድትሆን እውነተኛ ፈቃዴ ነውና ዘውዱን እርስዎ እንዲጭኑላት እለምናለሁ።

አሏቸው። ሊቀ ጳጳሳቱም ዘውዱን ከንጉሠ ነገሥቱ እጅ ተቀብለው ይዘው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ጸሎት ጸለዩ።

[94] የንጉሦች ሴት ልጆች ለክብርህ ናቸው፣ በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋፍና፣ ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች። መዝ. 44 ቍ 9 (አመነ)

[95] ልጄ ሆይ ስሚ፣ እዪ፣ ጆሮሽንም አዘንብዪ፤ ወገንሽን፣ የአባትሽንም ቤት እርሺ፣ ንጉሥ ውበትሽን ወዶአልና፣ እርሱ ጌታሽ ነውና። መዝ. 44 ቍ 10 (አመነ)

አቤቱ አምላካችን ሆይ፣ በአገልጋይህ በእቴጌ መነን ላይ ይህን የደስታና የክብር ዘውድ አኑር። ይኸውም የቸርነትና የርኅራኄ፣ የዕውቀትና የጥበብ ዘውድ ይሁንላቸው። አቤቱ ቅዱስ አብ ሆይ የክብር የምስጋናም ዘውድ አድርግላቸው። አሜን።

ብለው ጸለዩ። ጸሎቱንም እንደጨረሱ ወደ እቴጌ ቀርበው

ይህን የደስታና የክብር ዘውድ ይቀበሉ፣ ይህን የወርቅ ዘውድ እንደ ጫኑ እግዚአብሔር በልብዎ እርሱን የሚፈሩበት፣ ንጉሠ ነገሥቱን የሚያከብሩበት ዘውድ ይጫንልዎ።

ብለው ዘውዱን ጫኑላቸው።

እቴጌዪቱም ዘውዱን ከጫኑ በኋላ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ቀርበው በአንገት እጅ ነሥተው በወርቅ ወምበራቸው ላይ ተቀመጡ። በዚህ ጊዜ በዚያ ስፍራ የተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ ይበጅ ያድርግ እያለ በየቆመበት ሆኖ ሁሉም እጅ ነሣ። ሴቶች ወይዛዝርት ዕልልል አሉ። ካህናትም አክሊለ ተቀጺላ ታንሶሱ[96] የሚለውን ወረብ ወርበው በከበሮና በጸናጽል ደስታቸውን ገለጹ። ከዚህ በኋላ መዘምራኑ የምዕራፉን ዜማ ወይሰግዳ ሎቱ አዋልደ ጢሮስ በአምኃ[97] ከሚለው አንሥተው አዜሙና ወያበውእዎን ውስተ ጽርሐ ንጉሥ[98] ከሚለው ላይ ሲደርሱ አቆሙት።

በዚህ ጊዜ የመንግሥት ዘር የሆኑ አራት ወይዛዝርት ለእቴጌይቱ በአንገት እጅ ከነሡ በኋላ አክሊላቸውን አድርገው ከእቴጌይቱ በስተኋላ በተዘጋጀላቸው ወምበር ተቀመጡ።

## ስለ ጸሎተ ቅዳሴና ስለ ዑደት

ከዚህ በኋላ ጸሎተ ቅዳሴው ቀጠለና አ ሥሉስ ቅዱስ መሐረነ[99] የሚለው ተዜመ። ወዲያው ዲያቆን፣ እስመ በጸሕኮ በበረከት ሠናይ፣ ወአንበርከ አክሊለ ዲበ ርእሱ ዘእምዕንቍ ክቡር፣ ሐይወ ሰአለከ ወወሀብኮ[100] ብሎ በዜማ ምስባክ ሰበከ።

ቄሱም ወንጌል ቅዱስ ዘማቴዎስ ብሎ አዜመና በማቴዎስ ወንጌል ም 22 ቁ. 15-22 የተጻፈውን በግእዝ አነበበ። የወንጌሉንም ቃል አቡነ አብርሃም በአማርኛ ተርጕመው ባጭሩ አሰሙ።

ከዚህ በኋላ የእስክንድርያው ፓትረያርክ አቡነ ዮሐንስ የላኩት የቡራኬ ቃል በዐረቢኛ ተነበበና ትርጓሜውን በጅሮንድ ዮሴፍ በአማርኛ አሰሙ።

---

96 ዘውድን ተቀዳጅታ ትመላለሳለች። (አመነ)

97 የጢሮስ ሴቶች ልጆች እጅ መንሻን ይዘው ይሰግዱለታል። መዝ. 44 ቍ 12። (አመነ)

98 ወደ ንጉሥ እልፍኝም ያስገቡዋቸዋል። መዝ. 44 ቍ 15። (አመነ)

99 ሥሉስ ቅዱስ ሆይ ማረን። (አመነ)

100 በበጎ በረከት ደርሰህለታልና፣ ከክቡር ዕንቍ የሆነ ዘውድን በራሱ ላይ አኖርህ፣ ሕይወትን ለመነህ፣ ሰጠኸውም። መዝ. 20 ቍ 3-4። (አመነ)

የቡራኬው ቃል ከተነበበና ከተሰማ በኋላ አቡነ ሳዊሮስ ጸጋ ዘአብ ኂሩት ዘወልድ ሱታፌ ዘመንፈስ ቅዱስ[101] የሚለውን ቃለ ቡራኬ እስከ መጨረሻው አንብበው አሳረጉና ባርከው ተቀመጡ።

በዚህ ጊዜ ሊጋባ ወዳጄና ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል ወደ አዋጅ መንገሪያው ስፍራ ሄደው የንጉሠ ነገሥቱን የአዋጅ ቃል ተናገሩ።



*ዑደት ሲያደርጉ*

የቅዳሴውም ጸሎት እንደ ሥርዓቱ ቀጠለ። በዚህ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌይቱ ከወምበር ተነሥተው ቆሙ። ዘውዳቸውን ከራሳቸው አውርደው በጠረጴዛ ላይ አስቀመጡት። የላይኛውንም ልብስ መንግሥታቸውን አውልቀው የሥጋ ወደሙ መቀበያ ሌላ ነጭ ሐር ልብስ ለበሱ። ሥጋ ወደሙ ከተቀበሉና ጸሎተ ቅዳሴው ከተፈጸመ በኋላ እንደገና ልብሰ መንግሥታቸውን ለብሰው፤ ዘውዳቸውን ጭነው፤ በትረ መንግሥታቸውን ይዘው፤ ሉል ጨብጠው ወጡ።

ጳጳሳቱና ቀሳውስቱ ታቦት አውጥተው በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ ዑደት ተደረገ። ሕዝቡ የሰሌን ቅጠል በእጁ ይዞ ነበር። መዘመራኑም ቡሩክ አንተ ንጉሠ እስራኤል[102] የሚለውን ወርበው እያሸበሸቡ በታቦቱ ፊት ቀደሙ። ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌይቱም ታቦቱን ተከትለው ሦስት ጊዜ ዑደት አደረጉ።

ከዑደቱ በኋላ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ ግቢ ከፍ ብሎ በተሠራ ስፍራ ላይ ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌይቱ ብቻ ቆመው ለሕዝብ ታዩ። በዚህ ጊዜ ወንዱ በጭብጨባና ሴቱ በዕልልታ ደስታውን ገልጸላቸው ወደ ማረፊያው ድንኳን ተመለሱ።

---

[101] የአብ ጸጋ፣ የወልድ ቸርነት፣ የመንፈስ ቅዱስ አንድነት። (አመነ)

[102] አንተ የእስራኤል ንጉሥ የተባረክህ ነህ። (አመነ)



ከንግሡ በኋላ ዙፋን ላይ ተቀምጠው

## ወደ ቤተ መንግሥት ስለ መመለስ

ከዚህ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌይቱ በስድስት ፈረሶች በሚሳብ በወርቅ ሠረገላ ተቀምጠውና ከፊትም በኋላም በመሳፍንትና በመኳንንት ታጅበው በወታደርና በሠራዊት ሰልፍ መካከል አልፈው ወደ ቤተ መንግሥታቸው ተመለሱ። መሳፍንትና መኳንንት የመንግሥታት መልእክተኞችም በየማዕረጋቸው በሠረገላ ወይም በአቶሞቢል ሆነው አጀቡ። እምቢልታውና መለከቱ ሲንካለል፤ ነጋሪቱ እየተጐሰመ ገብር ገብር ሲል እጅግ ደስ ያሰኝ ነበር።



በሠረገላ ወደ ቤተ መንግሥት ሲመለሱ

በመንገድ ዳር ሆኖ ለማየት የተሰበሰበውም ሕዝብ ሰላምታ እየሰጠና እጅ እየነሣ ሺህ ዓመት ያንግሥዎ እያለ አጨበጨበ።

ከቤተ መንግሥት በደረሱ ጊዜም ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌይቱ ለማሰናበቻ በተሰናዳው ስፍራ ቆመው ሲያዩለት ሕዝቡ ሁሉ እንደገና እያጨበጨቡና ሺህ ዓመት ያንግሥዎ ብለው እየመረቁ ተሰናበቱ።

## ስለ ግብሩ ሥርዓት

በዚህ በዘውድ በዓል ቀን ለመንግሥታት መልእክተኞችና መሳፍንት ለመኳንንትና ለሠራዊት ጭምር በቤተ መንግሥት ታላቅ ግብዣ ተደረገ። እንዲሁም ደግሞ ሳምንቱን

በሙሉ ከረቡዕና ከዓርብ በስተቀር ሙሉ ግብር ሲደረግ ሰነበተ። ቀጥሎም እስከ ኅዳር 11 ቀን ድረስ በከተማ ለሚኖሩ ነጋዴዎች ለእስላሞችና ለባንያኖች ለሌላም ጎሣ ሁሉ ግብዣውና ግብሩ ሳያቋርጥ ሰነበተ።

የዘውዱን በዓል ለማክበር ከያገሩ ለመጡት የመንግሥታት መልእክተኞች በተለይ ግብዣ ሲደረግና የመታሰቢያ የወርቅ ሜዳይና ልዩ ልዩ ኒሻን ሲሰጥ ሰነበተ። በያውራጃው እየተዘዋወሩም አገርን እንዲጐበኙ ተደረገ። ከዚህም በኋላ ከኅዳር 3 ቀን ጀምሮ በየቀኑ ከጃንሆይ እየተሰናበቱና እንደ ቀድሞውም በመሳፍንትና በመኳንንት በታላቅ ክብር ተሸኝተው በባቡር እየተሣፈሩ ደስ ብሏቸው ወደያገራቸው ተመለሱ።

ከነርሱም መካከል የእንግሊዝ ንጉሥ ልጅ ልዑል ዱክ ኦፍ ግሎስተር ከተከተሏቸው መኳንንት ጋራ ወደ አሩሲ ለመሄድና አውሬ ለማደን ስለፈለጉ ተከታይና መንገድ መሪ ታዞላቸው ሄዱ። ተከታዮቹ በጅሮንድ ተሰማ ባንቴና[103] አቶ ዳባ ብሩ ናቸው።

ከጀርመን መንግሥት የመጡትም ምክትል መልእክተኞች ባሮን ቮን ፕሌሰን ወደ አሩሲ ለመሄድና የዝዋይን ሐይቅ ለመጐብኘት ፈልገው ስለጠየቁ ፍላጎታቸው ተፈጸመላቸውና ደስ ብሏቸው ኅዳር 12 ቀን በባቡር ተሣፍረው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ።

## የዘውዱ በዓል በያገሩ ስለ መከበሩ

የዘውድ በዓል ጥቅምት 23 ቀን አዲስ አበባ ላይ ሲከበር በሌላም ስፍራ ሁሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ተከብሮ ውሎ ነበር። ይኸውም በሐረር፣ በደሴ፣ በመቀሌ፣ በደብረ ታቦር፣ በደብረ ማርቆስ፣ በጎሬ በወለጋና በወላይታ ሶዶ ይህን በመሰለውም ከተማ ሁሉ ማለት ነው። ስለ አከባበሩ እንደ ተሰማው በየስፍራው ሕዝቡ ተሰብስቦ ካህናት መዝሙር እየዘመሩ፤ ሊቃውንት ዲስኩርና ቅኔ እየተናገሩ ተከብሮ ውሏል።

እንዲሁም ደግሞ ከኢትዮጵያ ውጭ በአሥመራ ከተማ በቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በቆንስላው ቤት የዘውድ በዓል ከፍ ባለ አኳኋን ተከብሮ የዋለ መሆኑ ተሰማ። በዚህም ምክንያት የቆንስሉ የአቶ ወዳጆ ዓሊ ትጋትና ብርታት በምስጋና ተነገረ። የበዓሉ አከባበር እንደሚከተለው ነበር።

ካህናቱ በዚያ ሌሊት በቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ማኅሌት ቆመው አደሩ። በማኅሌቱም ውስጥ ወይኴንን እምባሕር እስከ ባሕር፤ ወእምአፍላግ እስከ አጽናፈ ዓለም[104] የሚለውን ዚቅ አውርደው አመረገዱ። በቸብቸቦም እምርት ዕለት በዓልነ ነያ ኃይለ ሥላሴ አብርሃም ዘተመነየ ሰብሐ ወበዓለ ሰመያ[105] እያሉ አሸበሸቡ። ሕዝበ ክርስቲያኑም በቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ውስጥ ተሰብስቦ የደስታ ተካፋይ ሆነ።

እሑድ በቆንስላው ግቢ የምሳ ግብዣ ስለተደረገ ግቢው በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማና በልዩ ልዩ ጌጥ አጌጠ። የጃንሆይ ፎቶግራፍ በሰንደቅ ዓላማ ተከቦ ከመግቢያው ላይ ሆኖ

---

103 አጭር የሕይወት ታሪክ አባሪ 2 ገጽ 227 ይመልከቱ። (አመኀ)

104 ከባሕር እስከ ባሕር ድረስ፣ ከወንዝም እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ይገዛል። መዝ. 71 ቍ 8። (አመኀ)

105 ኃይለ ሥላሴ አብርሃም የተመኛት፣ የተመረጠችው ቀን እነሆ በዓላችን ናት። አመስግናት በዓልም አድርጋት። እነሆ ኃይለ ሥላሴ የተመኛት በዓላችን የታወቀች ዕለት ናት። (አመኀ)

ይታይ ነበር። በተወሰነው ሰዓት የኤርትራ አገር ገዥና ያገሩ መኳንንት፤ ካህናትም በቆንስላው ተገኝተው የምሳው ግብዣ ተጀመረ። በግብዣው መጨረሻ በሻምፓኝ ጊዜ ቆንስሉ አቶ ወዳጆ ዓሊ ንግግር አደረጉና አገረ ገዥው ደስ የሚያሰኝ መልስ ሰጡ። ከመኳንንቱም እነ ደጃች ኃይለ መለኮት ወልደ ሚካኤልና ሌሎችም ዲስኩር ተናግረው ሥነ በዓሉ ተፈጸመ።



ከግራ ወደ ቀኝ የተቀመጡ ቢሾፕ ዣሩሶ፣ ማዳም ፕላውማን፣ ደጃዝማች እምሩ ኃይለ ሥላሴ፣ ሚስተር ፕላውማን (የእንግሊዝ ቆንስል)፣ ማዳም አሞ

ሐረር ላይ የንግሡ በዓል ሲከበር


## ንጉሠ ነገሥቱ ምሕረት ስለ ማድረጋቸው

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የዘውድን በዓላቸውን ምክንያት በማድረግ በወህኒ ቤት ላሉ ለብዙ እስረኞች ምሕረት አድርገውላቸው ተለቀቁ። እንዲሁ ደግሞ ቁም እስር ሆነው በግዞት ለነበሩት ለደጃዝማች አባ ውቃው ብሩ በዚሁ ጊዜ ሙሉ ምሕረት አደረጉላቸውና በኅዳር 9 ቀን አዲስ አበባ ከቤታቸው ገቡ። እኒህ ሰው ከሁለት ዓመት በፊት በመንግሥት ጸጥታ ላይ ሁከት በማድረግ ወንጀል ተወንጅለውና ተፈርዶባቸው አንኮበር ላይ ታስረው የነበሩት ናቸው። ጥቂት ቆይተውም ቁም እስረኛ ሆነው ከከተማ ውጭ በግዞተኛነት ይኖሩ ነበርና አሁን ወደ ከተማ ለመግባት ዕድል አግኝተዋል።

## ደብረ ሊባኖስን ስለ መሳለም

የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን የልደት በዓል ለማክበር ግርማዊ ጃንሆይ ታኅሣሥ 20 ቀን ከጳጳሳትና ከመሳፍንት ጋር በአውቶሞቢል ወደ ደብረ ሊባኖስ ወረዱ። የተከተሏቸው ሊቀ ጳጳሳቱ አቡነ ቄርሎስ፣ አቡነ ሳዊሮስና አቡነ ይስሐቅ ሲሆኑ መሳፍንቱም ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን፣ ልዑል ራስ ኃይሉና ልዑል ራስ ሥዩም ናቸው። እንዲሁ ደግሞ ብዙዎች መኳንንት ተከተሏቸው። እነርሱም ራስ ከበደ መንገሻ፣ ደጃዝማች ብሩ ወልደ ገብርኤል፣

ቢትወደድ ጌታቸው አባተ፣ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ዓባይነህ፣ ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው፣ ደጃዝማች ደበበ አንዳርጋቸው፣ ደጃዝማች መንገሻ ይልማ፣ ደጃዝማች ጉግሣ አልዩ፣ ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ፣ በጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴ ከተማ፣ ፊታውራሪ አምባው ተክለ ማርያም፣ ግራዝማች ኃይለ ማርያም ገሠሠና ፊታውራሪ ጣሰው ዋለሉ ናቸው።



ዳግማዊ ምኒልክ ያሠሩት በኋላ የፈረሰው ገዳም

ደብረ ሊባኖስ ሲደርሱ የአገሩ ገዥ ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ በሰልፍ ተቀበሏቸው። ከዚያም በኋላ መለዮ ባደረጉ ፈረሰኞች ታጅበው ወደ ገዳሙ ወረዱና መጀመሪያ ቤተ ክርስቲያኑን ቀጥሎ የመስቀል ቤቱን ተሳለሙ። በማግሥቱም የሴት ደብር ወደሚባለው ገዳም ተሻግረው በቤተ ሰሊሆም የሚገኙትን ድኾች ጡረተኞችን ጐበኙ። ይህ ቤተ ሰሊሆም በ1910 ዓ.ም. በግርማዊነታቸው ገንዘብ ተቋቁሞ በእነ አባ ሐና አማካይነት የሚካሄድ የርሳቸው የራሳቸው የበጎ አድራጎት ድርጅት ነው።

የጡረታው ቤት ወንዶችም፣ ሴቶችም በየወገኑ የሚኖሩበት ሆኖ ጃንሆይ ለየክፍሉ አስታማሚና ጠባቂ አድርገውለታል። አልጋውና ልብሱ፣ ምግብና ሌላው አስፈላጊው ነገር ሁሉ እንደ ሆስፒታል ሥርዓት የተሰናዳ ነው። እህሉን በማስፈጨት ረገድ እንዳይቸገሩም ጃንሆይ በገንዘባቸው የወፍጮ መኪና አቁመውላቸዋል። ከዚህም ሌላ ለቤተ ሰሊሆም መረጃ የሚሆን ርስት ሰጥተዋል።

ጃንሆይን የተከተሉት መሳፍንትና መኳንንትም ይህን የበጎ አድራጎት ድርጅት በአዩ ጊዜ በብዙ እያደነቁ የንጉሠ ነገሥቱን ቸርነት አመሰገኑ።

ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱም በ1919 ዓ.ም. በግንቦት ወር ደብረ ሊባኖስን ለመሳለም ወርደው ሳሉ ቤተ ስሊሆምን ጐብኝተው ነበር። በድርጅቱም ስለተደሰቱ ለመናንያን መርጃ የሚሆን ቤት እንዲሠራ አዘው ሥራው ተጀምሮ ነበርና አሁን ሥራው አልቆ ስለተገኘ ጃንሆይ ቤቱን ጐበኙ ወደፊትም ቤቱ በተመደበለት አገልግሎት ላይ እንዲውል ትእዛዝ ሰጥተው ተመለሱ።

ታኅሣሥ 24 ቀን ዓርብ ግርማዊ ጃንሆይ የጻድቁን በዓል በማክበር ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዱ። ታቦት ከመውጣቱም በፊት ከመነኰሳቱ መካከል ሽማግሌዎቹንና ዋና ዋናዎቹን አስጠሩና በሊቀ ጳጳሳቱና በልዑል ራስ ካሣ ፊት የሚከተለውን የምክር ቃል አስነበቡላቸው።

> የሚያሰክር መጠጥ ሰውነትን የሚጐዳ፣ ናላን የሚያጠፋ ስለሆነ የመንፈሳዊ አብነት የሆናችሁት እንኳን እናንት አባቶቻችን ዓለማውያንና ሥጋውያን የሆኑ ሰዎችም የሚያሰክር መጠጥ ሰውነትን የሚጐዳ መሆኑን ዐውቀው በፈቃዳቸው ብዙ ሰዎች ትተውታል። እናንተማ የሙታንን ነፍስ ለማስማር ወደ ተዝካር ቤት ሕያዋንን ለማማለድ ወደ ዝክር ቤት፤ ወደ ግብርም በምትሄዱበት ጊዜ የሚያሰክርና ሰውነትን የሚጐዳ መጠጥ መጠጣት ትታችሁ፤ ሰውነት የሚያለመልም ለጤና የሚስማማ ቢገኝ ብርዝ ባይገኝ ጭልቃና የብቅል ጠላ እየጠጣችሁ ብትመለሱ መልካም ነውና ይህን ለማድረግ ፈቃዳችሁ ይሁን። በእናንተ ተጀምሮ ለሌላውም ለገዳማቱ ሁሉ በዚሁ ዓይነት ቢደረግላቸው በናንተ ስለ መጀመሩ ብቻ ለደብረ ሊባኖስ ትልቅ ክብር ይሆናል።
>
> ገድለ ተክለ ሃይማኖት ሲነበብ ወበእንተ ሕርመትሂ ተዐቀቡ እምበሊዐ ሥጋ ዝህፃ[106] የሚለውን ቃል ሰምተናል።
>
> ይህንም ማለቱ በሥጋችሁም በነፍሳችሁም የምትጠቀሙ ስለ መሰለኝ ነው እንጂ ይህ ትንሹ የመጠጡ ነገር ይቅርና ትልቁን ምንኲስናውንም ቢሆን በፈቃዳችሁ ያደረጋችሁት ነው እንጂ በትእዛዝ አይደለም። ስለዚህም በተዝካርና በዝክር የሚያሰክር መጠጥ እንዲቀር የልባችሁ ፈቃድ መሆኑን አስታውቁኝ።
>
> የልባችሁ ፈቃድ መሆኑን ከአስታወቃችሁኝ በኋላ ለመኖሪያችሁ የተወሰነላችሁ የገዳሙ ቦታ እንደ ማኅበረ ሥላሴ በቅጥር እንዲለይ አደርግላችኋለሁ።

መነኰሳቱም ይህን ቃል ከሰሙ በኋላ ወደ ሌሎቹ መነኰሳት ዘንድ ሄደው ተመካክረው ተመለሱና በተዝካርና በዝክር ጊዜ የሚያሰክር መጠጥ ቀርቶ ቢገኝ በብርዝ ባይገኝም በጭልቃና በብቅል ጠላ እንዲሆን የልባችን ፈቃድ ነው ብለው ተናገሩ። በተጨማሪም የመነኰሳቱና የደብተራው ቦታ ተከልሎ ቢለይልን በተሻለ ነበር ብለው አመለከቱ። ጃንሆይም ይህን ሰምተው እንግዲህ በዚሁ መሠረት ይፈጸማል ብለዋቸው መነኰሳቱ እጅ እየነሡ ተመለሱ።

106 ምግብን ስለመተውም፤ ሥጋን ከመመገብ ተጠበቁ/ተከልከሉ። ገድለ ተክለ ሃይማኖት። (አሙኀ)

ከዚህ በኋላ ታቦት ወጥቶ ዑደት ተደረገና ሊቀ ጳጳሳቱ ባርከው አሳርገው ታቦት ሲገባ 11 ጊዜ መድፍ ተተኰሰ። ግርማዊ ጃንሆይ በዚህ ቀን ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት ዘውድና ላንቃቸውን ገጸ በረከት ሰጡ። ለካህናቱም ብዙ ሽልማት ሰጥተው ደስ አሰኟቸው። ለመነኰሳትና ለነዳያንም ብዙ ገንዘብ መጸወቱ።

ከቤተ ክርስቲያንም ተመልሰው በታላቅ ድንኳን ውስጥ ለመኳንንትና ለካህናት ለሠራዊትም ግብር አደረጉ። በማግሥቱ ጥር 25 ቀን ቅዳሜ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው ከእኩለ ቀን በኋላ ከቤተ መንግሥታቸው በደኅና ገቡ።

## የጳጳሳት ሀገረ ስብከት ስለ መደልደሉ

የእስክንድርያ ፓትርያርክ አቡነ ዮሐንስ በ1921 ዓ.ም. በግንቦት ወር ካይሮ ላይ ጵጵስናን የሰጡዋቸው አራት ኢትዮጵያን መምህራንና ከሰባት ወር በኋላ አዲስ አበባ ላይ ጳጳስ ያደረጓቸው አቡነ ሳዊሮስ በአዲስ አበባ ከሊቀ ጳጳሳቱ አቡነ ቄርሎስ ጋር በአንድነት እየሠሩ ቆይተው ነበር። ምክንያቱም የጳጳሳቱ ሹመት አዲስ ነገር ስለሆነ ሕዝቡ ባለማወቅ ክፉ ነገር እየተናገረ እንዳይጐዳና እነሱም በሥራው እንዲለምዱ በማለት ነበረ። አሁንም ግን ስለተለመደ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በጥር 22 ቀን 1923 ዓ.ም. በጻፉት ደንብ ሀገረ ስብከቱን ከዚህ በታች እንደ ተጻፈው ደልድለው ወሰኑላቸው።

አንደኛ ለአቡነ ሳዊሮስ፤ የሸዋ ደቡብና የጉራጌ አገሮች፣ ከምባታና ወላይታ፣ ሲዳሞና ቦረና፣ አሩሲና ገሙ ተመደበላቸው።

የአድራሻቸውም አርእስት «አቡነ ሳዊሮስ ጳጳስ ዘደቡበ ኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘደብረ ሊባኖስ ተላዊ አሰሩ ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት» እንዲባል ተወሰነ።

ሁለተኛ ለአቡነ ይስሐቅ ትግሬ በሙሉ ዋግና ላስታ፣ ዋድላና ደላንታ ተመደበላቸው።

የአድራሻቸውም አርእስት «አቡነ ይስሐቅ ጳጳስ ዘሰሜነ ኢትዮጵያ ተላዊ አሰሩ ለአቡነ ሳሙኤል» እንዲባል ተወሰነ።

ሦስተኛ ለአቡነ አብርሃም በጌምድርና ስሜን፣ ጐጃም በሙሉ ተመደበላቸው።

የአድራሻቸውም አርእስት «አቡነ አብርሃም ጳጳስ ዘምዕራበ ኢትዮጵያ ተላዊ አሰሩ ለአቡነ ሐራ» ተወሰነ።

አራተኛ ለአቡነ ጴጥሮስ ወሎ በሙሉ ከሸዋ መንዝና ኤፍራታ፣ አንጾኪያና ግድም፤ ሐረር ተመደበላቸው።

የአድራሻውም አርእስት «አቡነ ጴጥሮስ ጳጳስ ዘምሥራቀ ኢትዮጵያ ተላዊ አሰሩ ለአቡነ ኢየሱስ ሞዓ» እንዲባል ተወሰነ።

አምስተኛ ለአቡነ ሚካኤል፤ ወለጋና ኢሉባቦር፣ የሼኽ ሆጄሌ አገር በሙሉ፣ ከፋና ጊሚራ ተመደበላቸው።

የአድራሻቸው አርእስት «አቡነ ሚካኤል፤ ጳጳስ ዘአዜበ ኢትዮጵያ ተላዊ አሰሩ ለአቡነ ዜና ማርቆስ» እንዲባል ተወሰነ።

ከዚህም በኋላ ጳጳሳቱ በውሳኔው መሠረት በየሀገረ ስብከታቸው ማስተማርና መስበክ ጀምረዋል።



ላይ ከግራ ወደ ቀኝ፣ አቡነ አብርሃም፣ አቡነ ሚካኤል። ታች፤ አቡነ ጴጥሮስ፣ አቡነ ይስሐቅ
የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት



እቴጌ መነን



ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ



ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከልዑል መኰንን ጋር



ጃንሆይና እቴጌ ዙፋን ላይ ተቀምጠው




ልዕልት ፀሐይ



ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን





ከላይ፤ ልዕልት ፀሐይ፣ ልዕልት ተናኘ ወርቅ፣ እቴጌ መነን፣ ልዕልት ዘነበ ወርቅ፣ ልዕልት ወለተ እስራኤል
ከታች፤ እቴጌ መነን፣ ልዑል አስፋ ወሰን፣ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ ልዑል መኰንን

ንጉሣዊ ቤተሰብ



ግብዣ ላይ



ከጀርመን ሚኒስትርና ባለቤቱ ጋር



ልዑል መኰንን ከራስ ሙሉጌታ ጋር



ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሲያስቀድሱ






ከላይ፣ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት (አሁን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ)። ከታች ፖስታ ቤት አዲስ አበባ በ1920ዎቹ







**መድኃኒት መሸጫ ቤቶች።**


**አዲስ አበባ በ1920ዎቹ**





አራዳ፤ ከላይ ወደ እሪ በከንቱ የሚሄደው መንገድ። ከታች ደጎል አደባባይ አካባቢ
አዲስ አበባ በ1920ዎቹ








አራዳ፤ ከላይ ራስ መኰንን ድልድይ አካባቢ፣ ከታች ታክሲ ተራ
አዲስ አበባ በ1920ዎቹ





የእሳት አደጋ መከላከያ
አዲስ አበባ በ1920ዎቹ





የዚህ ታሪክ ጸሐፊ አቶ መርስዔ ኀዘን ተረከበው ያስተዳደሩት የመጀመሪያው ዘመናዊ ወህኒ ቤት (ከርቸሌ) አዲስ አበባ በ1920ዎቹ





ከላይ፤ 200 ያህል ደንበኞችን ያስተናግድ የነበረው የቴሌፎን ማዞሪያ፤ ከታች አዲስ አበባ ከአየር ላይ ፎቶ
አዲስ አበባ በ1920ዎቹ





**ከላይ፤ ማዘጋጃ ቤት፤ ከታች እቴጌ ጣይቱ ሆቴል**

**አዲስ አበባ በ1920ዎቹ**

ተጨማሪ ማንበብ ከፈለጉ መጽሐፉን ከ

www. mersie-hazen.com

ማዘዝ ይችላሉ